
# አባታችን ሆይ !



ከሊቀ ሥልጣናት ሀ/ማርያም ወርቅነህ

አዲስ አበባ ፲፱፻፹ ዓ. ም.

በትንሣኤ የማሳተሚያ ድርጅት ታተመ ።





## መቅድም ፤

ጌታችን ኢየሱስ ስለ ጸሎት ጠቃሚነት አስፈላጊነትም ሲናገር የጸሎቱን ስልትና ዓይነት ገልጦ አስተምሯል ፤ ከዚህም ጋር እርሱ ያስተማረው ጸሎት ቃላቱ ሳይቀሩ ምርጦች የሆኑ ብዙ ምሥጢርን ያዘሉ ሲሆኑ እግዚአብሔር አምላክን አባታችን ብለን በድፍረት እንድንጠራው ፤ አባታችንም አድርገን እንድንቀርበው በማመልከት «አቡነ ዘበሰማያት» የሚለውን ጸሎት አስተማረን ። አሁንም እኛ የጸሎታችን መጀመሪያ መደምደሚያም ይኸነኑ « አቡነ ዘበሰማያትን » በማድርግ ስንጠቀም እንገኛለን ።

በመሠረቱ አንድ ሰው መጸለይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ተገቢ መሆኑን፤ ግዴታውምእን ደሆነ መገንዘብ አለበት ። ይህም ከሆነ ዘንድ ስለ ጸሎት ጠቃሚነት አስቀድሞ በስፋትና በጥልቀት ማወቅና መረዳት አለበት ።

ጸሎትም ማለት ምድራዊ ሰው ሰማያዊነቱን የሚገልጥበት ፣ ከሰማያዊው አምላክ ጋር የሚገናኝበት መንገድ ነው ፤
ይህንም አስተያየት በማስፋፋት የቤተ ክርስቲያናችን የሕግ መጽሐፍ የተባለው ፍትሐ ነገሥት

«ጸሎት ማለት ሰው ከልዑል እግዚአብሔር ጋር የሚያደርገው ንግግር /ውይይት/ ነው...... » ሲል ገልጧል ። /ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፬ ቍ. ፭፻፳፭/

በእውነትም ስንመለከተው ጸሎት ማለት ከታላቁ አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር በጽሞና የሚደረግ ውይይት ነው ፤ እንግዲያውስ ማንም ሰው ጸሎት ሲይዝ ሌላ ሐሳብ ማሰብ ፤ ሌላም ነገር መመልከት ፈጽሞ ክልክል መሆኑን ማወቅ አለበት ። እንዴት ሰው ያንን ታላቅ አምላክ አባቱ አድርጎ በፊቱም አቅርቦ በሚያነጋግርበት ጊዜ ሌላ ነገር ያስባል ? ሌላ ነገርስ ይመለከታል ? እንግዲህ በጸሎት ጊዜ ሌላ ነገር የሚያስብ ፤ ሌላም የሚመለከት ሰው ከኖረ ከእግዚአብሔር ጋር አይደለም ማለት ነው ፤ እንግዲያውስ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር አለ ለማለት አይቻልም ይኸም ከሆነ ጸሎቱ ከንቱ ነው ።

እውነተኛ ምእመን ግን የማይታየውን እግዚአብሔርን በሃይማኖት እየተመለከተ የሚያሻውን ሁሉ ይለምነዋል ፤ ስለ ውለታውና ስለ በጎ አድራጎቱም ደግሞ ያመሰግነዋል ፤ በጠቅላላውም ለእግዚአብሔር ተገቢውን አምልኮት ያቀርባል ማለት ነው ።





እንግዲህ ጸሎት ስንጸልይ አፋችንን ከልባችን ፤ ልባችንንም ከአፋችን አንድ አድርገን መጸለይ አለብን ፤ እንዲህ አድርጎ የሚጸልይ ሰው እግዚአብሔርን እንደ አባትነቱ ይመለከተዋል ፤ እግዚአብሔርም እንደ ልጁ ተመልክቶ የጠየቀውን ሁሉ ሳይንቅ ፣ ሳያቀል ፤ ሳያጣጥልም ይሰጠዋል ።

ጸሎት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጥ ትልቅ የፍቅር መግለጫ መሣሪያ ነው ፣ ማለት ሁልጊዜ የሚጸልይ ሰው እግዚአብሔርን ከመውደዱ የተነሣ ሁልጊዜ እርሱን ለመገናኘትና ለመወያየት የሚፈልግ መሆኑን ያረጋግጣል ፤ እንዲሁም እግዚአብሔር አምላክ ከፍቅሩ ብዛት የተነሣ ሰው የለመነውን ሁሉ ይሰጠዋል፣ ጩኸቱን ያዳምጥለታል ፤ ወደ ችግሩም ይመለከትለታል ። ስለዚህ ብዙዎቹ ምእመናን በጧትና በማታ በየዕለቱም ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ግንኙነትን ለማድረግ እርሱንም ከመናፈቅ የተነሣ ያለማቋረጥ ጸሎት ሲያደርጉ ይገኛሉ ።

ይኸም የጸሎት አስፈላጊነት ከጥንት ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር አብሮ የተገኘ አስፈላጊ ነገርም ሲሆን ቀደም ብሎ የጸሎቱ ዓይነት የተወሰነ አልነበረም፤ ስለዚህም እያንዳንዱ ካህን እያንዳንዱም ነቢይ





በፈለገው መልክ ይጸልይ እንደ ነበረ በቅ. መጽሐፍ ልንረዳ እንችላለን ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ይኸን ዓለም አድሶ አዲሱን ክርስቲያናዊ ሥርዓት ማኅበር ከመሠረተ ወዲህ አዲስ የጸሎት ዓይነት « አቡነ ዘበሰማያት » የሚለውን አስተምሯል ።

እንደ ግብዞች ጩኸ ፤ አብዝቶ እስኪዘነጋ ድረስ መጸለይን ጌታ ነቅፎ እውነተኛውና ልከኛው ጸሎት ይኸ መሆኑን በማስረዳት « አናተስ እንዲህ ጸልዩ» ብሎ ለሁሉ የሆነውን ሊጨመር በትም፤ ሊቀንስበትም ፤ የማይገባውን ጸሎት «አቡነ ዘበሰማያት »የሚለውን አስተማረ /ማቴ.፮. ፭—፲፫/

የጸሎትን ሥነ ሥርዓት ሳይጠብቁ የጸሎትን ትርጉምና ጠቃሚነትን ሳያውቁ እንጸልያለን የሚሉ ብዙዎች ናቸው ፤ እነርሱም ከልማድ የተነሣ ብቻ የሚጸልዩ ናቸው ፣ ይኸ ግን ተገቢ አይደለም።

እንዲግህ ቋሚ ለኋሚ ፤ ገረድ ደንገጥር ሌላ አሽከር ፤ ጌታ እመቤት ፤ ካህን የጨዋ ልጅ ሳይል፤ ወይም በጉዞ ላይ ሆኖ በየብስ ፤ በባሕር ፤ በአየር የሚጓዝ ፤ ወይም በእሥር ቤት ያለ ችግረኛ ፤ ወይም በተወሰነ ሥራ ላይ ያለ አማኝ ቢሆንም ችግር ሳይገጥመው በቀላሉ ሁሉም ሊጸልየው የሚ





ገባውን ይኸን « አቡነ ዘበሰማያት » የሚለውን ጸሎት ጌታ ለደቀመዛሙርቱ አስተማረ ፤ ስለዚህ አሁንም ዕለትና ሰዓት ሳንወስን ሁላችንም ይኸን ጸሎት ልንጸልየው ይገባናል ። ከሁሉ በፊት ግን የጸሎቱን ትርጉም ፣ ምሥጢሩንም ደህና አድርጎ መማርና መመርመር ማወቅም ለሁሉ ያስፈልጋል።

ብዙዎች ሰዎች ሲጸልዩ

፩. ሕሊናቸውን ሳይሰበስቡ በልማድ ብቻ እንጸልያለን ይላሉ ፤

፪. ሌሎች ደግሞ የጸሎቱን ምሥጢር ሳይረዱ በተለይም ይኸ ጸሎት ከሁሉ የበለጠ መሆኑን ሳይገምቱ ብዙም ጥንቃቄ ሳያደርጉ እንዲሁ ሲያነበንቡ ይገኛሉ ፤

፫. በአጠቃላይ ደግሞ እናንት ይቅር በሉ እኔም ይቅር እንድላችሁ የሚለውን አምላካዊ ትዕዛዝ ሳያከብሩና ሳይፈጽሙ በቂምና በተንኮል ሁነው የሚጸልዩ ብዙዎች ናቸው። ግን ዋጋቸውን እንዳያጡ ከቂምና ከበቀል ነፃ ሁነው መጸለይ ይገባቸዋል « እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱና ዕወቁ » ሲል ነቢዩ ዳዊት ተናግሯል /መዝ. ፻፵፬. ፲፰/ ። ይኸም ማለት እግዚአብሔርን በጸሎት ቅረቡት ቸርነቱንም ቅመሱት ማለት ነው ። እር

ሱንም ለምኖ ያጣ የለም እርሱ ቸር ነውና ፤ ለሁሉም የለመኑትን ይሰጣልና ፤ ስለዚህ ቸርነቱን ቅመሱ ፤ ከዚህ በኋላ ማንነቱን ዕወቁ ከዚያ በኋላ ለራሳ ችሁ ለምኑ ፤ ጸልዩ ማለቱ ነው ።

ይኸን የመሰለ ጸሎት የሠራልን ፤ ያስተማረን ፤ አባትነቱንም ያስታወቀን አምላክ ከፍጹም ቸርነቱ የተነሳ ነው ፤ ይኸም ፤ ከሆነ ዘንድ እርሱ ያስተማ ረንን ጸሎት ትርጉሙን ምሥጢሩንም ልናውቅና ልንረዳ ፤ እንደፍቃዱም ልንጸልይ ይገባናል ፤ እን ግዲያውስ ወደመካከሉ ገባ ብለን የአቡነ ዘበሰ ማያትን ትርጉምና ምሥጢር እንሚደከተለውእን መርምር ፤ እግዚአብሔር አባታችን የመረዳትን መንፈስ ያድለን ።

አ ሜ ን ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተማርያም ወርቅነህ ።





## መግቢያ ፤

ይኸ ጌታችን ያዘዘውወይም «አቡነ ዘበሰማያት» በመባል የታወቀው ጸሎት በመጠን በኩል በጣም አጭር መስሎ ይታያል ፤ ግን በጥቂት ቃላት ብዙ ነገሮችን ይገልጣል ፤ ምሥጢሩ ሰፋ ያለና ብዙ ነገሮችን አጠቃሎ የያዘ ፤ ሥጋዊውንም መንፈሳዊውንም ፍላጐታችንን የሚሸፍን ፤ ይኸ ቀረህ ይኸ ጐደለህ የማይባል ፤ ለሁሉም ተስማሚ የሆነ ፍጹም ጸሎት ነው ። ለጸሎትም ሁሉ ምሳሌነት ያለው በዚህ መልክ ሁል ጊዜ መጸ ለይ እንዳለብን የሚያስረዳ ጸሎት ነው ።

ይኸን ጸሎት የሠራው ያስተማረውም ፍጹም አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መሆኑ ጸሎቱም ፍጹም ነው ፤ በፍጹም አእምሮ ለመመ ርመርና ለማወቅ ለፍጡር የማይቻል ሲሆን የነ በረውን መለኮታዊ ፈቃድ ጌታ ግልጦ ያስተማ ረው ነው ፤ ስለዚህም አማኒ የሆነ ሁሉ እኔን አይመለከተኝም በማለት ቸል ሳይል ሊጸልየው የሚገባ ጸሎት ነው ። በአቡነ ዘበሰማያት ውስጥ የሚገኙ ቃላት እያንዳንዳቸው ከፍ ያለ ትርጉም ፤ ከፍተኛም ምሥጢር ያላቸው ናቸው ፤ እያንዳንዱም





ቃል ቅዱስ ቃል ነው ፤ አምላካዊም ቃል ነው ።

ይኸ ጸሎት በጣም አጭር ሁኖ ሁሉን ሰብ ስቦ የያዘ እንደመሆኑ ጩኸን አሰምተን ሰው ይይልን ይስማልንም ብለን እንዳንጸልየው ማስ ጠንቀቂያና መመሪያ ሰጥቶ ከሁሉም የተለየ ጸሎት አድርጎ ሰጥቶናል ፤ መለኮታዊ ጸሎት እንደ መሆኑ በብዙ ጥንቃቄ እንድንጸልየው ያስገነዝ በናል ፤ ማለት በመንፈስ ሁነን በሰቂለ ሕሊና በአንቃዕድዎ አዕይንት ሁነን እንድንጸልየው ያስገነዝበናል ።

ኣሳዛኙ ነገር ይኸን ጸሎት ከሕፃንነት ዕድሜ ያችን ጀምሮ ያጠናነው ስለሆነ እንደ አውቶማ ቲክ እናነበንበዋለን እንጂ ስሜት ኑሮን ምሥ ጢሩ ገብቶን እንደ ጌታ ፈቃድ የምንጸልየው አለመሆኑ ነው ። ከሁሉ በፊት የአምላክ ፈቃድ ምንድን እንደሆነ ማወቅና እንደ ፈቃዱ መጸለይ አለብን ፤ ቀጥሎም ምስጢሩ ምን እን ደሆነ አውቀን ገብቶንም መጸለይ አለብን ፤ ከመ ንፈስ ተራቁተን እንዲሁ ከሕሊናችን ውጭ በሆነ መልክ እንጸልየዋለን ብንል ጌታ የነቀፈውን የጸሎት ዓይነት መልሰን እኛም በእርሱ ጸሎት ላይ እናስገባለን ማለት ነው ። ጌታ የጠላው





የነቀፈውም ጸሎት ይኸን የመሰለውን ነው ፤ እርሱም እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀናል «አሕዛብ በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ ነርሱ በከንቱ አትድገሙ ። ስለዚህ አትምሰሏቸው ። ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስ ፈልጋችሁን ያውቃልና» (ማቴ ፮. ፯) ።

እንግዲህ ልባችንን ከአፋችን ፤ አፋችንንም ከልባችን አድርገን ካልጸለይን ሕሊናችን ከትር ከጉሙ ከምሥጢሩ ተራቁቶ ከንፈራችን ብቻ ይን ቀሳቀሳል ማለት ነው ። ለሥጋችንም ለመንፈሳች ንም ምን እንደጠየቅን አናውቀውም ፤ ከአባታ ችን ምን እንደምንሻ ምንስ ይጅ እንደምንጠና ቢጠይቁን እንኳን የምንሰጠው መልስ የለንም ። እንግዲያውስ በዚህ መልክ እንድንጸልይ ስሙንም እንድንጠራ ከቶ አላስተማረንም ። በምን ጸልይበት ጊዜ አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ብለን ጠርተነዋል እርሱም ደግሞ እንደ ለመንከው ይሁንልህ እንደ ሃይማኖትህም ይደረ ግልህ ይለናል ፤ ግን ምኑን እንደለመነው ምንስ እንዳልን ሳናውቀው ለየትኛው ጸሎታችን መልስ አገኘን እንላለን ?

እንግዲህ ሰዎች እንዴት መጸለይ ምን ማለት

እንደሚገባቸው ራሱ ገልጦ ያስተማረው ስለሆነ መመሪያውን ጠብቀን እንደመመሪያው መጸለይ አለብን ።

ቀድሞ ያልነበረ ለኛ ለክርስቲያኖች በአዲስ ኪዳን የተዘጋጀልን ጸሎት አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ነው ።

እርሱም እንደ ወንጌላዊ ማቴዎስ አገላለጥ ይኸን ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ስለ ጸሎት በሚናገርበት አንቀጽ ጠቅሶ ለመናገር እንዲህም ብላችሁ ጸልዩ ለማለት « አንትሙሰ ከመዝ ጸልዩ » ብሎ ራሱ እንደ አምላክነቱ አውቆ ያስተማረው ነው /ማቴ ፮..፱—፲፫/ ።

ወንጌላዊ ሉቃስ እንደገለጠው ደግሞ ደቀመዛሙርቱ ጸሎት እንዲያስተምራቸው በጠየቁት ጊዜ ይኸን ጸልዩ ለማለት አቡነ ዘበሰማያትን እንደነገራቸው እንረዳለን / ሉቃ. ፲፩. ፩—፬/ ። እንዲሁም ሌላው አስተያየት ይኸን ጸሎት ጌታ ሁለት ጊዜ እንዳስተማረ የሚናገሩ አሉ ፤ ስለዚህም በመጠኑም ቢሆን የቃል መለየየት በመካከሉ ሊገኝ ቻለ ፤ በዚህም ሆነ ወይም በዚያ የጸሎቱ ሠሪ አስተማሪም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ የታመነ ነው ፤ ስለዚህም ጌታ ያስተማረው





ጸሎት እየተባለ ይጠራል ፤ ሁሉም አክብሮ በየዕለቱና በየሰዓቱ ይጸልየዋል ። ይኸም ጌታችን ያስተማረው ጸሎት በአጠቃላይ በ፫ ታላላቅ ክፍል ይካፈላል ።

ይኸውም ምስጋና ፥ ልመና ፥ መደምደሚያ የሚል ነው ። ይሁን እንጂ በያንዳንዱ ክፍል ደግሞ ሌሎች የተለያዩ ጥያቄውች ይገኛሉ ፤ እነዚህም ክፍሎች በአንዳንድ ሊቃውንት ዘንድ በ፭ ይከፈላሉ በሌሎች ደግሞ በ፮ ፥ በሌሎችም እንዲሁም በ፯ ይከፈላሉ ። በሰባት የሚከፍሉት ሊቃውንት ትክክለኛ እንደሆኑ ይገመታል ፥ ምክንያቱም «ኢታብአነ ውስተ መንሱት » የሚለውንና« አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ ዕኩይ » የሚለውን ከሁለት ስለሚከፍሉት ነው ።

በስድስት የሚከፍሉት ደግሞ « ይትቀደስ ስምከ » የሚለው ቃል ምስጋና እንጂ የልመና መልክ ስለሌለው ከክፍልነት ውጭ በማድረጋቸው ነው ።

እንግዲህ ይኸ ጸሎት በ፯ ክፍል ጥያቄዎች የተመሠረተ ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ክፍል ፫ቱ ጥያቄዎች የእግዚአብሔርን ምስጋና የሚመለክቱ ናቸው ፤ የተቀሩት ፬ቱ ግን የሰውን ችግር የሚገልጡ እንዲሁ ለሌላው ሊለምንለት በጸሎትም





ሊያስበው የሚገቡ መሆናቸውን የሚገልጥ ነው እንግዲያውስ ይኸ ጸሎት እንደ ፲ቱ ቃላተ ኦሪት በ፪ ታላላቅ ክፍል ይከፈላል ማለት ነው ፤ ይኸውም የመጀመሪያው ክፍል ለታላቁ አምላክ ለእግዚአብሔር የሚሆን ክፍል ሲሆን ለእውነተኛው አምላካችን ምስጋና ማቅረብ የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት ይሆናል ።

በ፪ኛው ክፍል ደግሞ ሰው ለመሰሉ ለሰው ሊጸልይለት እግዚአብሔር ችግሩን እንዲያስወግድለት ይቅርታም እንዲያደርግለት የሚያቀርበው ምሕላና ጸሎት ነው ።

ይኸን ልዩ ጸሎት በየዕለቱ እንድንጸልየው ጌታ ያዘዘው ስለሆነ ያለምንም ምክንያት ሁላችንም መጸለይ አለብን ፤ ጸሎቱም ውኩፍ ነው ፤ ያዘዘው የሠራውም እርሱ ጌታ እንደመሆኑ ለመስማት ፤ ለመቀበልም ዝግጁ ነውና ።

በብዙ አባቶች የተቀመሩ ብዙ የጸሎት ዓይነቶች ይገኛሉ ፤ ሁሉም በመንፈሰ እግዚአብሔር እየተመሩ የተደረሱ ቢሆኑም ይህ ጌታችን ያስተማረው ጸሎት ግን ከሌሎች ጸሎቶች በጣም የበለጠ ስለሆነ ሁላችን ቅድሚያን ለእርሱ መስጠት አለብን ምክንያቱም ፤





፩. የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ በትክክል የሚገልጥ እግዚአብሔርም ያዘዘው ጸሎት ነውና ።

፪. የሰውን ሁሉ ፍላጐት የሚያሟላ ፤ ስለመንፈሳዊውም ፍላጐቱ ገልጦ የሚያስረዳ ጸሎት ነውና ።

፫. « አቡነ ዘበሰማያት » በሚለው ጸሎት መመስገን ፤ በዚህም ጸሎት አማካይነት ልመና ማቅረብ የልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ነውና ስለዚህ ሁላችን አዘወትረን ይኸን ጸሎት መጸለይ አለብን ፤ እርሱም ፈጥኖ ይሰማናል ። እግዚአብሔር አምላክ አሳጥሮ አጠቃሎ ፈቃዱ ምን እንደሆነ የገለጠበት ጸሎት ነው ፤ ሁልጊዜም በዚህ ጸሎት አማካይነት እንድንገናኘው ፤ እንድንለምነው ምስጋናም እንድናቀርብለት ይፈቅዳል ። በዚህ ጸሎት አማካይነቱ እግዚአብሔርን ስንለምን እንደሚሰማን « እውነት እውነት አላችኋለሁ ከአብ የምትለምኑትን ሁሉ በስሜ እንዲሰጣችሁ » ሲል ራሱ ክርስቶስ በማይታበል ቃሉ ተናግሯል /ዮሐ. ፲፮ - ፳፫/ ።

እግዚአብሔርን አባት ብሎ ፤ አባትም አድርጎ ይኸን ጸሎት የሚጸልይ ሁሉ ፍጹም የሆነ ተስሚነት አለው ፤ ስለዚህ ጊዜና ቦታ ሳንወስን ፤ ምክንያትም ሳናበዛ እንጸልየው ዘንድ ይገባናል ። የጌታ

ጸሎት ጥልቅ ምሥጢር ያለው ተቀድቶ የማያልቅ የማይደረስበትም ሲሆን በመጠኑም ቢሆን እያንዳንዱ ቃል ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙ ከነሐተታው እንደሚከተለው ተገልጧል ፤ ስለዚህ እያንዳንዱ ምእመን ይኸ ምን ማለት ነው እያለ ከመጠየቅ ይድን ዘንድ ሁሉን የምታብራራ ይኸችን የአቡነ ዘበሰማያት ትርጉምን « አባታችን ሆይ! ..» በሚል ርእስ አዘጋጅተን እናቀርባለን ።

አዘጋጁ ።





## ጠቅላላ መግለጫ ስለ ጸሎት ።

ሕይወታችን ከአምልኮት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ሁሉጊዜ ለአምላካችን አምልኮትንም ሳንፈጽም ልንኖር ከቶ አንችልም ፤ አምልኮት ማለት በልዩ ልዩ መልክ የሚፈጸም የተገዥነት ምልክት ነው ። ይኸም በልዩ ልዩ መልክ የሚገለጥ ሲሆን ዋናው መግለጫ ግን ጸሎት ነው ። የጸሎትን አስፈላጊነትንና የጸሎትን ስልት ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ በተራራው ትምህርቱ ሰፋ አድርጎ ገልጠ ተናግሮት እናገኛለን ።

ጸሎትንም ማንኛውም ሰው በማንኛውም ዕለትና ሰዓት ማድረግ ሲገባ ስለቦታውና ስለጸሎቱ ስልት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መግለጫ መስጠት ብቻ ሳይሆን ምን ዓይነት ጸሎት መጸለይ እንዳለብን ምሳሌ የሚሆን « አቡነ ዘበሰማያትን » አስተምሮናል ።

ጸሎት የሚጸልይ ሰው ከሁሉ በፊት ልቦናውን ሰብስቦ ወስኖም በሐሳቡ መሬትን ለቆ ወደ ሰማይም መጥቆ ከሰማያዊ አባቱ ጋር ግንኙነት አድርጎ መጸለይ ተገቢ ነው ።

እንዲሁም በተሰበረ ሕሊና በጠራ ልቡና ሁኖ





በእውነትም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምኖ እግዚአብሔርን አባባ ለማለት የቀረበ ሆኖ መገኘት አለበት ።

ሰማያውያን መላእክት የተፈጥሮ ጠባያቸውን ሳያሳድፉ ከመገናታቸው ጋር የማያቋርጥ ምስጋና ለሰማያዊው ንጉሥ ለሁላችን አባት ለእግዚአብሔር ሲያቀርቡ በመገናታቸው የመላእክትን ምስጋናቸውን እንደወደደላቸው « በሰማይ መመስገን ፈቃድህ እንደሆነ እንዲሁም በምድር » እያልን እንድንጸልይ ክርስቶስ አስተምሮናል ።

እንግዲህ ጸሎት ማለት በእግዚአብሔር ፊት የሚናገር መሥዋዕት ማለት ነው ፤ ራሱን ለአምላክ መስጠት ተገዥነትንም መግለጥ ስለሆነ የምድር ሰው የሰማይ መልአክ ሁኖ በትክክል ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ እግዚአብሔር የሚቀበለውን ጸሎት መጸለይ ተገቢ ነው ።

ጸሎት የእግዚአብሔር ክብር መግለጫ ነው ፤ ማለት ፈጣሪ ፍጥረታትነቱን ፤ አምጻኤ ዓላማትነቱን መግለጥ ስለሆነ እንደገናንነቱ ፤ እንደአምላክነቱ የክብር ምስጋና ለማቅረብ ዝግጁ ሁኖ መቅረብ እንጂ የምንግዴ መጸለይ ተገቢ አይደለም ፤ ይኸንን ካላደረግን ግን ስሙን ከንቱ ማድረጋችን እንደሆነ ማወቅ አለብን ።





መላእክት ለአምላክ የሚገባውን ምስጋና እርሱ በሚፈቅደው መልክ የሚያቀርቡ ከሆነ እኛም እንደነርሱ እርሱ በሚፈቅደው መልክ መጸለይ ግድ አለብን ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሁላችን አምላክ ስለሆነ እነርሱ ግዴታቸውን አውቀው ሲሠሩና ሲወጡ ፤ በዚያውም ሲመሰገኑ እኛ ግዴታችንን የማንፈጽምበት ምክንያት ከቶ ሊኖረን አይቻልምና ።

እንዲያውም ግዴታችንን ከመፈጸማችን ጋር የሰው ፍላጎቱ ብዙ እንደመሆኑ ያን ሁሉ ለማሟላት ሲባል ከመላእክት ይልቅ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ የምንጠይቀው ብዙ እንደመሆኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ስዕለትና አስተብቁዖት ማድረግ አለብን ።

እንግዲህ የጸሎትን ስልት ስንናገር የሚገባና የማይገባ ጸሎት የትኛው እንደሆነ ፤ ተገቢውም የጸሎት ስልትና ውጤት እንዴት እንደሆነ እንደሚቀጥለው እንገልጣለን ።

**፩. የግብዝ ጸሎት ፤** ግብዞች ሲጸልዩ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰው ቢያይላቸው ሰውም ቢሰማላቸው የበለጠ ይወዳሉ ፤ ስለዚህ ሁል ጊዜ

በሰው ፊት ለመጸለይ ጩኸውና አሰምተው ለመጸለይ ይፈቅዳሉ ። እንደዚህ ያሉት ሰዎች ጸሎተኞች ናቸው ተብለው ውዳሴ ከንቱ ይሰጣቸው እንደሆን እንጂ ከቶ ሌላ የሚያገኙት ጥቅም የላቸውም ። ውዳሴ ከንቱ የሚባለው ደግሞ ዋጋ የሌለው ከንቱ ምስጋና ማለት ነው ፤ ቀጥሎም ከሰው እንጂ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኙት አንዳችም ዋጋ የላቸውም ። ሰዎች ራሳቸው ኃላፊዎች ጠፊዎች ከንቱዎችም ሲሆኑ ከሰዎች የሚሰጣቸው ምስጋናም የከንቱ ከንቱ ይሆናል ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲሰማና እንዲያይ ማድረግ እንጂ በሰው ፊት የሚደረገው ሁሉ መቅረት አለበት ።

ክርስቶስ ይኸን አስከፊ የጸሎት መልክ በመንቀፍ ሲናገር ምሳሌ ያደረገው በየአደባባዩና በየምማዕዘኑ እየቆሙ ይጸልዩ የነበሩት ንፈሪሳውያንን በመጥቀስ ነው። እነዚህ ፈሪሳውያን ከማህበር ጸሎት እየገቡ ይጸልዩ ነበር ፤ ለምን ሲሏቸው የእግዚአብሔር ፍቅር አስገድዷቸው ከጸሎት ቤት ፣ ወይም ከራሳቸው ቤት ደርሰው የግል ጸሎታቸውን እስኪጸልዩ ጊዜ እንዳያልፍባቸው ጸሎቱም እንዳይቋረጥባቸው በማለት ነው ፣ ለሰው ይምሰል እንዲሁ ያስቡ ይመስላሉ እንጂ ፍሬ ነገሩ ግን ጸሎት አ።





ውታሪ ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋጋሪ መስሎ ለመታየት ፣ ከሰው ከንቱ ውዳሴን ለማግኘት ብቻ ነው ።

እኒህ ፈሪሳዊያን ፣ ጸሐፊዎችም ለሰው ይምሰል በዐደባባዩ ከመጸለያቸው ጋር ጸሎታቸውን ያስረዝሙ ፣ ጩኸው አሰምተውም ይጸልዩ ነበር ይኸም ሁኔታ አንዳንድ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ሰዎች ስሜት ለመማረክና ጸሎተኛ መስሎ ለመታየት ለመመስገንም ነበር ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ይኸን የመሰለውን ጸሎት በይፋ ተቃውሞ ነቅፎም ፣ በዚህም አጋጣሚ ሌላ አዲስ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ለአዲሱ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኀበር ሰጠ ።

ምንም በብሉይ ዘመን በዚህ መልክ የሚጸልዩ ነበሩ ብለን በታሪክ መልክ ብንናገርም ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህን ዓይነት ጸሎት ቢነቅፍም እስከ ጊዜያችን ድረስ ከላይ በገለጥነው ፣ ጌታም በነቀፈው መልክ የሚጸል እስከአሁን ይገኛሉ ።

## ፪ ፤ የግብዞች ጸሎቅ ዋጋ ፤

ከእግዚአብሔር ጸጋ ይልቅ ከሰው የሚገኘውን ከንቱ ውዳሴን በመፈለግ በሰው ፊት የሚጸ





ልዩ ሁሉ ጸሎታችውን ማስረዘም ፤ ጩኾና አሰምቶ በመጸለይም የሚኖሩ ሰዎች ዋጋቸው ከንቱ ውዳሴ ብቻ ነው ፤ ይኸውም ከሰው ብቻ የሚገባኝ ነው ለዚህም ማስረጃ ክርስቶስ እንዲህ ይላል «እውነት እነግራችዋለሁ ዋጋቸውን እንደወሰዱ» (ማቴ ፣ ፮ ፣ ፭ ፣ ) ።

የጸሎትም ትርጉሙ የሰውና የእግዚአብሔር ውይይት ግንኙነትም ሲሆን እነዚህ ግብዞች ግን ግንኙነታቸውም ከሰው ጋር ውይይታቸውም ከነፋስ ጋር በመሆኑ ዋጋ የላቸውም ።

## ፫ እውነተኛው ጸሎትና ዋጋው ፤

እውነተኛው ምእመን በማንኛውም ጊዜ ወደ ልዩ ልዩ ጸጥታ ክፍል ገብቶ በሩን ዘግቶ በስውር ወደሚያየው ሰማያዊ አባቱ ይጸልያል፤በስውር የሚያየው ሰማያዊ አባቱ ደግሞ ጸሎቱን ሰምቶ ተገዥነቱን አይቶዋጋውን በግልጥ ይሰጠዋል ።

የእውነተኛውን ጸሎት ዓይነት ፤ እውነተኛውን የጸሎት ስርዓት ራሱ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ተናገረ « አንተ ግን በጸለይክ ጊዜ ወደ ቤትህ ግባ ደጅህንም ዝጋ፤ ላባትህም በስውር ለሚያይህ ጸልይ፣ በስውር የሚያይህም አባት በግልጥ ይሰጥሀል ። (ማቴ ፣ ፮ ። ፮ ) ።





በግልጥ በጸጥታ ቦታ ፤ በስውርም ሊጸልይ የሚገባው የግል ጸሎት ሲሆን አንድ ሰው ብቻውን በሚጸልይበት ጊዜ ነው ፤ ይኸም የሚያስረዳው ክርስቶስ የተናገረው ቀዋሚ ቃል ነው ፤ ይኸውም « አንተስ በጸለይክ ጊዜ » እያለ በነጠላ ቁጥር በ፪ኛ ሰው አቅርቦ በመናገሩ ይታወቃል ።

እውነተኛው ምእመን በማኅበር ጸሎት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ፤ በቤተ ሰብእ ጸሎት ጊዜ ደግሞ ከቤተ ሰቡ ጋር በግልጥ መጸለይ ይገባዋል ፤ ይችላልም ፤ ግን የግል ጸሎቱን በሚያደርግበት ጊዜ ወደ ምኝታ ቤቱ ወይም ወደ ገለልተኛ ክፍል ገብቶ በሩን ዘግቶ ለፈጣሪው ብቻ እንዲታይ ሁኖ መጸለይ አለበት ። እንጂ በአደባባይ ሁኖ መታየት የለበትም ።

ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ስም የሚያስገኘው የምእመኑ አንድነት ስለሆነ ምእመኑ በኅብረት መጸለይ መዘመር ተገቢው ነው ፤ ግዴታውም ነው ፤ ይኸም ውዳሴ ከንቱ አይሆንም ፤ አንድ እምነት ፤ አንድ ሥርዓት ያለው ምእመን ሁሉ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሁኖ ሲጸልይ ውዳሴ ከንቱ አይሆንበትም ።

የወል አምላክ የሆነው ሰማያዊ አባታችንን በማኅበር ማመስገን ግዴታችን ነው ስለዚህ ነቢዩ

ዳዊት « እግዚአብሔርን በማኅበር አመስግኑት » ሲል ተናግሯል (መዝ ፡ ፷፰፡፳፮)

እግዚአብሔርን አባት ያደረገ ፤ የእርሱም ልጅ የሆነ ሁሉ ፤ አንድ አካል አንድ ነፍስ አለው ብለን እናምናለን ፤የአንድ የእግዚአብሔርም ቤተ ሰብ እንደመሆኑ በአንድ ቤተ ሰብእ መልክ ይጸለያል ።

በጣም ከሚያስፈልጉት ነገሮችና ከክርስቲያናዊ ግዴታዎች አንደኛውና የመጀመሪያው በማኅበር ጸሎት በተወሰነው ቦታ ተገኝቶ የእግዚአብሔርን ምስጋና በአንድነት ማቅረብ ነው ።

በግል ጸሎት ግን ብቸኝነት ፤ ቤትንም መዝጋት ያስፈልጋል ፤ ጸሎተኛ መሆኑ እንዳይታወቅ በት ያስፈልጋል ።

ቤቱን ዘግቶ በስውር ወደ ፈጣሪ ይጸለይ ስንል ሰውየው የሚሰወረው ከሰው እንጂ ስሙን የሚጠራው ሰማያዊ አባቱ ግን ሁል ጊዜ ያየዋል ጸሎቱንም ይሰማዋል ፤ እታዲያ በስውር የጠየቀውን እግዚአብሔር በግልጥ ያደርግለታል ።

የትም ሁኖ ቢጸለይ እግዚአብሔር በዓለሙ ሁሉ ሙሉ ስለሆነ ይሰማዋል ያየዋልም ፤ ስለዚህ የጠየቀውን ሁሉ ያደርግለታል ። ዮናስን ብንመለከት





ከፍተኛ ማስረጃ ይሆነናል ፤ በዓሳነባሪው ሆድ ሳለ የጮኸውን ጩኸት ሰምቶ ችግሩን ተመልክቶ ከዓሳነባሪ ሆድ ያወጣው እውነተኛ አምላክ ነውና ። እንዲሁም ነቢዩ ዳንኤልን እንመልከት ፤ ከአንበሳ አፍና ከአንበሳ ጉድጓድ ያወጣው እግዚአብሔር ነው ፤ሌሎችንም በዚህመልክ የረዳ አምላክ ነውና (ትንቢተ ዮሐንስ ምዕ፥ ፩—፪፤ዳንኤል ፮፡፲፮—፳፫)።

## ፬. እውነተኛ ጸሎት ፤

እውነተኛው ጸሎት ከእውነተኛው ሰማያዊ አባት ጋር በመንፈስ ለመገናኘት ለመወያየትም በእውነት መቅረብ ነው ። ይኸ ሰማያዊ አባት በእውነት እንደ ልጆቹ በሚመለከተን ጊዜ እኛ እንደ ባዕድ ሳንሆን እንደ እውነተኛ ልጆቹ ሁነን በንጹሕ ሕሊና ቀርበን እንደባለውለታነቱ ምስጋና፥ እንየድችግራችን ብዛት ደግሞ ልመና ማቅረብ ተገቢ ነው ። ይኸም በሚሆንበት ጊዜ ጸሎቱ ፤

፩፡ ትርጉም የለሽ ዝም ብሎ ዝብዘባ ብቻ እንዳይሆን ።።

፪፡ የሚመላለስ ቃልና የስሜት የማይሰጥ እንዳይሆን

፫፡ ጩኸና አሰምቶ ከመጸለይ መራቅ ፤

፬፡ ለሰው ይምሰል ለይዩኝና ለይስሙልኝ አለመጸለይ ።





እግዚአብሔር አምላክ እኛ የምንሰማበትን ጆሮ የፈጠረ አምላክ ነው ፤ ስለዚህ ቀስ ብለው ቢጸልዩ ይሰማል ፤ ደንቆሮ አምላክ አይደለምና ።

እንዲሁም የምናይበትን ዓይን የፈጠረ አምላክ በስውርም ብንጸልይ ያየናል ፤ እንደችግራችንም ይረዳናል ከቶ የሚሰወረው ነገር የለም ። እኛ የምናውቅበትን አእምሮ የፈጠረ አምላክ ስለሆነ ሁሉን ያውቃል ፤ ለእርሱ ተሰውሮት የሚቀር ነገር የለም ፤ እንዲያውም ለኛ የሚያሻውን ሁሉ እርሱ አውቆ ሳንጠይቀው አስቀድሞ ያደርግልናል ። እንግዲህ አብዝቶ ጩኾ መጸለይና ትርጉም የለሽ ቃልን እየመላለሱ መጸለይ በክርስቶስ ዘንድ የተጠላ ጸሎት ነው፤ይኸንም ተገንዝበን እንዲህ ካለው መራቅ የሁላችንም ግዴታ ነው ።

ይኸን የመሰለውን ጸሎት ክርስቶስ እንዲህ ሲል ይነቅፋል «በጸለያችሁም ጊዜ ነገር አታብዙ እንደ አሕዛብ ፤ በነገራቸው ብዛት የሚሰማቸው ይመስላቸዋልና አትምሰሏቸው ፤አባታችሁ የምትሹትን ያውቃልና እርሱን ሳትለምኑት—» (ማቴ፡፮፡፯—፰) ።

የነገር ብዛት ሰሚውን ያሰለቻል ፤ ተናጋሪውንም ከምን ተነስተን ከዚህ ደረስን እስኪል ያዘነጋልና ።





እንግዲህ እንኳን በንጉሠ ነገሥቱ በእግዚአብሔር ፊት በአንድ ትልቅ ሰው ፊት እንኳን ቁም የሆነውንና ያልሆነውን የተናገረ ሰው ነገርን አብዝቶ ድምፅን አሰምቶ የተናገረ እንደሆነ እንኳን ሊሰማ ቅጣትም ሊደርስበት ይችላል ።

ነቢዩ ዳዊት « የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው ፤ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም » ሲል እንደተናገረው ለጸሎት ስንነሣ ልቦናችንን ሰበር አድርገን ራሳችንን አዋርደን ለተመልካቹ አምላክ እንደሚገባ ሁነን መቅረብ አለብን (መዝ ፡፶ ፡ ፲፯) ።

እኛ ራሳችን ከባልንጀሮቻችን ጋር እንኳን በምንነጋገርበት ጊዜ ነገር የሚያበዛውን የሚዘበዝበውን እንታዘበዋለን በመስማትም ፈንታ እአምሮውን ትክክል እንዳልሆነ እንቆጥረዋለን ፤ እታዲያ ሁሉን ለሚሰማ ፤ ሁሉንም ለሚያውቅ ለእግዚአብሔር የልብ ጸሎት በለዘበ ድምፅ መቅረብ እንዴት አይገባ?

ሁኖም ጸሎትን ሳያቋርጡ ዕለትና ሰዓት ሳይወስኑ መጸለይ ተገቢ እንደሆነ በሌላ ቦታ ራሱ ክርስቶስ ተናግሯል ፤ ማለት በአመጸኛው ዳኛና በአቤት ባይዋ መበለት ምሳሌ ሰጥቶ ሲናገር እርሷ ሳታቋርጥ ከመለመኗ የተነሣ እንዳትዘበዝበው እንደፈረደላት

ምሳሌ አድርጎ ጸሎትም እንዲሁ ሳንሰለች ሳናቋርጥ መጸለይ እንደሚገባ ተናግሯል (ሉቃ፡ ፲፰ ፡፩—፯) ። እንዲሁም በሌላ ቦታ ራሱ ክርስቶስ ሌሊቱን ሁሉ በጸሎት ሳያቋርጥ እንዳሳለፈው እንዲህ ሲል ይናገራል «ሆነም በዚያች ወራት ወደ ተራራ ወጣ ይጸልይ ዘንድ በእግዚአብሔር ጸሎትም ተግቶ ነበር ሌሊቱን ሁሉ » (ሉቃ ፡፮፡፲፪) ። ሌላም ይህን የመሰለ ብዙ ይገኛል ፤ ሁኖም እንደሁናቴውና እንደጸሎቱ ዓይነት ሊሆን ይችላል ። በመሠረቱ ግን ጸሎት ብሎ ጸሎትም አድርጎ የሠራልን ፤ ያስተማረንም አቡነ ዘበሰማያትን ስለሆነ እርሱን እሱው በፈቀደው መልክ መጸለይ ተገቢ ነው ።

## ፰ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ ፤

የተሻለውና የተፈቀደው ጸሎት ይህ ስለሆነ ሁላችን ይህንን እንጸልይ ።

ክርስቶስ ይኽን ጸሎት ለሐዋርያት ሲያስተምር ቀደም ያሉ የተለያዩ ጸሎቶች ወይም የጸሎት ዓይነቶች ኑረው ከነዚያ ውስጥ በመምረጥ ይህ ይሻላልና ይኽንን ጸልዩ ብሎ ያስተማረው አይደለም ፣ ነገር ግን እርሱ እንደአምላክነቱ ተገቢነቱን አውቆ እውነተኛውን ጸሎት አቡነ ዘበሰማያትን አስተማረ እንጂ ፤ ይኽንም ጸሎት ሲያስተምር ፣





፩፡ ቋሚ ጸሎት ዘመን የማይሽረው አድርጎ ሁልጊዜም እርሱን እንድንጸልይ አዟል አስተምሯል።

፪፡ እውነተኛውን የጸሎት ምሳሌ ይኽን አቡን ዘበሰማያትን አድርጎ ስለአስተማረ ማንኛውም አማኒ በዚህ መልክ እንዲጸልይ የሚገባ መሆኑን ገልጦ አስተማረን ።

ከዚህም የተነሣ በግላችንም ፤ በቤት ሰብእም ፤ በማኅበርም ጸሎት ብንጸልይ ማንኛውም ነገድ በማንኛውም ልሳን ቢሆን በዚህ ጸሎት ምሳሌነት ሊጸልይ እንደሚገባ ቤተክርስቲያን ታስተምራለች ፤ ስለዚህ አቡነ ዘበሰማያት የወል ጸሎት ሊሆን ቻለ ፤ እርሱንም ጌታ ለሐዋርያት አስተማረ ፤ ሐዋርያትም ለተተኪዎቻቸው አስተማሩ ፤ ሲወርድ ሲዋረድ እነሆ እስከኛ ሊደርስ ቻለ፤አሁንም ቤተ ክርስቲያን ለሁሉ ታስተምራለች ።

ጌታም ራሱ ይኽንን ጸሎት በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደጸለየው ይነገራል ፤ ለምሳሌ ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቶ የመጨረሻውን እራት ለደቀመዛሙርቱ አብልቶ ምስጢረ ቁርባኑን በመሠረተ ጊዜ ጸሎት እንደጸለየ ፤ መዝሙርም እንደዘመረ የታወቀ ነውና (ማቴ፡፳፮ ፡ ፴ ፤ማር፡፲፬፡ ፳፮ ፤)





በዚያንም ጊዜ እርሱ የጸለየው ጸሎት ይኸው አቡነ ዘበሰማያት እንደሆነ በብዙ ሊቃውንት ዘንድ ይነገራል፤ ምክንያቱም ይኽን አቡነ ዘበሰማያትን ለምሥጢረ ቍርባን ማከበሪያ መባረኪያ አድርጎ ሠርቶታልና ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አቡነ ዘበሰማያት የሚለው ጸሎት በየቤተክርስቲያኑ በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ ከፍ ያለውን ክፍል ይዞ ሲዘመር ሲጸለይ ይገኛል ።

ቅዱሳን ሐዋርያትም ከሰማያዊ አባት ጋር የሚያገናኘውን ይኽን ጸሎት አዘውትረው ይጸልዩት ለተከታዮቻቸውም ለጊዜው በቃል ፤ ቆይቶ ግን በጽሑፍ ሰጥተዋል ።

በመጀመሪያ የክርስትና ዘመን ማንኛውም አዲስ አማኒ ክርስቲያናዊ እምነቱን አሟልቶ እንደተጠመቀ ወዲያውኑ ጮኾ አሰምቶ የሚናገረው ቃል « አቡነ ዘበሰማያት» የሚለውን ጸሎት ነበር፤ ምክንያቱም በጥምቀተ ክርስትና ከእግዚአብሔር መወለዱን አምኖ ሰማያዊ አባቱን በደስታ ድምፅ መጥራቱን ያጠይቃልና ።

ይኽ አዲስ አማኒ ከአረማዊ ግብር ፣ ከአረማዊም ሕይወት ወጥቶ ወደ መንፈሳዊ ዓለም ለመግባቱ ፤ የእግዚአብሔር ልጅም ለመሆኑ ምስክርነትን መስጠቱ ነውና ።





በዚህም መሠረት በየ ቤተክርስቲያኑ በጠዋትና በማታ ጸሎት ጊዜ ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶት ሁሉም የእግዚአብሔር ልጅነቱን እርስ በእርስ ደግሞ ወንድማማችነቱን እኅትማማችነቱን በመግለጥ ይጸልየዋል

ይኽን ጸሎት ሁሉም ከሕፃንነት ዕድሜ ጀምሮ ክርስቲያን የሆነው ሁሉ የአፉ መክፈቻ የመላሱ መፍቻ የንግግሩ መጀመሪያ በማድረግ ያጠናዋል እንዲሁም ጌታና አሽከር ፤ እመቤትና ገረድ ፤ ደሀ ባለጸጋ ፤ ወንድና ሴት ሳይል ሁሉም እንዲጸልየው የታዘዘ ጸሎት ነው ።

ይኽ አቡነ ዘበሰማያት የተባለው ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎት መልክ ያስተማረው እንጂ የጸሎትም ፤ የተአምኖትም የትምህርት ክርስትናንም መልክ የያዘ ነው ። ስለዚህም እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በነዚህ በ፫ቱ አርእስት መሠረት ይጠቀምበታል ።

የጸሎቱን መልክ የተመለከትን እንደሆነ በግል ጸሎት ፤ በቤተሰብእ ጸሎት ፤ በማኅበር ጸሎት ሲጸለይ መነሻውና ማሳረጊያው ይኸው የጌታ ጸሎት ነው ። በተለይ በጸሎተ ቅዳሴው ጊዜ ከላይ እንደ ተናገርነው በየቤተክርስቲያኑ የተለየ ቦታ ተሰጥቶት ከሚያስፈልጉት ጸሎቶች ውስጥ አቡነ ዘበሰማ

ያት ፭ኛው ሁኖ ሲዘመር ሲጸለይ ይገኛል ።

በተአእምኖትም መልክ የተመለከትን እንደሆን የአምላክን ሕልውና የሚገልጥ አምጻኤ ዓለማትነ ቱን ፈጣሪ ፍጥረታትነቱን መግቦቱን የሚገልጽ የሚያስረዳም ትምህርት ሁኖ ይገኛል ።

በትምህርተ ክርስትናው በኩል የተመለከትን እንደሆነ ከሕፃንነት ዕድሜ ጀምሮ ማንኛውም ሰው የሚጸልየው የሚዘምረው ስለሆነ ከወላጅ አባቱ ጋር በማነፃፀር ሰማያዊ አባቱን እንዲያውቅ የሚ ረዳ ትምህርትሁኖ ይገኛል ።

እያንዳንዱ ቤተክርስቲያንም በነዚህ ፫ት አር እስት መልክ ይጠቀምበታል ፤ ስለዚህ ከ፩ሺህ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች አቡነ ዘበሰማያትን ተተር ጉም ሲጸለይ ሲነበብ ሲተረጐም ይገኛል ።

የእኛ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ በነዚህ ፫ ዓላማዎች መሠረት ትጠቀምበታለች ፤ በተለይ በጸሎት መልክ ስንመለከተው በገዳም የሚገኙ መነኮሳትና በተለ ያዩ ቦታዎች የሚገኙ መናኒያን በ፯ቱ ሰዓት ሁሉ አቡነ ዘበሰማያትን ይደግማሉ እንዲያውም በ፩ ሰዓት ፲፪ ጊዜ ይጸልዩታል ፤ እንግዲህ ፯ ጊዜ ፲፪





ቿ፹፬ ይሆናል ፤ ይህን ያህል ጊዜ ይጸልዩታል ማለት ነው ፤

ይኸም የግሉን ብቻ እንጂ የማኅበሩን ጸሎትሳይጨ ምር የሚጸለይ ነው ። በዚህም መልክ ከሰብአ ዓለም ቢሆንም አልፈው አልፈው የሚጸልዩ ይገኛሉ ።

በትምህርተ ክርስትናውም በኩል ከፍ ያለ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ትምህርት ነው ፤ ምንም የፊደልን መልክ የማያውቀው ምእመን ሁሉ አቡነ ዘበሰማያትን የማያውቅ እርሱንም የማይጸልይ የለምና ።

ካህናቱም የጸሎቱ ሁሉ መክፈቻ የጸሎቱም ሁሉ መደምደሚያ አድርገው አቡነ ዘበሰማያትን ስለሚመለከቱት በቤተ ክርስቲያናችን ተወዳጅነ ትና ተቀባይነት ያለው ጸሎት ፤ ትምህርት ሁኖ ይገኛል። ይህን ሁሉ ስንመለከት አቡነ ዘበሰማያት ሁሉን የያዘ የወንጌል አስተዋጽኦ እንደሆነ ያመለ ክታል ። አሁንም ይህን የመሰለ ዓላማ ያለው ሁሉንም አጠቃሎ በአንድ መልክ ይዞ የቀረበውን ጸሎት ስንጸልይ አፋችንን ከልባችን ልባችንንም ከአፋችን አንድ አድርገን ምስጢሩን ተረድተን ዓላማውን አውቀን መጸለይ አለብን ።





ይኸም ጸሎት አጭር መስሎ ይታያል እንጂ ይኸን እንኳን በአንድ ልብ ሁኖ መጸለይ በጣም አስቸጋሪ ነው ። እንግዲያውስ ልቡናውን ሳይሰበ ስብ ስሜትም ሳይኖረው እንዲሁ የሚጸልየው ሁሉ ከመንፈስ የተራቆተ ነው ። ምንም ከእግዚአብሔ የሚያገኘው ዋጋ የለውም ለማለት ይቻላል ።

ታላቁ ንጉሥ አፄ ቴዎድሮስ መነኮሳትን የሚወዱ አብሮም መወያየት የለመዱ ነበሩ ፤ ከዕ ለታት አንድ ቀን ብዙ መየኮሳት ከተሰበሰቡበት መካከል እርሳቸው ምክር አዘል ትምህርት ሲሰጡ «እናንተ አባቶች ከዚህ ዓለም ግብር የራቃችሁ ፤ ወደ ሰማያዊው አባታችን የቀረባችሁ ናችሁ ፤ የም ናከብራችሁም የምንፈራችሁም ከዚሁ የተነሳ ነው፤ ነገር ግን ሰይጣን እየተፈታተናችሁ ከእኛ ከአለማ ውያን ያልተሻላችሁ ናችሁ ጸሎት በምትጸልዩበት ጊዜ ልቦናችሁን ስታባክኑ አእምሮዋችሁንም ስት በትኑ ትገኛላችሁ ፤ ይኸም ከሆነ አንድ ሰው ሌላ ውን የተለያየውን ጸሎት አብዝቶ ሊጸልይ ፤ ቀኑ ንም ሌሊቱንም ሁሉ ሊጸልይ ይቅርና አጭር ጸሎት የተባለውን ይኸን አቡነ ዘበሰማያትን እን ኳን በአንድ ልብ ሁኖ ሊጸልይ አይችልም ? አሁን ከእናንተ ከአባቶች ውስጥ ሌላ ነገር ሳያስብ





ልቦናውንም ሳይበትን በአንድ ልብ ሁኖ «አቡነ ዘበሰማያትን» የሚደግም ይገኛልን ቢኖር ግን በቅሎየን እሰጠዋለሁ ሲሉ ተናገሩ »አንድ ሰው ከዚያ በፊት በምን መልክ እንደሚጸልይ ራሱንም ተቆጣጥሮ የማያውቅ ሁል ጊዜ ሲጸልይ በትክክል በ፩ ልብ ብቻ የሚጸልይ መስሎት ቸኩሎ እኔ አለሁ ፤ እኔ ሌላ ነገር ሳላስብ አቡነ ዘበሰማያትን እጸልያለሁ ሲል መለሰ ።

ንጉሡም በል ጀምርና ጸልይ አሉት «አቡነ ዘበ ሰማያት ---በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር» ሲል አቁም በቃህ አሉት ። እርሱም አፋመና ምነው ምን አጠፋሁ አላቸው ፤ እርሳቸውም በል አሁን ሦስት ዐረፍተ ነገር ብቻ ነው የጸለይከው በዚህ ቅጽበት ውስጥ ምንም ሌላ ትርፍ ነገር አላሰብክምን? አላሰብኩም የምትል ከሆንክ ግን ቴዎድሮስ ይሙት በለኝ አሉት ። ሰውየው እውነ ተኛ ኑሮ አረ ይቅርታ ጃንሆይ ሌላ ነገር አስቤአ ለሁ፤ይኸውም በቁሎዎን የሚሰጡኝ ሌጣዋን ይሆን ወይስ ከነኮርቻዋ ብየ አስቤአለሁ አላቸው።

እንግዲህ ሁላችን በዚህ መልክ እንገኛለን ማለት ? ነው አብዝተንማ ስንጸልይ እንዴት ልን ሆን ነው። በአቡነ ዘበሰማያት በአጭር ጸሎት ጊዜ እንዲህ የምንሆን ።

አቡነ ዘበሰማያት እኮ አጭር ጸሎት ይምሰል እንጂ ምሥጢሩ የረቀቀ ፤ ትንተ ናው የበዛ ከመሆኑም በላይ ጌታ ያዘዘው ጸሎት በመሆኑ ከፍተኛ ክብደት ያለው ጸሎት ነው ፤ ስለዚህ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን በጸጥታ በጽሞና ሁነን ልቦናችንም ሰብስበን መጸለይ አለብን በፍ ርሃትና በአክብሮትም ሁነን መጸለይ አለብን ፤ እንኳን ሌላ ነገር ልናስብበት የአቡነ ዘበሰማያት ምሥጢሩ የረቀቀ ፤ ትንተናው የበዛ ከመሆኑ የተነሣ ሌላ ሐሳብን ልንጨምርበት አይገባንም ፤

በአቡነ ዘበሰማያት ላይ እንኳን ሌላ ነገር ልናስገባበት የእርሱንም ምስጢር እንኳን በመላ ልንረዳው አንችልም እታዲያ እንዴት ሌላ ትርፍ ነገር ልናስገባ እንችላለን ? እንግዲያውስ ጌታ እርሱ የፈቀደው እርሱ ያስተማረው እንደመሆኑ እንደርሱ ፈቃድ መጸለይ አለብን ።

ይኸን ጸሎት አንድ ሰው ሲጸልይ ከምድራዊ ዓለም ወጥቶ በሰማያዊ ዓለም እንዳለ ከሥጋዊ ልጅነት ወጥቶ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምኖ እንዲጸልይ ያስፈልጋል ። ጠቅላላ ትርጉሙን ለመ ረዳት ወደ ሚቀጥለው ክፍል እንግባ ፤ እርሱንም በነቃ መንፈስ እንመርምረው ፤ እንረዳውም ።





# ክፍል ፩ የጌታ ጸሎት

## ንዑስ ክፍል ፩ ምስጋና ፤

፩፡ ሰማያዊ አባታችን—

«አቡነ ዘበሰማያት ይትቀድስ ስምከ» (ማቴ፡ ፮፡፱ ) ።

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ ፤

ይህም የመጀመሪያ ክፍል የምስጋና ክፍል ፤ የተባለው ነው፤ « ስምህ ይቀደስ » ይሳልና ።

ሀ፡ የአባትን ስም መጥራት ፤ ሰማያዊ ፈጣሪና ምድራዊ ፍጡር የሚያደርጉት ውይይት በዚህ ቃል «አቡነ ዘበሰማያት » በማለት ይጀምራል ። በአቡነ ዘበሰማያት ውስጥ የሚገኙ ቃላት እያንዳንዳ ቸው ልብን የሚነኩ ምሥጢራትን ያዘሉ ሲሆኑ፤ እያንዳንዱን ቃል በዝርዝር በየቦታው እንናገረ ዋለን ።

ዕብራዊያን የእግዚአቡሔር ቤተሰብእ የእግዚ አብሔርም ወገን እየተባሉ ይጠራሉ እነርሱ ስለ እውነተኛው አምላክ ይወቁና ይመስክሩ እንጂ ከእ ርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሆነ አያው ቁም፤ ስለዚህ አይቀርቡትም ነበር ፤ ማለት አምላ ክን ሲጠሩት ኢሎሂም ፤ ይሆባ ፤ አዶናይ በሚል





ዘይክል ኩሎ ፤ አምላከ ኃያላን ፤ .................. የሚል ገናንነቱን ኃያልነቱን ብቻ የሚገልጥ እንጂ የፍቅር አምላክ ወይም ራሱ ፍቅር መሆኑን አያውቁም ነበር ። እግዚአብሔር አባት ስለሆነ ልጆቹን ይወዳል ፤ ስለዚህ ልጆቹ ያለፍርሃት አባት ብለው ስሙን ይጠራሉ ፤ ያለፍርሃትም ወደ እርሱ ይቀ ርባሉ ።

እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ያየው ያወቀውም ከቶ አልነበረም ፤ ከአንድያ ልጁ በቀር ፤ እርሱ ግን የሚያውቀውን ያየውን ለኛ ለክርስቲ ያኖች ነገረን (ዮሐ፡፩፡፲፩)። መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን ሆይ በሚለው ጸሎት የብሉዩን ዘመን የብሉዩንም አስተሳሰብ አተመው ዘጋው ፤ አዲሱን ቃል ኪዳን ከፈተ ፤ አዲስ የተስፋ ቃል ለሰው ሁሉ አሰማ ።

በዚህ የተስፋ ቃል የፀሐይ ጨረር ሁሉን እን ዲሞላ የተስፋው ብርሃን የተስፋውም ጨረር የሰ ውን ልቦና ሁሉ ሞላው ፤ ሁሉም እግዚአብሔር አባቱ እንደሆነ አወቀው ተረዳው ።

በእግዚአብሔር ላይ ያለውን የአባትነ ቱን ፍቅር ሰው ሁሉ ተረዳ ፤ ፍርሃቱን ሁሉ አስወ ገደ ፤ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥነቱ ሥልጣኑንለማ





ሳየት ጣል በግድ እሰር በግንድ የማይል ወይም እ ንደ ቅኝ ገዥ የሚያስፈራራና የሚያስጨንቅ ሳይ ሆን አንድ አባት ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ ልጆቹን በሥነ ሥርዓት እንደሚያሳድግ እንደሚያስተዳድር እንደሚመራም ይኸን ዓለም በፍጹም ጥበቡ በፍ ጹም ፍቅሩ ያስተዳድራል ፤ ይመራል እንጂ የቁጣ ውን የበቀሉን ሥራ እንደችሎታው መጠን አያደ ርገውም ።

እግዚአብሔር ብዙ የክብር ስሞች ሲኖሩት ከሰው ጋር ከሚያደርገው ግንኙነት የተነሣ አባት የሚለውን ቃል መርጠ በእርሱ እንድንጠራው ፈቀ ደልን ፤ይኸም ፍጹም ፍቅሩን ያሳያል ፤ ወደ እር ሱም እንድንቀርብ ያደርገናል ።

የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም ነው ፤ በዚህ ዓለም ፍጹም ፍቅር አላቸው የሚባሉ በእርግ ጥም ሊኖራቸው የሚገቡ በመጀመሪያ ደረጃ ባልና ሚስት ናቸው ፤ ነገር ግን ከመዋልና ከማደራቸው የተነሣ ፍቅራቸው ያልቅና ይሰለቻቻሉ ስለዚህም ሲቀናኑና ሲካሰሱ ለጥል ሲዘጋጁ ይገኛሉ ። እንዲ ሁም በ፪ኛ ደረጃ የአንድ አባትና እናት ልጆች ፍቅር ከፍ ያለ ነው ፤ በጣም ይዋደዳሉ ይተሳሰባሉ ነገር ግን በሀብት በንብረት ይጣሉና ለግድያ ሳይ

ቀር ይፈላለጋሉ ። ሌሎችም ባልንጀሮች አብሮ አደ ጐች የሆኑ ልባዊ ፍቅር ይኖራቸዋል ፤ ግን በልዩ ልዩ ጥቅም ይለያያሉ፣ እንዲያውም አንደኛው የሌላውን ሕይወት እስከ ማጥፋት ይደርሳል ፤ እንግዲህ ፍጹም ፍቅር አላቸው የምንላቸው ወገኖች፤ ሁሉ በዚህ መልክ ይኖራሉ ፤ በዚህም መልክ ይለያያሉ ።

እውነተኛውና ዘላቂው ፍቅር ግን አባት በልጆቹ ላይ የሚያሳየው ነው ፤ይኸም ዓይነቱ ፍቅር ከምንም ጥቅም ጋር ያልተያያዘ ነው ፤ ስለዚህም አባት በልጁ ላይ የሚያሳየው ፍቅር ፍጹምና ዘላቂ ፍቅር ነው ። እንግዲያውስ አባት ለልጁ መሥዋዕት እስከመሆን ሕይወቱንም እስከመለወጥ ድርሶ ልጁን ይወዳል ፤ አባት ለማንም የማያደርገውን ሁሉ ለልጁ ያደርጋል ምክንያቱም ልጁ ነውና ፤ ሥጋውም ነውና ከባሕርዩም የተከፈለ ነውና ። አባት በሌላ ነገር ሁሉ ከሚደሰተው ይልቅ በልጁ እርምጃ የበለጠ ይደሰታል ፤ ግን ልጁ እርሱን መስሎ እንዲሄድ ይወዳል ፤ ስለዚህም አባት ለልጁ የተለያየ መመሪያ በየጊዜው ይሰጣል ።

እንዲሁም ታላቁ አምላካችን ሰማያዊውም አባታችን ከምድራዊው አባታችን የበለጠ ነው ፤





ለሰው ሁሉ የሚያደርገውን የማይቆጠር በንግግርም የማይገለጥ ብዙ ውለታ ነው ።

አባታችን እግዚአብሔር እኛን ሰዎችን ይወደናል፣ ፍቅሩም ፍጹም ነው ፤ የፍቅሩም ምልክት ስለኛ ድኅነት ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁን ለሕማም ለሞት አሳልፎ በመስጠቱ ይታወቃል (ዮሐ፡ ፫፡፲፮ )። ይኸም ሁናቴ ፍጹም የአባትነት ፍቅር መግለጫ ነው፣ ማለት ልጁን ለሞት አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ የፍቅር መግለጫ የለምና (ዮሐ፡ ፲፭ ፡፲፫)

እንግዲህ የአባታችን የእግዚአብሔር ፍቅር በኛ ላይ ያለው በዚህ መልክ ሲገለጥ ይህን ያህል ፍጹም ሲሆን እኛ ልጆቹስ በአባታችን በእግዚአብሔር ላይ እንዴምን ያለ ፍቅር አለን? መጠኑስ ምን ያህል ፤ነው? በምንስ ፥ እንዴትስ ሊገለጥ ይችላል !

የልጅ ፍቅርም በአባቱ ላይ ያለው አባት በልጁ ላይ እንዳለው መሆን አለበት ማለት የአባት ፍቅር ፍጹም እንደሆነ የልጅም ፍቅር ፍጹም መሆን አለበት ፥ ይኸንም ልጆቹን በፍጹም ፍቅር በሚወድ አባትና በተመሳሳዩ መልክ ልጆቹም በሚወዱት ቤተሰብእ መስለን እንናገራለን።

አንድ ቤተሰብ አሳዳሪ ፫ልጆች የነበሩት ፍቅ





ሩም ፍጹም የሆነ አባት ነበር ፥ የልጆቹን ፍቅር የያንዳንዳቸውን በተናጠል መጠኑንና ልኩን ለማወቅ ፈለገና ልጆቹን ተራ በተራ ምን ያህል እንደሚወዱት ጠየቃቸው ።

በመጀመሪያ ታላቁን ልጁን ልጄ እንደምትወደኝ አውቃለሁ፤ ነገር ግን ምን ያህል ትወደኛለህ? መጠኑስ ምን ያህል ይሆናል ሲል ጠየቀው ። ልጅየውም ሲመልስ አባቴ ሆይ ! እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ መጠኑ ስፋቱ ክብደቱ ወይም ጥልቀቱ ግን እንደ ዐባይ ወንዝ ነው ። ይኸም የዐባይ ወንዝ በዓለም ከሚገኙት ወንዞች በትልቅነቱ ፩ኛ እንደሆነ እኔም በአባቴ ላይ ያለው ፍቅር ታላቅ ነው ፤ ፩ኛም ነው። የዐባይ ወንዝ መነሻና መድረሻ ሩቅ ነው ፤ ምጡቅም ነው። እንዲሁም የዐባይ ወንዝ ሰፊ ጥልቅም እንደመሆኑ እኔም በአባቴ ላይ ያለኝ ፍቅር ሰፊ ነው ፥ ጥልቅም ነው አይለካም አይመጠንም ሲል አስረዳ።

፪ኛ. ልጁን ደግሞ እንደዚሁ ሲል ጠየቀው እርሱም አባቴ እወድሃለሁ ፥ የፍቅሬም መጠን እንደ ራስዳሽን ተራራ ነው፣ ይህ የራስ ዳሽን ተራራ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ተራራዎች ውስጥ ፩ኛ እንደመሆኑ እኔም በአባቴ ላይ ያለኝ ፍቅር ፩ኛ ነው፣





ማንንም በዚህ አላስተካክልም ። የራስ ዳሽን ተራራ ትልቅ እንደመሆኑ ማንም ሊወጣው እንደማይችል የኔም ፍቅር በአባቴ ላይ ያለው እንዲሁ ከፍተኛ ነው ማንም ሊደርስበት አይችልም የራስ ዳሽን ተራራ ሰፊ እንደመሆኑ እኔም በሰፊ ልቡና አባቴን እወዳለሁ አለ ።

አሁንም ፫ኛ ልጁን አባት እንደ ሁለቱም ያለ ጥያቄ ጠየቀው፣ ይኸም ልጅ በዕድሜ ትንሽ ይሁን እንጂ በአእምሮ የላቀ በመሆኑ ከሁሉም የበለጠ ሁሉንም የሚያጠቃልል መልስ ሰጠ ።

ልጄ እንደምትወደኝ አውቃለሁ የፍቅርህ መጠኑ ፥ ክብደቱ፣ ስፋቱና ጥልቀቱ የቱን ያህል ነው? እንዴትስ በምንስ መልክ ልትደገልጥልኝ ትችላለህ ሲል ጠየቀው ። ልጅየውም አባብዬ እኔ የምወድህ አንተ የምትወደኝን ያህል ነው! ሲል የማያዳግም መልስ መለሰለት ። በእርግጥም የአባት ፍቅር በልጅ ላይ አይለካም ፥ አይመጠንም፣ እንግዲያውስ ልጁም ትክክለኛ ነው አባቱ የሚወደውን ያህል ከወደደው ፍጹም ፍቅር በአባቱ ላይ አለው ማለት ነው ።

እግዚአብሔር ሊገለጥ ሊተረጐም በማይቻል ፍጹም ፍቅሩ እኛን ይወደናል ፥ ስለዚህም ልጆቹ

አድርጎናል ፤ እንግዲህ እኛስ ምን ያህል እንወደዋ
ለን? ፍቅራችንንስ እንዴት በምን እንገልጠዋለን ?

እንደ እውነቱ ከሆነ የእግዚአብሔር የአባታ
ችን ፍቅር በኛ ላይ ያለው ፍጹም እንደሆነ የእ
ኛም በእግዚአብሔር በአባታችን ላይ ያለው ፍቅር
ፍጹም መሆን አለበት፣ ከትእዛዛቱም ውስጥ ፩ኛውና
ዋናው « ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም
ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ ታላቂቱና
ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይቺ ናት። » ሁለተኛይቱም
ይቺን ትመስላለች እርስዋም ባልንጀራህን እን
ደነፍስህ ውደድ የምትለው ናት» (ማቴ፡ ፳፪፡ ፴፫
—፴፱) ።

በዚህ መልክ እግዚአብሔር አባታችንን ልን
ወድ ልናከብረው ይገባናል ፤ ከወደድነውም ሕጉን
እናከብር ትእዛዙንም እንጠብቅ (ዮሐ፣ ፲፬.፲፭—
፳፫) ።

ከላይ የተገለጠው ምድራዊ አባት በልጁ ላይ
ስላለው ፍቅር ውለታም ተናግረናል፣ በዚህም አን
ፃር በሰማያዊ አባታችን ዘንድ ዕጥፍ የሆነ ፍቅ
ርና ውለታ ይደረግልናል ፤ አባታችንም የምንለው
ለከንቱ አይደለም ፤እንዲሁ ስም ብቻ ለመስጠት
አይደለም ፤ አባታዊ ፍቅሩ ርኅራኄው ከአባት የበ
ለጠ በመሆኑ ነው ።





በምሕረቱ በጸጋው የወለደን እውነተኛው
አባታችን ያውም ሰማያዊ አባታችን እግዚአብሔር
ነው፣ ስለዚህ የልጅ ፍቅር ያለው ፣ ልጆቹን የሚ
መግብ ፤የሚጠብቅ እንደለጋስነቱም ሁሉን የሚ
ሰጥ አባታችን ነው ።

እንዴትም ልጆቹ እንደሆን እንዴትም እንደ
ወለደን ቅ.መጽሐፍ ትውልዳችንን እንዲህ ሲል ያስ
ረዳናል ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብ
ሔር ልጅ የዓለሙም መድኃኒት መሆኑን ያመኑ ሁሉ
ይጠመቃሉ ፣ በዚህን ጊዜ ሁለተኛ ይወለዳሉ ፣
ይህ የሁለተኛ ጊዜ ልደት ከመንፈስ ስለሆነ የእግ
ዚአብሔር ልጆች ያደርጋቸዋል ።ስለዚህም የእግ
ዚአብሔር ልጆች ይባላሉ « ለተቀበሉት ሁሉ ግን
ሥልጣንን ሰጣቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ
ዘንድ በስሙ የሚያምኑ » (ዮሐ ፣ ፩ . ፲፪) ። ይህም
ቃል አማናዊ በመሆኑ ቅ.ጳውሎስ ምስክርነቱን
በማጽናት እንዲህ ይላል «እናንት ሁላችሁ የእግ
ዚአብሔር ልጆች ናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማ
ኖት » (ገላት ፫ . ፳፮) ።

እግዚአብሔር አምላክ ከፍጹም ፍቅሩ የተ
ነሣ እኛን ሰዎችን ልጆቹ አደረገን ይህንም ወንጌ
ላዊ ዮሐንስ ሲገልጥ «እዩ እንዴት ያለውን ፍቅር





ሰጠን አብ የእግዚአብሔር ልጆች እንባል ዘንድ
- - - - ( ፩ዮሐ፣ ፫፣፩) ።

በምድር ላይ ያሉትን ወላጅ አባት ፣ የቀ
ለም አባት ፣ የሃይምኖት አባት ፣ ሌላም የልዩ ልዩ
አገልግሎት ኃላፊዎች የሆኑትን ሁሉ አባቶችቻን
እንላቸው ነበር ፣ በእግዚአብሔር አንፃር ግን እነ
ዚህ ሁሉ አባቶች አይደሉም ራሳቸው አላፊዎች
ጠፊዎች ናቸው ። እውነተኛው አባታችን ያውም
ዘለዓለማዊውና ሰማያዊ አባታችን ግን እግዚአብ
ሔር ነው ፤ ይኸንም ክርስቶስ ሲያጸድቀው « በም
ድር ላይም አባት ብላችሁ አትጥሩ ፣ አባታችሁ
አንድ ነውና እርሱም በሰማይ አለ» ብሏል (ማቴ፡
፳፫ . ፱) ።

እንግዲህ በእግዚአብሔር በኩል ያለው አባ
ትነት እነዚህን በመሳሰሉ ማስረጃዎች የተረጋገጠ
ነው፤ ነገር ግን የእኛ እምነት ፣ የእኛ ምግባር ለል
ጅነት ሳያበቃን የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ የራሳችን
መሆኑን እንረዳው፤ ስለዚህ ለልጅነታችን መታወ
ቃያ የሚሆነውን ሁሉ በሥራ እንግለጠው በአ
ንደበታችንም ምስክርነታችን እንስጥበትን ።

እግዚአብሔርን አባት ብለን ፤ አባትም አድ
ርገን የምንጸልየው ጸሎት ፤ ልጅነታችንን የምን





ገልጥበት ፤ የምናረጋግጥበት ምልክት ነው ። ይኸ
ንም ጸሎት በጸለይን ጊዜ አእምሮአችንን ወደላይ
ያነሣዋል፤ ወደሰማይም ከፍ ከፍ ያደርገዋል ፣ የእ
ግዚአብሔርንም አባትነት ወደማወቅ ያደርሰዋል፣
እንዲሁም በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን
ትውክልታችንን ያጸናዋል ። እግዚአብሔርን አባ
ታችን ስንል አባታችንም ስናደርግ የለመነውን
ሁሉ የተመኘነውን ሁሉ እንደምናገኝ የኃጢአታ
ችንን ይቅርታ እንደምናገኝ ፣ ጽድቅን ፣ ቅድስናን
መዳንን፣ ልጅነትን እንደምናገኝ ሙሉ ተስፋ አድ
ርገን ነው፣ ምክንያቱም አምላክ በከንቱ ልጆቼ
አላለንም ልጆቹም አላደረገንምና ።

በዓለም ሙሉ የሆነውን ፣ ሁሉን የሚያውቀ
ውን ታላቁን አምላክ አባት ማለት አባትም አድ
ርጎ መጥራት የፍጹምነት ምልክት ነው ፤ ስለዚህ
በፍጹምነት ወደርሱ ደርሰን ግዳጃችን ሁሉ እንዲ
ወገድልን ሁነን መቅረብ አለብን ።

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስንል
እግዚአብሔር ሩቅ እንደሆነ በሰማይም ብቻ እንደ
ሚኖር መገመት የለብንም እኛ እራሳችን ወደ እርሱ
እንቀርባለን ፤ ወደ ሰማይ እንመሰጣለን ፣ ሰማያው
ያን እንሆናለን ፣ ከሰማያዊ አባታችን ጋር አንድ
እንሆናለን እንጂ ።

**ለ. የአባት ትርጉም** ፤ እያንዳንዱ ሰው ወደ ዚህ ዓለም ለመምጣት ምክንያት የሆነው አንዳንድ ምድራዊ አባት አለው ፡ ከእርሱም የነሣው ሰብአዊ አካልና ባሕርይ ሕይዎትም አለው ። እንግዲህ በዚህ መልክ አባት የሚለው ቃል የልጅ አስገኝ ፡ ወይም ወላጅ መሆኑን በትክክል ያመለክታል። ልጅ ማለትም ከአንድ የሆነ አባት መወለድን ያሳያል፤ ማለት አባት ካልን ልጅን ፡ ልጅም ካልን አባትን በግድ ያመጣል፡መሆንም ግድ አለበትና ።

በዚህ መልክ እንግዲህ እግዚአብሔር አምላካችንን አባታችን ስንል እኛን በልጅነት እርሱን ደግሞ በአባትነት የሚያገናኝ ቃል እንደሆነ ይታያል፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አባታችን ይሆን ዘንድ አባታችንም እንሰው ዘንድ እንዴት ወለደን ? እኛስ ፍጡራን ስንሆን እንዴት ልጆቹ ልንሆን ፡ ልጆቹም ልንባል ቻልን? የሚል ጥያቄን ያመጣል የዚህም ጥያቄ መልስ በጣም ከባድ ነው፡ ፍጡር ደፍሮ ፈጣሪውን አባት ብሏልና፡ ፈጣሪ እግዚአብሔርም ምንም ቸርነት ልማዱ ሁኖ እኛን ፍጡራንን ልጆቹ ሲለን ልጆቹም ሲያደርገን ይገኛል ይህንን ሲመለከቱት መልሱ ከባድ ነው ፤ ሁኖም እግዚአብሔር አምላክ ምስጋና ይግባውና በጸጋው





ወለደን ፤ስለዚህም ልጆቹ አደረገን ፡ ልጆቹም ተባልን፡ ስለዚህ አሁን በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች ነን ። እግዚአብሔር አምላክም አባታችን ነው ስለዚህም « አባታችን ሆይ !በሰማይ የምትኖር » እያልን ደፍረን ልንጠራው ፡ ልናመሰግነው፡ ልንለምነውም እንችላለን ።

ይኸም ከእግዚአብሔር ጋር ያለው የአባትነትና የልጅነት መብት የተገኘው በ፩ በተወሰነ ነገር ነው ፡ ይኸውም ከውኃና ከመንፈስ በመወለድ ብቻ ነው (ዮሐ፡ ፫፡ ፭ )።

ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ እንደሆነ አምነን በአብ ፡ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በመጠመቃችን ፡ ጥምቀቱንም በሜሮን ማኅተምነት በማረጋገጣችን ከእግዚአብሔር መወለዳችን ፡ የእግዚአብሔርም ልጅነታችን ይታወቃል ይመሰከራልም ። ስለዚህ በጥምቀት ክርስትና ከእግዚአብሔር በመወለዳችን የእግዚአብሔር ልጆች እንባላለን ፤ ስለዚህ ደግም « አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር » እያልን ልንጠራው ልጅነታችንንም ልንገልጥ እንችላለን ፡ ደግሞ ይገባናል ።

ሰማያዊው አባታችንን ማወቅ ስንፈልግ በመጀመሪያ ከምድራዊ አባታችን መነሣት አለብን ። ምድራዊ አባታችን ከእርሱ እንደመወለዳችን





እንደ ምድራዊነቱ ለልጆቹ ምግብ ልብስ ያስባል ፡ የተቻለውን ሁሉ በጎ ነገር ያደርጋል ፡ ግን ምድራዊ እንደመሆኑ የሚሰጠን ፤ የምንወርሰውም ሁሉ ምድራዊ ነው፡ እርሱም ሁሉ ያልፋል ይጠፋል ፡ እንዲያውም ሞትን ሳይቀር ከእርሱው እንወርሳለን ስለዚህ እኛም ሟቾች እንሆናለን ።

ሰማያዊ አባታችን ግን ሰማያዊ እንደመሆኑ የምንሻውን እንደፈጣሪነቱ አውቆ ይሰጠናል ፤ የፈለግነውንም እንድናገኝ ተዝናንነንም እንድንለምነው እድል ሰጥቶናል ። ስለ ሥጋዊም ስለ መንፈሳዊም ሕይወታችን ይናገራል ይሠራልም ። ሰማያዊ አባት እንደመሆኑም ሰማያዊ ሀብትን ፡ ጸጋን ይሰጣል ፡ የማያልፈውን ርስተ ሰማይ መንግሥተ ሰማያትን ያወርሳል ። አባታችን እንግዲህ ይኸን የመሰለ ፡ ይኸንም ሁሉ የሚፈጽም መሆኑ የታወቀ ነው ።

አባት ስንል ደግሞ የወልድ የባሕርይ አባት ነው ፡ እርሱን ዓለም ሳይፈጠር ከባሕርዩ ወልዶታል ፡ ስለዚህ እርሱ ወልድ ዋሕድ ይባላል ፤ ተቀዳሚም ተከታይም የለውምና። በፍጻሜ ዘመን ግን እኛን ሰዎችን በጸጋው ወልዶናል ስለዚህ ውሉድ ዘበጸጋ እንባላለን እኛም አባታችን እንለዋለን ።





አብን የወልድ አባት ስንል ወልድን አይበልጠውም አይቀድመውም ዕሪናቸው አንዲት ናትና ወልድና አብ ዕሩየ ባሕርይ ዕሩየ መለኮትም ናቸው ። ወልድ ከእውነተኛ ብርሃን የተገኘ እውነተኛ ብርሃን፡ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ነው ። አብና ወልድ አንድ ናቸው«አብን ያየ ወልድን አየ» ሲል ክርስቶስ ተናግሯልና (ዮሐ፡ ፲፬ ፡፱)።

አብ ከወልድ ጋር ያለውን አንድነት ፡ እኩልነት የገለጠልን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ እርሱም « እኔና አብ አንድ ነን » ሲል ተናግሯል ( ዮሐ፡ ፲ ፡ ፴) ።

እንግዲህ የወልድን አምላክነት ፡ የባሕር ልጅነት በዚህ መልክ ከተረዳን ይኸው አባት እኛን ደግሞ በጸጋው በምሕረቱ ይወልደናል ፤ ስለዚህም እኛ የእርሱ የጸጋ ልጆች ሆንን እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነ ሥጋንም ለበሰ ፡ ፍጹም እንደኛ ሆነ ። በእርሱ አምላክ ወሰብእነት በማመናችን ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ልጆችም ተብለን እንጠራ ዘንድ ሥልጣንን ሰጠን፡ (ዮሐ ፡ ፩ ፲፪) ።

እንግዲህ እኛ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን ሁሉ ሳናፍርና ሳንፈራ እግዚአብሔርን አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር እያልን ልንጠራው እንችላለን ።

በክርስቶስ አምነው ፥ ፪ኛ ልደትን በጥምቀት ተወልደው የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሁሉ እግዚአብሔርን አባታችን ሊሉት በትክክል ይችላሉ፣ በ፪ኛው ልደት በጥምቀት ጊዜ በመንፈሱ ወልዱቸዋልና ።

ነገር ግን በስም ክርስቲያን ሁነው ወይም መስለው እንዲሁ የሚኖሩት እግዚአብሔር አባታችን ሊሉት ልጆቹም ሊሆኑ አይችሉም ፤ደግሞ አይገባቸውም ። የእግዚአብሔርን ስም አጥፊዎች ናቸው ሐሰተኞችም ናቸው እንጂ። ምንም እግዚአብሔር የፍጥረቱ ሁሉ አባት ቢሆንም በዚህም መልክ የሁሉ አባት ቢባልም አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ብለው ሊጠሩት ሊለምኑትም የሚችሉ በመንፈስ በጥምቀተ ክርስትና ከእርሱ የተወለዱ፣እርጌውን አካል ያስወገዱ ብቻ ናቸው ። እነዚህም በፍቅሩ የጸኑ ፣ የትእዛዙም ተቀባዮች የሕጉም ፈጻሚዎች ናቸው።





እንግዲህ እኛ የንጉሠ ነገሥቱ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ በቸርነቱ በጥምቀት ወልዶናልና ፥ ልጆቹም እንደ መሆናችን ወራሾቹ ነን ፤ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ኩራት ይሰማናል፡ትምክህትም አለን፣ዝቅተኞች የነበርነውን ከፍ ከፍ አድርጐናልና፣ መሬታውያን የነበርነውን ሰማያውያን አድርጐናል ። ርቀን የነበርነውን በጸጋው አቅርቦናልና ፤ ባዕዶች የነበርነውን ልጆቹ አድርጐናልና። እንግዲህ ከዚህ ከወረዳው ተግባር ከዓለማዊም ሥራ መራቅ መኩራት አለብን ፥ ኃጢአት ፤ የውርደት ምልክት ነው፣ የውርደትም ሥራ ነው ፤ ኃጢአትም የሚሠሩ ሁሉ ወራዶች ናቸውና ። ልጅ እንደ አባቱ መሆን አለበት ፣ እንግዲያውስ አባታችንን እንወቀው እርሱንም እንከተለው። የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን የልጅነት ግዴታ አለብን፣ ይኸውም ፦

፩፣ ፍጹም ፍቅር በአባታችን በእግዚአብሔር እንዲኖረን

፪፡ ትእዛዛቱን ማክበርና መጠበቅ እንዳለብን

፫፣ ሁል ጊዜ ምስጋና ማቅረብ ሌላም ይኸን የመሳሰሉ የልጅነት ምልክት የሚሆኑ ልን





ጠብታቸው የሚገቡ ግዴታዎች አሉብን ። ልጆች በመሆናችን ወራሾች እንሆናለን ፥ ግን የአባታችንን ትእዛዝና ሕጉን ስንፈጽም ልጅነታችን ይጸድቃል ወራሽነታችንም ይታወቃል ።

አሁንም እንመን ልጆቹ ነን፤ ለእርሱ ያለው ሁሉ ለኛ ነው፣ እንግዲያውስ እርሱን ብቻ ደጅ እንጥና፣ እርሱን ብቻ እንከተል ፥ እርሱንም ብቻ እንለምን።

**ሐ ፣ አባት ሆይ፣** አባት ብሎ እግዚአብሔርን መጥራት የሰውን ተፈጥሮ ከፍ ያደርገዋል፤ እምነቱንም ፍጹም ያደርግለታል፣ ይኸም እውነተኛውን ጸጋ የማግኘት ምልክት ነው፤ ምክንያቱም የሁሉ ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን አባት ብሎ አባትም አድርጎ መቅረብ የፍጹምነት ምልክት ነውና ።

በዚህ ዐረፍተ ነገር እንደምንረዳው ሰው እንደፍጡርነቱ ሳይሆን አምላክን አባት አድርጎ አባትም ብሎ እርሱ ደግሞ ልጅ ሁኖ መቅረብ የሰውን የተፈጥሮ ጠባይ ይለውጠዋል በጣም ከፍ ያደርገዋል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምረን እግዚአብሔርን አባት እንድንለው ያዘናል እንጂ





መምህር ፥ ጌታ፣ንጉሥ እንድንለው አላዘዘንም ፥ አላስተማረም ፤ምክንያቱም ልጆቹ ከሆን ወራሾቹ እንሆናለንና ። ጌታችን ካልነው ግን ባሮች መሆናችን ነው ፥ ባሮችም ከጌታቸው ሀብት ምንም የሚወርሱት ምንም የሚደርሳቸው ነገር ከቶ የለም፣ ልጆች ግን ደጃፍ የመሰለውን ፥ ማጀት የጐረሰውን ፥ በውጭም ያለውን ሀብት ንብረት ይወርሳሉና ። እንዲያውም ከዚህ የበለጠ ባርያ ሁሉ ጌታው ምን እንደሚያደርገው ከቶ አያውቅም ፤ ይሸጠውና ይለውጠው እንደሆነ በቤቱም ያቆየው እንደሆን ምንም የሚያውቀው ነገር የለውም ።

ምስጋና ለእግዚአብሔር ይድረሰውና ሰዎች ባርያ እየተባሉ ይሸጡበት፣እንደዕቃም ይለወጡበት የነበረው ዘመን አልፏል ፥ ያለፍርሃት ያለኃፍረትም በገበያ ላይ የሚውሉበት ጊዜ አሁን ቀርቷል ፤በዚያን ጊዜ ግን ልጅ የሆነ እንደሆነ እንደ አባትየው የሀብት ብዛትና ማነስ ይለያይ እንጂ ሁልጊዜ ወራሹ እርሱነው ወራሹ እንደመሆኑም ከቶ የሚፈራው የሚሰጋበትም ነገር አልነበረም።ባሪያው ግን በዚያን ጊዜ ጌታው እንደፈቀደ የሚያውለው ስለ ነበረ ለኑሮው መድኅን ከቶ አልነበረውም መቼ ፥ ይሸጠኝ መቼስ ይለውጠኝ ፥ መቼ ከቤቱ ያወጣኝ ብሎ ይፈራ ነበርና

«ባሪያውም በቤት አይኖርም ለዘለዓለም፤ ልጅ ግን ለዘለዓለም ይኖራል » ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አግናኖዊ ቃሉን አሰምቷል (ዮሐ፡፰. ፴፭)

ክርስቶስ ራሱ ከኃጢአት ባርነት ነፃ ያወጣን የእግዚአብሔር ልጆችም ያደርገን ዘንድ ስለ ወደደ እግዚአብሔርን አባት ብለን እንድንጠራው መብት ሰጠን ። ልጅ በአባቱ ቤት ድልድል ቅምጥልም ነው ፤ ባርያ ደግሞ ሲሞት እንኳን እናቱ አትሰማም ስለዚህ አትቀብረውም ፤ ልጅ ግን ሲሞት ሰው ሁሉ ያለቅሳል፤ ጥይታውን ይገልጣል ፤ ለምሳሌ «የሹም ልጅ ሲሞት መቶ ሃምሳ ፤ ሹም ሲሞት ሃምሳ » ይባላልና ። እንግዲህ በልጅና በባሪያ መካከል ያለውን ልዩነት አጥብቀን እንመልከት እግዚአብሔር ግን ምስጋና ይግባውና ምንኛ ቢወደን ነው ልጆቹ እንጂ ባሮቹ ያላደረገን! አባት ብለንም እንድንጠራው የፈቀደልን! ።

ጌታ ሁሉ ለባሪያው ምን ማድረግ እንዳለበት ምን እንደሚያምረው ከቶ ግድ የለውም ፤ አያስብም ከአብራኩ ለተከፈለው ልጁ ግን ሁልጊዜ ያስባል ይሠራል። ልጁም ከዚህ ሁሉ መከባከብ የተነሣ በተስፋ ይኖራል፤ በሚደረግለት በሚታሰብለትም ሁሉ ይደሰታል ።





ባሪያ ደከመኝ ልረፍ ፤ አመመኝ ልተኛ ከቶ ሊል አይችልም ፤ ከቶ የዕረፍት ጊዜ የለውም ፤ እንዲሁም ሠርቶ የሚያገኘው ምስጋና የሚቆየው የሚጠበቅለት ተስፋ የለውም ፤ ቢሠራ ባለመመስገኑ ባለመሥራቱ ደግሞ የሚቀጣ በመሆኑ ተስፋው የጨለመበት ኑሮው መድኅን የሌለው ነው ።

እንግዲህ በዚህ ዓለም ኑሮ የባሪያና የልጅ ሕይወት ይኸን ያህል ልዩነት ያለው መሆኑን ተረዳን ፤ የእግዚአብሔር ልጆችም እንደ መሆናችን በወዲያኛው ዓለም ከፍ ያለ ተስፋ አለን ፤ ማለት ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን ወርሰን እንኖራለንና ። የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን የመንግሥቱ ወራሾች የስሙ ቀዳሾች ሁነን እንኖራለንና ፤ ስለዚህ ተስፋችን የተጠበቀ ነው። ይህ ይቀርብናል ይኸንንም እናጣለን ብለን የምንፈራበት መንፈስ ከቶ የለንም ፤ ልጆቹ እንደመሆናችን ሁሉን እንወርሳለንና ፤ ስለዚህ አምላካችን እግዚአብሔር ልጆቹ አደረገን ልጆቹም እንደመሆናችን «አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር » እያልን እንድንጠራው ዕድል ሰጠን ።

የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኔ እዘምራለሁ ፍጹም ደስታም ይሰማኛል ፤ የእርሱ ልጅ በመሆኔ





ሁሉን እወርሳለሁና ፤ ለከንቱም ልጁ አላደረገኝምና ።

እናት የወለደችውን ልጅን የምትረሳ ብትሆን እንኳን አባታችን እግዚአብሔር ፍጥረቱን ከቶ አይረሳም ፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆችም የሆን ሕይወታችን የተስፋ የደስታ ሕይወት ነው ።

የእኛን ልጅነት የእግዚአብሔርንም አባትነት ክርስቶስ ገልጦ ሲያስተምር እኛን በአንድ በጠፋ ልጅ የአባቱንም ሀብት ባባከነው ሲመስል፤አባታችን እግዚአብሔርን ደግሞ በደገኛው አባት መስሎ ተናግሯል ። ያ ደግ አባት በጠፋው ልጁ ሕይወት እንጂ በባከነው ሀብት ሳያዝን እንደቆየ ፤ እግዚአብሔርም በጠፋው በሰው ልጅ አዘነ ፤ ስለዚህም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን ልጁን ቤዛ አድርጎ ለሕማም ለሞት አሳልፎ ሰጠ ፤ ውረድ ተወለድ ሲል ላከው እንጂ የሰው ልጅ እንደወጣ እንዲቀር አላደረገም ። ያ የጠፋ ልጅ ጥፋቱን አምኖ ወደ አባቱ ቢመለስ ደግሞ አባቱ በክብር እንደተቀበለው እግዚአብሔርም የወደቀውን የሰው ልጅ በልጁ ሞት ታርቆ በክብር ተቀበለው ። ስለልጁ መመለስ አባትየው ፍሪዳ አርዶ ግብር አብልቶ ደስታውን እንደገለጠ አምላክም ቅዱስ ሥጋውን ክቡር





ደሙን ድኅንተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስ ይሆን ዘንድ ለሁሉ ሰጠ (ሉቃ. ፲፭፡፲፩ — ፴፪) ።

እንግዲህ በልጅና በባሪያ መካከል ያለውን ከፍተኛ ልዩነት አሁንም አጥብቀን እንመልከት አባት ለጊዜው ቢቆጣና ቢያዝን እንኳን ስለልጁ መሻሻል ፤ ስለልጁ ደኅንነት ሲል ነው እንጂ ቢቆጣም ቁጣው ለዘለዓለም አልሆነም ፤ ልጁም ጥፋቱን አውቆ ቢመለስለት እንደአባትነቱ ራርቶ በክብር ተቀብሎታልና ።

እንግዲህ እያንዳንዱ ሰው ለጊዜው መስሎት ተሳስቶ ከእውነተኛው መስመር ቢወጣ የእግዚአብሔርንም ልጅነት ቢያጣ በኋላ ተጸጽቶ ከተመለሰ እግዚአብሔር አምላክ በዚህ መልክ ይቀበለዋል ፤ እንደወጣ እንዲቀር አያደርገውም ቁጣው ለዘለዓለም አይደለምና ።

ይኸ አባታዊ ርኅራኄ በእግዚአብሔር ዘንድ ከፍ ያለ መሆኑን ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ሲል ይገልጣል « አባት ለልጆቹ እንዲራራ እንዲሁም እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል » (መዝ፡፻፫፡፲፫) ። በዚህ መሠረት ነው እግዚአብሔርን አባታችን ብለን እንጠራው እንቀርበውም ዘንድ ክርስቶስ ያስተማረን ።

የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም ነው ወሰን የለውም ፣ አይከፈልም ፣ ከቶ እግዚአብሔር ማንንም አይጠላም ፣ ማንም ከእርሱ እንዲለይ እንዲርቅም አይፈቅድም ፣ የሁሉ አባት ነውና ። እግዚአብሔር በማንም ላይ ክፉ ነገርን አያደርግም ፣ ለክፉም ነገር አሳልፎ አይሰጥም ፣ እኛ እያንዳንዳችን ለራሳችን ከምናስበው የበለጠ እርሱ ለእኛ ያስባል ፣ስለ እኛም ይሠራል ።

ማንም ሰው ለማንም ባሪያ እንዲሆን አይፈቅድም ፣ ማንም ሰው እንደ ባሪያ እየፈራ ለሕይወቱም እየተጠራጠረ እንዲኖር አያደርግም ፣ እርሱ የሁሉ ፈጣሪ እንደመሆኑ የሁሉም አባት ነው ፣ ስለዚህ ለሁሉ በጐውን ሀብት ፣ በጐውንም ዕድል ይሰጣል እንጂ ። እግዚአብሔርን አባታችን ስንል እንደ አባታችን እንደ አዳም ዘሩ ትውልዱ ሲቆጠር ሩቅ የሚሆን አይደለም ፣ ምስጋና ለእርሱ ይሁንና በቀጥታ ልጆቹ እንድንሆን ፈቅዶልናል ፣ ስለዚህ አባታችን እንለዋለን ቀጥተኛ አባታችን ነውና ።

እግዚአብሔር አምላካችን አባታችን እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮናል ፣ አባታችንም ብለን እንድንጠራው አዞናል፣ ይኸን እኛ





ማመንና መቀበል ፤ በእርግጥም እግዚአብሔርን አባታችን ማድረግ አለብን ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ እንዲጠራም ሥልጣን ተሰጥቶታል (ዮሐ. ፩.፲፪) ።

ጌታችን ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ከአባታችን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስተዋውቀን ነው፣ በዚህም መሠረት ነው እግዚአብሔርን አባታችን እያልን እንድንጠራው የሚያስተምረን ፣ ችግራችንንም ገልጠን እንድንነግረው እንድናወያየው እንድንለምነውም ነግሮናል ። ከኃጢአት ባርነት ነፃ አውጥቶ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን ዕድልን ሰጥቶናል ፣ የክርስቶስን አዳኝነት አምነን የምንቀበል ሁላችን የእግዚአብሔር ልጅነት አለን ከኃጢአት ባርነት ነፃ ወጥተናልና ። ሥራችን የቀና ሃይማኖታችን የጸና የሆን ሁሉ በትክክል የእግዚአብሔር ልጆች ነን ፣ እግዚአብሔርን አባታችን እንለዋለን፣አባታችንም እናደርገዋለን ፣ ሥራው ክፉ የሆነ ግን የዲያብሎስ የግብር ልጅ ነው ፣ አባቱ የሚለውም ሰይጣንን ነው ( ዮሐ ፣ ፰፣ ፵፬) ።





እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆን ትእዛዙን መጠበቅ ፣ ፍቅሩን በየጊዜው መግለጥ ፍለጋውን መከተል አለብን ፣ ምክንያቱም ተቆጣጣሪ አባት ያለው ልጅ ሁሉ መረን አይሄድምና ። በሕገወጥነት የሚሄዱ ሁሉ አባት የሌላቸው ተቆጣጣሪም ያጡ ናቸው ፤ እኛ ግን እግዚአብሔር አባታችን ስለሆነ በሕጋዊ መንገድ መሄድ ግዴታችን ነው።

ክርስቶስ በከበረ ደሙ ዋጀን ፣ ከኃጢአትም ባርነትም ነፃ አወጣን የእግዚአብሔር ልጆችም እንሆን ዘንድ አደለን ። እርሱ የአብ የባሕርይ ልጅ እንደመሆኑ እኛም ደግሞ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆቹ እንድንሆን ፈቀደልን « እናንተ ሁላችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት » ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል (ገላት ፣ ፫፣ ፳፮ ) ።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ወልዶናል ያውም ለተስፋ ( ፩ ፣ ጴጥ፣ ፩፡፫ ) ። ስለዚህ እኛ የእርሱ የጸጋ ልጆች ነን ፣ የልጅነትንም መንፈስ ስለሰጠን እግዚአብሔርን አባባ ፣ አባታችን ብለን እንጠራው ዘንድ ድፍረት አለን ( ሮሜ፣ ፰ ፣ ፲፭ ) ። ልጆቹ መሆናችንን አምነን የእርሱንም አባትነት ተቀብለን ወደርሱ ካልቀረብን አባታችን ልንለው ከቶ





አንችልም ፣ ደግሞም አይገባም ፣ የእርሱ የስም አጥፊዎች እንሆናለን እንጂ ። ነገር ግን በጸጋው እንደወለደን አምነን ሳንፈራ ሳናፍርም ወደ እርሱ እንድንቀርብ አባታችንም ብለን እንድንጠራው ፣ አባታችንም እንድናደርገው ክርስቶስ አስተምሮናል ።

እኛ ሰዎች ሟቾች ጠፊዎች ስንሆን የማይጠፋው እግዚአብሔር በቸርነቱ አቀረበን ፤ የልጅነትንም ጸጋ ሰጠን ፤ ስለዚህም ዘለዓለማዊውን አምላክ አባታችን ልንለው አባታችንም ልናደርገው ቻልን ፣ በዚህን ጊዜ የእኛንም ዘለዓለማዊነት እንገልጣለን ። የክርስቶስን ሥጋ በልተን ደሙን ጠጥተን እርሱን ተዋሕደን እርሱም እኛን ተዋሕዶን ለዘለዓለም ጸንተን እንኖራለንና (ዮሐ፣፮፣፶፭ — ፶፮) ።

ቀደም ብለው የተነሡ ነቢያት ፤ ካህናት ፤ ነቢዩ ዳዊት ሳይቀር ልዩ ልዩ የጸሎት ዓይነት ሲያቀርቡልን የምስጋና መዝሙርም ሲያዘጋጁልን ከእነርሱ ውስጥ ፩ኛውስ እንኳን ደፍሮ እግዚአብሔርን አባት ብሎ አባትም አድርጎ ያሳየ የጸለየም የለም ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ግን ስለኛ ክብር ሰው የሆነው እርሱ የአብ የባሕርይ ልጅ ሲሆን

እኛ ደግሞ የጸጋ ልጆቹ እንድንሆን አደለን ፡ስለ ዚህም የእግዚአብሔር ልጆች ሁነን ፡ እግዚአብ ሔርን አባት ብለን ፡ አባት አድርገን «አቡነ ዘበ ሰማያት » እያልን እንድንጠራው አስተማረን። እግዚአብሔር በባሕርዩ ፍቅር ነው ፡ ስለዚህ እኛን ይወደናል ፡ ስለዚህም ልጆቹ ይለናል ፡ በጸ ጋውም ልጆቹ አድርጎናል ፡ ስለዚህ እኛም አባታ ችን እንለዋለን አባታችንም እናደርገዋለን።

## መ. አባታችን ፤

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር አባታ ችን ብለን እንድንጠራው እንጂ አባቴ እያልን በግል እንድንጠራው አላስተማረንም ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሁሉ አባት ሲሆን እኛም ሁላችን የእርሱ ልጆችእንደመሆናችን ወንድማማችችና እኅ ትማማቾች ነንና ፡ ስለዚህም አንዱ ለሌላው መጸ ለይ መልካም መመኘት ያስፈልጋልና አባታችን እንድንለው አስተማረን ። እንዲሁም ከግል ጸሎት ይልቅ የማኅበር ጸሎት የበለጠ ጠቃሚ ነውና አባ ታችን ብለን በማኅበር ሁላችን ለሁሉ እንጸልያ ለንና ።





አባታችን እግዚአብሔር የወል አባት እንደ መሆኑ እኛ ለሌሎች ፡ ሌሎችም ለእኛ ሊጸልዩልን እንደሚገባ አድርጎ ጌታ ጸሎትን ሠርቶልናል አስ ተምሮናልም ።

የሰው ሁሉ መገኛው አንድ ነው ፡ ማለት በሥጋው ከአዳምና ከሔዋን በመንፈስ ደግሞ ከእግዚአብሔር ይወለዳል ፡ ስለዚህ ሁላችንም ወንድማማቾችና እኅትማማቾችም ነንና ልዩ ነትም የለብንምና አንዳችን ለሌሎች መጸለይ መለመን አለብን ፡ ስለዚህም እግዚአብሔርን የሁ ላችን አባት ለማለት አባታችን ሆይ ብለን እንጠ ራዋለን ፡ አባታችንም እናደርገዋለን ፤ ልጆችም በበኩላቸው የአንድ አባት የእግዚአብሔር ልጅነ ታቸውን አውቀው እርስ በራሳቸው በስምምነት ሊኖሩ ይገባል ፡ ጥል፡ቅናት፡ምቀኝነት፡መለያየትም ይጠፋል ፤ በሰው ልጅ መካከል አንድነት ይፈጠ ራል ፡ ለኔ፡ለኔ የሚለውን ራስን ወዳድነት ይቀራል፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሁኖ ሰው ሁሉ በኅብረት በስምምነት እንዲኖር ያደርገዋል ።

እንዲሁም እግዚአብሔርን አባታችን ባልነው ጊዜ የሰውዘር ሁሉአንድ መሆኑን ሁሉም ከእግዚአ





ብሔር መወለዱን ፡ እኩልነቱን ፤ ደሀው ከባለጸ ጋው ፤ ዝቅተኛው ከከፍተኛው ፤ ሕዝቡ ከባለሥል ጣኑ ጋር እኩል መሆኑን ከማስተዳደር ሥልጣኑ በቀር ያልተለየ መሆኑን ፤ በጐሳ ፤ በቀለም ፤ በዜ ግነት ቢለያይም አንድ የእግዚአብሔር ልጅ መሆ ኑን አውቆ ተከባብሮ ተለባብሶ መኖር የሚገባ መሆኑን ያስረዳል ። እንዲሁም በጾታ በማዕርግ ልዩነት የሌለበት ሰው የተባለው ሁሉ የአንድ እግ ዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሁሉም አንድ መንግሥትን የሚወርስ መሆኑን ያስረዳል ።

ምንም ብዙዎቻችን የግል ችግር እየገጠመን በግላችን ብንጸልይና የግል ችግራችንን ለእግዚአ ብሔር ገልጠን ለመናገር ብንሞክርም በግድ ይኸን ጸሎት መጸለይ አለብን፤እታዲያ በዚህን ጊዜም ቢሆን የወል አባታችን የሆነውን የእግዚአብሔርን ስም ማንሣት አባታችንም ብሎ መጥራት ግድ ይሆንብ ናል ። እንግዲህ የእርሱን አባትነት የሰውን ሁሉ ወንድምነት እኅትነትም እንገልጣለን እንመስክ ራለንም ማለት ነው ።

እያንዳንዱ ሰው ለሁሉ ፡ ሁሉ ደግሞ ለእያን ንዳንዱ መጸለይ ግድ ይሆናል ፡ የክርስትናውም ዋና ዓላማ ይኸን የመሰለ ነው፣ ይኸን የመስለውን





ዓላማ በማጽደቅ ሐዋርያው ያዕቆብ «እርስ በርሳ ችሁ ተናዘዙ በኃጢአታችሁ ፡ አንዱም ለአንዱ ይጸል ይለት እንድትፈወሱ ፡ የጻድቅ ጸሎት ታላቅ ኃይል ታደርጋለችና » ሲል ይገልጥልናል ( ያዕ፡ ፭ ፡ ፲፮) ።

## ሠ. በሰማያት የምትኖር

«በሰማያት የምትኖር » እግዚአብሔር አም ላክ ሰማያዊ መሆኑን በከፍተኛውና በራቀው ዓለም የሚኖር እንደሆነ ለመጠቆም ሰማያዊ ብለን እንድ ንጠራው ክርስቶስ አስተማረን ።

እግዚአብሔር አምላክ በዓለሙ ሙሉ የሆነ እንጂ የተወሰነ ፡ የተለየ ቦታም የተለየ ሀገርም ያለው አይደለም ፤ ለዓለም መሠረቱ እርሱ ነው ፤ ጠፈሩም እርሱ ነው ፤ ወደቀኝም እርሱ ነው ፡ ወደ ግራም እርሱ ነው ፤ በፊትም እርሱ ነው ፡ በኋ ላም እርሱ ነው ።ስለ ክብሩና ስለ ልዕልናው ብቻ በሰ ማያት ያለ ከሰማያት የወረደ ፡ እንለዋለን እንጂ እርሱ የሌለበት ቦታ ከቶ የለም ፡ በአንድ በሰማ ይም ብቻ የሚወሰን አምላክ አይደለም ።

ክርስቶስ ስለ አብ ሰማያዊነት ብቻ ሳይናገር እርሱም ሰማያዊ አምላክ እንደሆነ ገልጦ ተናግሯል። «ማንም ወደ ሰማይ ያረገ የለም ከሰማይ ከወረደው በቀር ፡ እርሱም የሰው ልጅ በሰማይ የሚኖር »

ሲል ተናግሯልና ( ዮሐ፡ ፫ ፡ ፲፫ ) ።

በሰማያት የምትኖር ብለን ስንጸልይ ከዚህ ተጣ ብቀን ከምንኖበት ኃላፊና ጠፊ ዓለም ከዝቅተኛ ውም ሕይወታችን ያላቅቀናል ፤ ከፍ ከፍም ያደር ገናል ፤ ወደ ሰማያዊው አባታችንም ያደርሰናል ።

ይኸ ዓለም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንኖርበት ዘንድ ተሰጥቶናል ፡ነዋሪና ቀዋሚ ግን አይደለም፣ እንዲያውም ስለ የኋለኛው ሕይወታችን መሰናዶ እንድናደርግበት በጎ አድራጎትንም እንድንፈጽ ምበት የተሰጠን ዓለም ነው ፤ በዚህም መሠረት እስከዚያው እንንቀሳቀስበታለን እንጂ መኖሪያችን አይደለም ።

እግዚአብሔር አባታችን ሰማያዊ እንደመሆኑ ሰማያዊ ክብርን ሰማያዊ መንግሥትን አዘጋጅቶል ናል ፤እንግዲያውስ እኛም ከምድሩ የተላቀቅን ወደ ሰማይ የመጠቅን ፡ ሰማያዊ አባታችንን የምንከተል ሁነን መገኘት አለብን ።

በዚህ ምድራዊ ሕይወታችን በምንሠራው በጎአድራጎት የማታልፈውን መንግሥት ሰማያት ልንወርስበት ዘለዓለማዊውን ሰማያዊ አባታችንን ልናገኝበት እንችላለን ። አባታችን ለሁሉ የሚበቃ ቦታ አዘጋጅቷል ፡ ሁሉንም ወደርስቱ ወደ መን





ግሥቱ ይጠራል «ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብ ሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ ---» ሲል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይገልጽልናል (ዮሐ. ፲፬፡ ፩ )።

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከመውደዱ የተ ነሣ የስሙ ቀዳሽ የክብሩ ወራሽ ሁኖ ይኖር ዘንድ ከምድራዊ ሕይወት ተላቅቆ ሰማያዊውን አምላክ ተዋሕዶ ይኖር ዘንድ የተለያየ የክብር ቦታ አዘጋ ጅቷል ። ይኸም የክብር ቦታና በውስጡ ያለው ዝግጅት «ዓይን ያላየው ፡ ጆሮ ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበ ነው ። እግዚአብሔር ለሚ ወዱት ያዘጋጀው---» ሲል ቅ፡ ጳውሎስ ተናግ ሯል (፩ ቆሮ፡ ፪፡ ፱) ።

ይኸም ሰማያዊ ርስት ሰማያዊም ቦታ ከዓለም መፈጠር ቀድሞ ለሰው ልጅ ሁሉ የተዘጋጀ እንደ ሆነ ክርስቶስ መስክሮ ተናግሯል (ማቴ ፡ ፳፭፡፴፬ )።

እንግዲህ ጸሎት በጸለይን ቁጥር «አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር» ስንል የአባታችንን ሰማያዊነት እንመሰክራለን ፡ የእኛም ሕይወት ሰማ ያዊ መሆኑን እንረዳለን ለሰማያዊ ርስታችን በቂ ወራሾች መሆን እንዳለብን ያስጠነቅቀናል ።





አንድ አባት የሁል ጊዜ ምኞቱ ልጁ ደርሶ ለት በእግሩም ተተክቶለት የርስቱ የሀብቱ የመ ብቱ ወራሽ ሁኖለት ይኸን አይቶ መሞቱ ነው ። ልጁ ደግሞ ይኸንኑ ተረድቶ አባቱን መስሎ ፡ የአ ባቱንም ፍለጋ ተከትሎ ክብሩን ጠብቆ መኖርና ያን ሁሉ መውረስ እንዳለበት አምኖ ተጠብቆ ይኖራል ፡ ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ውርስ በመ ወለድ ብቻ አይደለምና ። ቢወለድም ሊካድ ይች ላል ፡ ምንም ሳይወርስ ሳያገኝም ሊቀር ይችላል ። እኛም እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ስንሆን ሰማያዊያን መሆናችን ፡ ሰማያዊ ክብር ያለን ፡ ሰማያዊ መንግሥትን የምንወርስ መሆናችንን ተገ ንዝበን የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ ፡ ትእዛዙን በማክበር ፡ መኖር አለብን ፤ ያለዚያ የተዘጋጀልንን የተጠበቀልንንም ርስትና መንግሥት ልንወርስ አን ችልም ። ምድራዊ ሐሳቡን ሳይለውጥ ምድራዊ ሰው ርስተ ሰማይን ሊወርስ አይችልምና ፡ በእግ ዚአብሔር ዘንድም መካድ መጠላት አለና ።

እንግዲያውስ ሐሳባችንም ምኞታችንም ሥራ ችንም ሰማያዊ እንዲሆን ፡ ሰማያዊ አባታችንን ለመከተል ሰማያዊ መንግሥቱንም ለመውረስ ይሁን ።





ክርስቶስ ሲያስተምር ብዙ ሰማዮች እንዳሉ እግዚአብሔር አባትም ሁሉን ሞልቶ እንደሚኖር አድርጎ «አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር » ሲል አስተምሮናል ።

ሰማያት ብዙዎች እንደሆኑ በብዙ ቦታ ዎች ላይ ክርስቶስ ገልጦ ተናግሯል (ማቴ፣ ፫፡ ፪፤ ፬ ፡ ፲፯ ፣ ፯ ፡ ፳፩)። ቅዱስ ጳውሎስም ስንት ሰማያት እንዳሉ ልካቸውን በቁጥር አልገለጠልንም እንጂ ቁጥራቸው ብዙ እንደሆነ እስከ ፫ኛውም ሰማይ እንደ ዐረገ ገልጦ ጽፏል (፪ ቆሮ. ፲፪. ፪ ) ። ይኸንንም ተከትለው ሊቃውንት የሰማይን ብዛት አምነው በቁጥር ወስነው ሰባቱ ሰማያት እያሉ ይጠሯቸዋል ፡ ስማቸውም እንደሚከተለው ነው፥

፩.መንበረ መንግሥት
፪.ጽርሐ ዓርያም
፫.ሰማይ ውዱድ
፬.ኢየሩሳሌም ሰማያዊት
፭.ኢዮር
፮.ራማ
፯.ኤረር የሚባሉ ናቸው ።

ስማቸው ይለያይ እንጂ ይኸን የመሰለ ቁጥር በዕብራውያንም ቴዎሎጂ ይሰጣል ፤ ማለት ሰማያት ፯ እንደሆኑ ይነገራል፤ምናልባትም የኛ አስተሳሰብም የመጣው ከነእርሱ ቴዎሎጂ ሊሆን ይችላል ። በዕብራ ይስጡ ግን ከመሠረቱ በነጠላ ቁጥር ሰማይ የሚ ቃል የላቸውም፤ሰማያት እንጂ ።

## ፪. ስምህ ቅዱስ ነው ፤

«ይትቀደስ ስምከ » ስምኽ ይቀደስማለት ሁል ጊዜ የተቀደሰ የተመሰገነ ይሁን ማለት ነው ። ስምህ በሰማይ ሠራዊት ዘንድ ቅዱስ፥ቅዱስ፥ቅዱስ እየተባለ እንደሚመሰገን እንዲሁም በምድር በደቂቀ አዳም ይመስገን ማለት ነው ። በሰማይ ያሉ መላእክት ዕረፍት ሳይኖራቸው ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ስም ሲቀድሱ እንደሚኖሩ ዮሐንስ በራእዩ ነግሮናል (ራእ፡፬፡፰) ። በእኛም ዘንድ እንዲሁ ያለዕረፍት ያለምቋረጥ ስምህ ይመስገን እንለዋለንና ።

ስምህ ይቀደስ ማለት ይከበር ፣ ይመስገን ፣ ማለት ነው ፣ እግዚአብሔር የክብር ባለቤት የምስጋናም ጌታ ነውና ፣ እግዚአ ስብሐት ፣ ንጉሠ ስብሐት እየተባለ ይመሰገናል ። የእግዚአብሔርን የአባታችን ስም ስንቀድስ ግን እኛም በንጽሕና ፤





በቅድስና አጊጠን ወደ እርሱ እንድንቀርብ ያስፈልጋል ።

እግዚአብሔር በባሕርዩ ቅዱስ ነውና ፣ ስለዚህ ይትቀደስ ስምከ እንድንለው አዘዘን ። እግዚአብሔር በመላ አካሉ በባሕርዩም ቅዱስ ነው ሳይል ስምህ ይቀደስ አለ ፣ ስም ሁሉን ያጠቃልላልና ፣ ስሙ ከጠፋ ሁሉ ጠፋ ፣ ስሙ ከታወቀ ሁሉም ይታወቃልና ። በመዝገብ የሚጻፍ ስም ነው፤ሰውየው በመላ የሚጠራው በስሙ ነው፤ ታሪኩ ሲጠፋ ስሙ ጠፋ ይባላል፤ ስም የሁሉ መግለጫ ነውና ። ስሙ የታወቀ ነው ፣ ስሙ ገናና ነው ሲባል በአጠቃላይ የሰውየውን ታላቅነት ያመለክታል ፣ ዝነኛነቱን ይገልጣል ፣ የእግዚአብሔር አምላክም ስሙ ቅዱስ ነው ስንል ሁለንተናውን ቅዱስ ነው ማለታችን ነው ።

የእግዚአብሔርም ስም ቅዱስ እንደሆነ ቅድስት ማርያም «ስሙም ቅዱስ ነው »ስትል መስክራለች ( ሉቃ፣ ፩ ፣ ፵፱ ) ።

የእግዚአብሔር ስም በኛ ምኞት በኛም ሐሳብ ብቻ የሚቀደስ አይደለም ፤ ነገር ግን ይኸን ጸሎት በጸለይን ጊዜ የእርሱን ቅድስና እንድንመሰክር ሲያስገነዝበን ብቻ ነው ፤ ምክንያቱም የእግ





ዚአብሔር ቅድስና ሰማይንና ምድርን የመላ ነውና።

ስምህ ይቀደስ ማለት ስምህ ምስጋናን ቅዳሴን የተመላ ነው ብሎ መመስከር እንዲሁም እኔን ስምህን ለመቀደስ የበቃሁ አድርገኝ ብሎ መለመን ነው ። በኛ ምክንያት ስምህ የሚነቀፍ የሚሰደብም አይሁን የሚቀደስ የሚከበር እንጂ።

እኛ ኃጢአተኞች ስንሆን የስምህ ቀዳሾች የክብርህም ወራሾች ለመሆን የበቃን አድርገን ማለት ነው ።

በመሠረቱ ሰው የተፈጠረው የእግዚአብሔር የስሙ ቀዳሽ የክብሩም ወራሽ ለመሆን ነው ፣ ሆኖም ይኸን ሁሉ አምላክ ከአልፈቀደው አይሆንምና የእርሱ ቅዱስ ፈቃድ እንዲጨመርበት«ስምህ ይቀደስ » ብላችሁ ጸልዩ ሲል ጌታ አዘዘ ።

ሰው ለምስጋና የተፈጠረውን ያህል በቃሉ ፣ በሥራው በኑሮው ሁሉ የእግዚአብሔርን ምስጋና መግለጥ አለበት ፣ ምክንያቱም አመስጋኙ እርሱ ብቻውን ሳይሆን እርሱን የሚመለከቱ ሥራውን ሁሉ የሚያውቁ የትሩፋት አበጋዝ ያስነሣህልን እያሉ እግዚአብሔርን እዲያመሰግኑት ምክንያት ይሆናልና (ማቴ፡ ፭ ፣ ፲፮ )። ይኸን የመሰለ ተግባር ሁላችንም እንፈጽመው ዘንድ ግዴታ አለ





ብን ፣ ግን ይኸን ሁሉ ለመፈጸም ደግሞ ከሥጋዊ ፣ ከዓለማዊ ግብር የራቅን በመንፈስ የጠለቅን እንደመላእክትም ለምስጋና የተሰለፍን እንድንሆን ያስፈልጋል ።

ቤተ ክርበቲያንን በመደገፍ ፣ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመከተል ፣ የቤተ ክርስቲያንን ትእዛዝ ሁሉ ከአሟላን ለእግዚአብሔር ስም መቀደስ ምክንያት ሆን ማለት ነው ፣ ስለዚህ ይኸንንም ተግባር ግዴታ መሆኑን አምነን መፈጸም አለብን ።

በተቃራኒው ግን የእግዚአብሔርን ስም የሚሳደብ ስሙን ከንቱ የሚያደርግ እግዚአብሔርም ሳይቀሥፈው አይቀርም (ዘጸ፣ ፳ ፡ ፯ ) ።

ሰው ሁሉ ፍጡር እንደመሆኑ ይበድላል ፣ እግዚአብሔርም አባት እንደ መሆኑ በደልን ሁሉ ይቅር ይላል፣የእግዚአብሔርን ስም የሰደበ ግን በደሉ ከፍተኛ ስለሆነ ኃጢአቱ አይሠረይለትም በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ፤ ለዘለዓለሙ ይቀጣል እንጂ (ማቴ ፣ ፲፪ ፣ ፴፩ — ፴፪ ፤ ማር፣ ፫ ፣ ፳፫ ፤ ሉቃ ፣ ፲፪ ፣ ፲ ) ። የእግዚአብሔርንም ስም እየሰደቡ በዚህ ዓለም እንኳን የተቀጡ ፣ መቅሠፍትም የደረሰባቸው ብዙዎች ናቸው ፤ ከእነርሱም ውስጥ ፣

፩፡ ብልጣሶር የተባለው የናቡከ ደነፆር ልጅ ነው፤ እርሱም በቤተ መቅደሱ ንዋያት ላይ የማይገባ ሥራ ስለ ሠራበት የእግዚአብሔርን ስም እንደናቀ እንዳቃለለም ተቆጥሮ መንግሥቱ ለሜዶናዊያን ተሰጠችበት (ዳን፡ ምዕ.፭) ።

፪፡ ንጉሡ ሰናክሬም ኃይል ቢሰማው በኢየሩሳሌም ውስጥ ለማዳን የሚችል ጣዖት አለን ? በማለት የእግዚአብሔርን ስም በመስደቡ በሌላ ጠላት ሳይሆን በራሱ ልጅ እንዲገደል አድርጎታል ( ፪ ነገ. ምዕ ፲፱ ) ። እኛ ክርስታያኖች ሥነ ምግባራችንን አሳምረን ለእግዚአብሔር ስም መመስገን ምክንያት መሆን፤ አለብን ፤ ያለዚያ ክፉ ልጅ አባቱን ያሰድባል ሲል ሰሎሞን እንደተናገረው፤ ለእግዚአብሔር ስም መሰደብ ምክንያት እንሆናለን ( ምሳ፡ ፲ ፡ ፩ ) ። እኛ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ስም መቀደስ ማሰብ መናገር መሥራት አለብን ።

የእግዚአብሔር ስም በምስጋና ብቻ ይነሣል፤ ይቀደሳል እንጂ መሰደብ አይገባውም፤ሰውን እንኳን የሰደበ በገሃነም የሚፈረድበት እንደሆነ ተነግሯል (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፪) ። የእግዚአብሔርን ስም የሰደበማ እንደምን የበለጠ አይፈረድበት !





የአምላክን ስም ሲደፍር በእርሱም ላይ ክፉ ሲነገር ዝም ብሎ ማየትና መስማት እንኳን እንደ ተሳዳቢው ያስገምታል ፤ ያለ እውቀት የሚናገር እንደሆን መምከር ማስተማር መገሠጽ ፤ እያወቀ ይሁን ብሎ ሠርቶት እንደሆን ደግሞ ለዚያ ንግግር ማስተባበያ መስጠት ፤ የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ እንደሆነ ማስረዳት ለአማንያን ሁሉ ተገቢ ነው ።

አንድ ሰው ድንገት ከሌላ ሰው ጋር ቢጣላና የመምታት ወይም የመግደል አደጋ አደርሳለሁ ቢል የእርሱ የሆነው ውሻ እያየ ዝም አይልም ፤ የጌታውን ሕይዎት ለማዳን ሲል የተቻለውን ያህል ይጣጣራል፤የጌታውንም ጠላት ወደ መንከስ ይመለሳል ። እንግዲያውስ ሰውየው ከውሻው ፤ ጌታም ከጌታው ይበልጣልና የእግዚአብሔር ስም ሲሰደብም ሲነቀፍም እያዩ ዝም ማለት ተገቢ አይደለም ፤ ከውሻ ማነስ ነውና ። ስለ እግዚአብሔር ህልውና ስለ እግዚአብሔር መግቦት ፤ ስለ እግዚአብሔርም ታላቅነት መመስከር ፤ መናገር ለሁሉ ተገቢ ነው እርሱ የሁላችን አባት ነውና ።

ማንም ሰው አባቱ ሲሰደብ ዝም ብሎ ቁሞ የሚያሰድብ ከቶ አይገኝም ፤ እንግዲያውስ እውነተኛው አባታችን ያውም ሰማያዊ አባታችን ስሙ





ይቀደስ እንጂ የስድብ ቃል ሊነገርበት አይገባም ።

እኛ የተፈጠርነው ለምስጋና ለቅዳሴ ስለሆነ፣ በየጊዜው ንጹሕ ምስጋና ልናቀርብለት ስሙን ልንቀድሰው ይገባናል ። እርሱ መልካም ልጆች ያሉት አባት ነው ፤ ልጆቹንም እንደሚቀድሳቸው የታመነ ነው ፤ ስለዚህ እኛም በአባታችን ፊት መልካም ልጆች እንደሆን የስሙ ቀዳሾች እንሆን ዘንድ ይገባናል ።

እኛ እውነተኞች ክርስቲያኖች እንደመሆናችን በሥነ ምግባራችን በጸጥታዊ ሕይዎታችን የእግዚአብሔርን ሕልውና የምናስመሰክር ስሙን የምናስቀድስ እንሁን ።

የቤተ ክርስቲያናችንን ትእዛዝ በመጠበቅ፤ በምታስተምረው ትምህርት መጽናናት የእግዚአብሔርን ህልዎት እንገልጣለን ፤ ለስሙም መቀደስ ምክንያት እንሆናለን ።

ማንም ሰው ክርስቲያን ነኝ እያለ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውጭ ከሆነ ለእግዚአብሔር ስም መሰደብ ምክንያት ይሆናል ፤ ለእግዚአብሔርም ስም መሰደብ ምክንያት የሚሆኑትን ቅ፡ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይወቅሳቸዋል «በእናንተ ምክንያት





የእግዚአብሔር ስም ይሰደባል በአሕዛብ ዘንድ—» ( ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ፤ ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፭ ) ። ክርስቶስ ደግሞ መልካም ሥራ የሚሠሩ ለአባቱ ስም መመስገን ምክንያት እንደሚሆኑ በሰፊው ገልጦ ተናግሯል ( ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ) ።

## ፪ የመንግሥተ ሰማያት መምጣት፤

«ትምጻእ መንግሥትከ ፤ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር » ( ማቴ . ፮፡፲ ) ።

መንግሥትህ ትምጣ ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁም በምድር ይሁን ።

ይኸም ከመጀመሪያው ክፍል የቀጠለ የምስጋና ክፍል የምስጋናም ጸሎት ነው ፤

«ትምጻእ መንግሥትከ » እያልን በጸለይን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት አካል ወይም ግዕዛን ኑሯት ወደኛ ትመጣለች ማለት አይደለም ፤ አስቀድሞ አምላክ ለእኛ ያዘጋጃት እንደመሆኗ ትሰጠን እንውረሳት ፍቀድልንም እንደማለት ነው፤ ይኸን ጸሎት በጸለይን ጊዜ ግን አንድ ሰው የጌታን ፪ኛ ጊዜ መምጣት የናፈቀ ፤ ዓለም ሳይፈጠር ያዘጋጃትን መንግሥቱን ለመውረስ የቸኮለ መስሎ ይታያል ።

መንግሥተ ሰማያት የሚለውን ቃል ሊቃውንት በልዩ ልዩ መልክ ተርጉመውታል ፤

፩፡ በጥምቀት የምትገኘው ልጅነት እንደሆነች ተናግረዋል ፥ እርሷ ትስጠን ማለት ነው ።

፪፡ መንግሥተ ሰማያት የምትባል ወንጌል ናት ፤ እርሷን በብዙ ቦታ ወንጌለ መንግሥት ይላታልና፥ ስለዚህ ወንጌለ መንግሥት ገንዘባችን ትሁን ፤ በወንጌል ትምህርት የሰለጠንን እንሁን ማለት ነው ።

፫፡ ከዓለም ኅልፈት በኋላ የምትመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ናት እርሷን፥እንውረሳት፤ ስጠን ለእርሷም አብቃን ማለት ነው ።

የእግዚአብሔር መንግሥት የምትባለው ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ልቡል እግዚአብሔር ለተመረጡና ለእርሱ ቡሩካን ያዘጋጃት ናት ፥ ይኸም እውነት መሆኑን ክርስቶስ ሲያስተምር « ኑ ያባቴ ቡሩካን መንግሥትን ውረሱ ፥ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን » ሲል መስክሯልና /ማቴ ፥ ፳፭ ፥ ፴፬/ ።

ሁል ጊዜ ስንጸልይ ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር ለኛ ያዘጋጃትን መንግሥት ለመውረስ የበቃን አድርገን ማለት ነው።ይኸንም ቃል የሚያስገነዝበን እያንዳንዱ ክርስቲያን ተድላና ደስታ ያለ





በትን የዘለዓለም የዕረፍት ቦታን ወርሶ ለመኖር መጓጓት፤መጣጣር፤መናገርም መጸለይም እንዳለበት የሚያስረዳ ነው ። ክርስቶስ ንጉሣችን ነው ፥ ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ አውጥቶ ያስተዳድረናል ፥ ስለዚህ እርሱም ንጉሥ ሁኖ እንደመጣልን የእርሱ መንግሥትም ትምጣልን እያልን እንጸልያለን ።

መንግሥተ ሰማያት የምትወረሰው በፍጻሜ ዘመን ቢሆንም ያችን ርስት ለመውረስ አስተማማኝ የሆኑትን ግብሮች አሁን መፈጸም ግድ ይሆንብናል ፥ ፩ኛውም ግብር ጸሎት ስለሆነ ለዚያች መንግሥት አብቃኝ ማለት « ትምጻእ መንግሥትከ» እያሉ ከአሁኑ መጸለይ ተገቢ ነው ። ተስፋችን የወዲያኛው ዓለም የእግዚአብሔር መንግሥት ነውና፤በምናየው ዓለም ለውጠን ያንተ መንግሥት ትምጣልን እንወርሳት ዘንድ ለማለት ትምጻእ መንግሥትከ እያልን እንጸልያለን ።

ሀ ፡ « ትምጻእ መንግሥትከ » እያልን ስንጸልይ የእግዚአብሔር መንግሥት ከዚህ ዓለም መንግሥት ፥ እርሱም ከዚህ ዓለም ንጉሥ ፥ ሕጉም ከዚህ ዓለም ሕግ የተለየ ስለሆነ አስቀድሞ እግዚአብሔርን ማወቅ ቀጥሎም መንግሥቱን መናፈቅ ለዚህም የሚያበቃ ግብር መፈጸም እንዳለብን ያስ





ገነዝበናል ።

ለ ፤ « ትምጻእ መንግሥትከ » እያልን ስንጸልይ የእግዚአብሔርን ሕግ የጠበቅን ለእርሱም የታዘዝን እንደሆን አብም ወልድም መጥተው ማደሪያ ያደርጉናል ፤ መንግሥተ ሰማያትም ማለት እርሱን ወርሶ ፥ እርሱንም ተዋሕዶ መኖር ነው ።

ስለዚህም ክርስቶስ ሲያስተምር የሚወደኝ ሕጌን ይጠብቅ ሕጌንም በሚጠብቀው እኔም አባቴም መጥተን ማደሪያ እናደርጋለን ሲል ተናግሯል / ዮሐ ። ፲፬ ፡ ፳፫ / ።

ሐ ፡ «ትምጻእ መንግሥትከ » በማለት ስንጸልይ መንግሥተ ሰማያትን ናፍቀናል ለመንግሥተ ሰማያት በቅተናል ማለት ነው ፥ በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ጸጋ ጽድቁም ቅድስናውም በእኛ ላይ ይነግሣል ፥ ልቡናችንም የእርሱ ዙፋን መ ዘርጊያ ይሆናል ።

## ፫. ፈቃድህ ይሁን ፥

«ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር» በዚህም ጸሎት ጊዜ ጥያቄያችን ሁሉ ፈቃድህን አድርግልን ፥ ኃይልህን ስጠን ፥ ውድህንና ፈቃድህን በምድር እንፈጽም ዘንድ ፍቀድልን የሚል ነው ።





የእግዚአብሔር ፈቃድ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምን እርሱንም እንድንቀበል ነው ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ « የምወደው ልጄ ይኸ ነውና ስሙት » የሚል አዋጅ አሰምቶ ነበርና / ማቴ ፡ ፲፯ ። ፭ / ። ክርስቶስ ደግሞ ሲያስተምር የአባቴ ፈቃድ በላከው ታምኑ ዘንድ ነው ይላል፤ ስለዚህ የእርሱ ፈቃድ ይኸ ነውና /ዮሐ ። ፮፡፳፰/። ይኸም ፈቃድ በሰማይ በሚኖሩ መላእክት ተፈጽሞ ይሆናል ፤ ሁሉም በእርሱ ይገዛሉና ፥ ስለዚህም ቅ ፡ ጳውሎስ ማነው ወደሰማይ ያረገው ፥ በአብ ቀኝም የተቀመጠው ? መላእክትም ሥልጣናትም ኃይላትም የሚገዙለት » ሲል ተናግሯል / ኤፌ ። ፩ ፳፩ ፤ ቆላስ ። ፩ ፥ ፲፭ / ። ይኸ በሰማይ በመላእክት ዘንድ የተፈጸመው ቅዱስ ፡ ፈቃድህ በምድርም በሰዎች ዘንድ ይፈጸም ማለት ነው ።

ቅዱሳን መላእክት ፈቃድህን በሰማይ ይፈጽሙ ዘንድ ፈቃድ እንዳ ሰጠሃቸው ለኛም በምድር ስጠን ፈቃድህንም አድርግልን ። መላእክት በሰማይ ሳያቋርጡ እንዲያመሰግኑ ፥ ይኸም የእነርሱ ምስጋና ፈቃድህ እንደሆነ እኛንም እንደመላእክት አድርገን ፤ ሁል ጊዜ አንተን በማመስገን ጸንተን እንድንኖር አድርገን ፥ የኛንም ምስጋና በአንተ

ዘንድ ተቀባይነትን የሚያገኝ አድርግልን ።

መላእክት በሰማይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽሙ ይታዘዙም ዘንድ ዝግጁ እንደሆኑ ፣ ነቢዩ ዳዊት ተናግሯል /መዝ. ፻፫. ፳፩/። እኛም እንደሰማያዊያን መላእክት በምድር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ዝግጁ አድርገን ፣ ይኸንንም ጸጋ አድርገህ ስጠን ብለን እንድንጸልይ ያስገነዝበናል ። በሰማይ ያሉ መላእክት የተፈጥሮ ጠባያቸውን ሳይለውጡ በንጽሕና በቅድስና ሁነው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ እንደሚኖሩ ፣ ይኸም ሥራቸው የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ እንደሆነ በምድርም ደቂቀ አዳም ሁሉ በንጽሕና በቅድስና ሁነው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑትና ይኸም በእግዚአብሔር ዘንድ የተፈቀደ አድርግልን ማለት ነው ።

በሰማይ ያሉ መላእክት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ሁልጊዜ ዝግጁ ሲሆኑ ፣ ኃዘን ዕንጉርጉሮ አይሰማቸውም ፣ በደስታ ይፈጽሙታል እንጂ ፣ እንዲሁም እኛ በምድር ያለን ሰዎች ፈቃዱን ያለ ኃዘን ያለ ዕንጉርጉሮ በደስታ እንድንፈጽመው በንቃትም እንድንጠብቀው አድርገን ።

እኛን ሰዎችን እግዚአብሔር ሲፈጥረን ለተ



ቀደሰ ዓላማ ነው ፣ ይኸውም ስሙን ቀድሰን ክብሩን ወርሰን እንድንኖር ነው ፣ ስለዚህ አምላክ የፈጠረበትን ቅ ፣ ዓላማ ፈጽመን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ አውቀን እንደፈቃዱም ሂደን እርሱን አስደስተን እንኖር ዘንድ «ወይኩን ፈቃድከ» እያልን መጸለይ አለብን ።

በዚህ ዓለም ስንኖር ከኛ ፈቃድ ይልቅ የእግዚአብሔርን ቅ፣ ፈቃድ እንፈጽም ዘንድ ግዴታ አለብን ፣ ይኸንንም ከጌታችን ከመምህራችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ተምረናል ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱን ፈቃድ እንጂ የእርሱን ፈቃድ ሊፈጽም እንዳልመጣ እንዲህ ሲል ይናገራል «እኔ ከሰማይ መጥቼለሁና የራሴን ፈቃድ ልፈጽም አይደለም ፤ ነገር ግን የላከኝን ፈቃድ እንጂ» (ዮሐ. ፮ . ፴፰) ። ክርስቶስ ይኸን መልእክት ሲያስተላልፍልን እኛም በመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ እንድንፈጽም፣ ከዚያም በኋላ የየግላችንን ሥራ እንድንከታተል የሚያመለክት ነው ። ሌላው ቀርቶ በሕማም ላይ እያለ እንኳን አባት ሆይ ይኸነን ጽዋዕ ከኔ አሳልፈው ፣ ነገር ግን ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደኔ ፈቃድ አይደለም ሲል እኛም በችግ



ርም እንኳን ብንሆን የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ እንዲፈጸም መናገርና መሥራት ተገቢያችን መሆኑን ያመለክታል (ሉቃ . ፳፪ . ፵፪) ።

ሰማያዊ አባታችን ፈቃዱ በሰማይ የተፈጸመ መሆኑን ተረዳን ፤እንዲሁ በምድር በእኛ ዘንድ ፈቃዱ እንዲፈጸም የልጅነታችንን ፍቅር ልናሳየው ልንገልጥለትም ይገባል ።

የልጅነታችን ምልክት የሚሆነው ፈቃዱን ስንፈጽም ፍሊጋውንም ስንከተል ነው ።

ከሁሉም በፊት የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ላይ ምንና ምን እንደሆነ ማወቅ እንደፈቃዱም መሥራት ተገቢያችን ነው ። «ወይኩን ፈቃድከ» የሚለው ጸሎት በምስጋናው ክፍል ያሉትን ፫ቱንም ጥያቄዎች የሚያጠቃልል የሚያገናኝም ነው ፣ ይኸውም «ይትቀደስ ስምከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር « ትምጻእ መንግሥትከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር »ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር » ሊል የሚያስችል ይሆናል ።



# ክፍል ፪ ልመና ፤

« ሲሳየነ ዘለለዕለትነ ሀበነ ዮም »(ማቴ.፮.፲፩)።
(የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ)

ለእግዚአብሔር ሊቀርብ የሚገባውን ምስጋና በመጠኑ ከአሳየ በኋላ እያንዳንዳችን ስለራሳችን እንዴት መጸለይ ፣ ምን መለመን እንዳለብን እንደሚከተለው ጌታችን ያሳያል ።

ልጆች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ለአባታቸው እንደ ሚነግሩ እንደሚጠይቁም እኛም የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን ሳናፍር ሳንፈራም የምንሻውን እንድንለምነው የሚያሻንን ሁሉ እንድንጠይቀው ያስተምረናል ። ባሕርይ እንስሳዊት በእኛ በሰውነታችን ይታያል ፣ ስለዚህ ምግብ ካጣ ሰውነታችን ይጎዳል ፣ መንቀሳቀስ ይሳነዋል ፣ ከአልበሉ ሬማ ከአፌ ለበሱ እንሰሳ የሚለው ትክክል አነጋገር ነው ፣ ስለዚህ ጌታ ሰውነታችንን ለመጠገን ሥጋዊ ምግብ ማስፈለጉን አውቆ ስለምግባችን እንድንለምነው አስተማረን ።

እንግዲህ ራሳችን የሚጸናበት ሕይዎታችን የሚጠበቅበት የዕለት ምግባችን ስለሆነ እርሱን በቀጥታ አባታችንን እንድንጠይቅ አሳየን ማለት

ነው ።የበሉትና የጠጡት ሁሉ ደም ይሆናል ፤ ነፍስም ደምን ተዋሕዳ ትኖራለች ፤ ስለዚህ ሰው ሁሉ ሕይዎትን አግኝቶ ይኖራል «እንበለ ሥጋ ኢትቀውም ነፍስ » የሚለው አነጋገር ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው ፤ ስለዚህ ለሕይዎታችን መደገፊያ የሚሆነውን ሥጋዊውን ሌላም አስፈላጊውን ሁሉ አባታችንን እንድንለምነው ያመለክታል ። ለሥጋችንም ለነፍሳችንም ጽንአትን የሚሰጠውን ሥጋዊውን መንፈሳዊውንም ምግብ እንዲሰጠን እንለምነው ዘንድ አዘዘን ሰው ከነፍስም ከሥጋም የተፈጠረ ነውና ።

ሰዎች እንደመሆናችን ሥጋዊ ምግብ በግድ ያስፈልገናል ፤ ያለዚያ ልንኖር ልንንቀሳቀስም ፈጽመን አንችልም ፤ ስለዚህ በየዕለቱ ምግባችንን ከአባታችን እንጠይቃለን ።

ወርቅ ብር ወይም ሌላ ትርፍ ነገር ለምሳሌ ስለጌጣጌጥ እንድንለምነው አላዘዘንም ፤ የዕለት ጎብስታችንን ስጠን ብሎ ስለምግብ ብቻ እንጂ፤ግን የሚያስፈልገን ይኸ ብቻ አይደለም ፤ ለሕይዎታችን የሚያስፈልጉን ነገሮች ብዙዎች ናቸው ፤ ሁኖም ሁሉም ነገር በዚሁ ውስጥ ተጠቃሎ ይገኛል ።





እነዚያን ሁሉ አጠቃሎ «ሲሳየነ» በማለት ተናገራቸው ፤ በየዕለቱም እነዚህን ሁሉ እንዲሰጠን ወደ አባታችን እንለምናለን ፤ ገልጠንም እንጠይቃለን ።

ምግባችን በማለት በብዙ ቁጥር ሲናገር አንድ ሰው ሁል ጊዜ ለቤቱለጎረቤቱ ፤ ለወገኑ ፤ለህገሩ፤ በጠቅላላም ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ችግር እንዳይደርስበት፤ምግብ እንዲኖረው ይመኛል ይጸልያልም፤ ምክንያቱም ሰው የተባለ ሁሉ የአንድ የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ አንድአካል አንድ ነፍስ ነውና ። ስለዚህ ግማሹ አካል ተመችቶት እየበላ ግማሹ አካል ሊንገላታ አይገባውምና፤ ማለት አንዱ እየበላ ሌላው ሊራብ ሊራቆት አይገባውምና ። «ዘመድ ቢረዳዳ ችግርም አይጎዳ» የተባለው በዚህ መንገድ ይፈጸማል፤ማለት አንዱ በጸሎት አንዱ በሀብት አንዱ በጉልበት ሲተሳሰብና ሲረዳዳ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ኑሮው ይቃናል አንድም ይሆናል ።

ለኛ የሚገባንን ለኛ ያልከውን የወሰንከውን ምግባችንን ስጠን በሉኝ አለ፤በዚህም ቃል የሰው የሆነውን ለኛም ያልታዘዘውን ያልተፈቀደውንም የኛ ገንዘብ ያልሆነውን ሁሉ እንዳንመኝ፤





እንዳንነካ የሚያስጠነቅቅ የሚያስገነዝብም ቃል ነው።

አንዱ የሌላውን ሀብት ንብረት በመመኘት ፈንታ የዕለት ምግብ ልብስ እንዲያገኝ ሲመኝለት ሌላውም ደግሞ ለእርሱ እንዲሁ ሲመኝለት ሲያስብለት ወንድማማችነት ፤ እኅትማማችነት በግልጥ ታወቀ፤ሰላም ፍቅር አንድነት በሰው መካከል ተመሠረተ ማለት ነው ።

እግዚአብሔር አምላክ ገንዘቡ አድርጎ ለእያንዳንዱ ያዘጋጀለት አለ ፤ ስለዚህ የእርሱ የሆነውን ማንም ሊነካበት አይችልም ፤በከንቱ ይመኝበታል እንጂ ። በዚህ ፈንታ ግን ለባልንጀራው በጎውን የተመኘለት የጸለየለት ፤ ለመርዳትም የተዘጋጀለት እንደሆነ እግዚአብሔርም እርሱን ለመርዳት ዝግጁ ይሆናል ።

ይኸ ጸሎታችን ፤ ይኸም መልካም ምኞታችን በየዕለቱና በየሰዓቱ እንደመሆኑ ፍቅራችን እየታደሰ ፤ ወንድሞቻችንን እኅቶቻችንን በየዕለቱና በየሰዓቱ እያሰብን በመኖራችን ችግር ሳያገኝን ልንኖር እንችላለን ማለት ነው ።

ሀ. «የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ» ስንል ግን በየዕለቱ ሳንሠራ እጃችንን አጣምረን ፤ እግራችንን ኮርትመን ተቀምጠን እየዋልን አይደለም





እየወጣን ፤ እየወረድን ፤ እየሠራን እንድንለምን ነው እንጂ ፤ እየሠሩ መጸለይ የሠራሁትን ባርክልኝ ፤ የደከምኩበትን ለኔ አድርግልኝ ፤ ድካሜ ከንቱ አይሁንብኝ እንደማለት ነው ። እግዚአብብሔር አምላክ ማንኛውንም ነገር ካልባረከ ፤ ቅዱስ ፈቃዱም ካላደረገው የቀረበውን እንጀራ እንኳን ለመብላት የሚችል የለም ።

እስራኤላዊያን በምድረ በዳ ሳሉ መና በየዕለቱ ከሰማይ ይወርድላቸው ነበር ፤ እስራኤላዊያንም የየዕለቱን ብቻ እንዲያስቡ ቢታዘዙ ከስስት የተነሣ የሁለትና የሦስት ቀን ምግብ የሚሆን እየሰበሰቡ ይዘው የሚገቡ ነበሩ ፤ ግን የአንዱ ዕለት እግዚአብሔር የፈቀደው ሲቀር ሌላው ይበላሽ ይትላ ይሸትም ነበር ፤ እግዚአብሔር አልፈቀደውምና ። ስለሰንበት ክብር ግን ዓርብ የሁለት ቀን እንዲሰበስቡ ስለተፈቀደ እርሱ አይበላሽም ነበር (ዘጸአ. ፲፮. ፬) ። አሁንም የዕለት እንጀራችንን ስጠን ብለን እንድንጸልይ ጌታ በእውነተኛ ቃሉ ያስተማረን የየዕለቱ ስለተፈቀደልን ያን እንድናገኝ ነው ።

የዕለት ምግብን ፤ ልብስን ፤ ሌላውንም አስፈላጊውን ሁሉ ሊሰጥ የሚችል እግዚአብሔር

ብቻ ስለሆነ ወደ እርሱ እንለምናለን ።

የዕለት እንጀራችንን ስጠን አለ እንጂ የወሩን የዓመቱን ስጠን አላለም ፤ ምክንያቱም የምንጸልየው በየዕለቱና በየሰዓቱ ስለሆነ የየዕለቱን ምግባችንን ልብሳችንን እንለምናለን እናገኛለንምና ፤ የየዕለቱንም ሁልጊዜ ከአገኘን የወሩንና የዓመቱን ትርፍ ማግኘት መጠበቅ ነው ፤ መሰብሰቡ ፤ መጠበቁ ድካሙ ትርፍ ነውና ። እግዚአብሔር አምላክ የማይረሳን ስለሆነ ፤ በየዕለቱና በየሰዓቱ ስንጸልይ ይሰማናል ስለዚህ የየዕለቱን ምግብ ይሰጠናል ፤ ጸሎቱ ግን መቋረጥ የሌለበት ነው ።

የዕለት ልብስ ፤ ጉርስ ከተገኘ ለሰው በቂ መሆኑን መጻሕፍት ተባብረው ደግፈውታል ፤ «ስለዚህ መብልና ልብስ ካገኘን ይበቃናል» ሲል ጳውሎስ ተናግሯል (፩ ጢሞ. ፮፡፰) ። ሰሎሞንም በምሳሌው «ከንቱንና አሰተኛ ነገርን ከኔ አርቃቸው ፤ ድኅነትንና ባለጸግነትንም አትስጠኝ ነገር ግን ብቻ ለአዳሬ የሚያሻኝን እንጀራ ሥራልኝ » ሲል ተናግሯል (ምሳሌ ፴፡፰) ። እንዲሁም ያዕቆብ «----የምበላውን እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ባገኝ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆናል ሲል ተናግሯል (ዘፍ. ፳፰፡፳) ፫፻፲፰ ሊቃውንትም በሕ





ንፃ መነኮሳት «----ዘእንበለ በአምጣነ ዘየአክል ለሕይዎትከ ወለሲሳይከ ወለአራዝከ በአቅም --» ብለዋል (ሃይ፡አበው፡ሕንፃ መነኮ መዕ፡፳፩፡ቁ ፩ ገጽ ፻፶፰ )። ማር ይስሐቅም እመቦ ዘተረፍከ እመፍቅደ ዕለትከ ሀቦ ለነዳይ «ሲል ተናግሯል (ማር፡ይሳ. ም፡፲፪፣።

ይኸም ሁሉ ምስክርነት የዕለት ምግብ ከአገኘን ሌላው ሁሉ ትርፍ መሆኑንና ለዚህም በየዕለቱ መሥራት በየዕለቱ መጸለይ ተገቢያችን መሆኑን የሚያመለክት የሚገልጥም እውነተኛ መመሪያ ነው ።

<u>**ሰ· የዕለት እንጀራችንን**</u> ፤ ሥጋውንና ደሙን ስጠን ሲል ነው፤በየዕለቱ የሚያሻንን፤መንፈሳዊ ምግባችንን ቅዱስ ፤ሥጋውንና ክቡር ደሙን ስጠን ። ለቅዱስ ቁርባን አብቃን ፤ ሥጋህን በልተን ደምህን ጠጥተን ለዘላለም ሕያዋን ሁነን እንድንኖር አድርገን ብለን እንድንጸልይ ሲገልጥልን ነው ። ያለዚህ መንፈሳዊ ምግብ ሥጋዊው ምግብ ብሆ ምንም ግዳጅ አይፈጽምምና ። መንፈሳዊው ምግብ ግን መንፈሳችን ያጠነክራል ፤ ለመንፈሳችን ሕይዎትን ይሰጣል ፤ ሥጋ ግን ምንም አይረባም አይጠቅምም (ዮሐ፡፮፡፷፫) ።





ሰው ከሥጋ የተወለደ ሥጋዊ ነው ፤ ስለዚህም ሥጋዊ ምግብ በየዕለቱ በየጊዜያቱ ያስፈልገዋል፤ ግዴታም ነው፤እንዲሁም ሰው ከመንፈስ የተወለደ እንደመሆኑ መንፈሳዊ ነው ፤ እንግዲያውስ መንፈሳዊ ምግብ በግድ በየዕለቱ ያስፈልገዋል ፤ ስለዚህ በየዕለቱ በየጊዜያቱ መንፈሳዊውን ምግብ ስጠን እያልን ሰማያዊውን አባታችንን መለመን አለብን ።

ሥጋዊ ምግብ በመመገባችን ፍጹም ሰው እንደሚያደርገንና ሰውነታችንን እደሚጠብቅ፤መንፈሳዊው ምግብም ለመንፈሳችን አጋዥ ይሆነናል ፤ ፍጹም መንፈሳዊያን ያደርገናል ከእግዚአብሔርም ጋር ያገናኘናል ያቀራርበናልም ።

ሥጋዊ ምግብ በየዕለቱ ለሥጋችን እንደሚያስፈልገን ስለዚህም ጊዜውን ጠብቀን እንደምንመገብ መንፈሳዊው ምግብ ለነፍሳችን በየዕለቱ ያስፈልጋታል፤ስለዚህ በየዕለቱ ማግኘት አለባት ። እግዚአብሔር የሥጋም የነፍስም ፈጣሪ እንደመሆኑ የሥጋንም የነፍስንም ምግብ ሠርቶልናል ፤ እኛም እንደአስፈላጊነቱ ጊዜውን ጠብቀን ሁለቱንም መመገብ ስላለብን ፤ ስለሁለቱ የዕለት ምግባችን መጸለይ አለብን ። ረሀብን አመ





ጣሁ ይላል ፤ይኸውም የሥጋ ረሀብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል አለመሰማት ነው ሲል መንፈሳዊው ረሀብ ከባድ መሆኑን ገልጦ ተናግሯል (አሞ፣ ፰. ፲፩) ። የነፍስ ምግቧ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት በእግዚአብሔር ፈቃድ መራመድ ነው፤ይኸም ከተጓደለባት ትራባለች ትጠማለች ።

ሥጋውን መብላት ደሙን መጠጣት ለእያንዳንዳችን በግድ አስፈላጊ ነው ፤ ጌታ ሲናገር «ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በኔ ይኖራል ፤ እኔም በእርሱ » ብሏል ( ዮሐ፣ ፮ ፣ ፶፭ — ፶፮ ) ።

በቅዳሴ ጊዜ ይኸው የጌታ ጸሎት በዝማሬ የሚጸለየው የቁርባንን ምግብነት ምሥጢርነትም ለመግለጥ ለማክበርም ነው ። ይኸ የጌታ ጸሎት ከተዘመረ በኋላ በቀጥታ ወደ ቁርባኑ እንሄዳለን ፤ በዚህም ጊዜ ካህኑ « ኅብስተ ሕይዎት ዘወረደ እም ሰማያት ክቡር ሥጋሁ ለክርስቶስ ፤ ብሎ መንፈሳዊ ምግብነቱን ገልጦ ይሰጣል ዘለዓለማዊ ሕይዎትን ሰጭነቱንም አስረድቶ ሁሉም ከዚህ እንዲካፈል ያደርጋል ።

በዕርግጥም ሥጋውን ደሙን ስንመገበው በኅ

ብስትና በወይን መልክ በምግብነት እንወስደዋለን፥ ሁኖም ሥጋዊ ምግብ ሳይሆን መንፈሳዊነቱን ማመን አለብን ፡ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነውና ። ይኸም ቍርባን ለነፍሳችን ጽንአትን ቅድስናን ይሰጣል ፡ በዚህ ጊዜም ሥጋችን ጽንአትን ያገኛል ።

## ሐ. የዕለት ምግባችን የእግዚአብሔር ቃል ነው ።

« ሰው በእንጀራው ብቻ አይኖርም ፡ ነገር ግን ከእግዚአብሔር አፍ በምትወጣው ሁሉ እንጂ» (ማቴ. ፬ ፡ ፬ ፤ ዘዳ ፡ ፰ ፡ ፫) ። ሥጋችን በየዕለቱ ምግብ ካላገኘ ሕይዎት አያገኝም ፡ የነፍስም ሞት የእግዚአብሔርን ቃል ካለመስማት የተነሣ ይሆና ልና ። በሰው ላይ ባሕርይ መልአካዊ ይታያል ፡ እርሱም ምግቡ የእግዚአብሔር ቃል የሆነ መንፈ ሳዊ ምግብ ነው ፡ ይኸን ካጣ ግን ይጐዳል ፡ ስለ ዚህ በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት አለ በት ።

ለነፍስ ምግብ የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ከጠፋ ለሰው ልጅ ሁሉ ሕይዎት ሊኖረው አይች



ልም ፤ ስለዚህ የዕለት መንፈሳዊ ምግብ ማግኘት ስላለበት የዕለት ምግባችንን ስጠን ለዛሬ ሲል ይለ ምናል ። ለሰው ከባድ ረሀብ ሆኖ የሚገኘው መንፈ ሳዊው ምግብ ቃለ እግዚአብሔር ሲጠፋ ነው ፤ መን ፈሳዊ ምግብ የእግዚአብሔር ቃል ከጠፋ ሥጋዊውን ምግብ ቢመገቡ አያጠግብም ረድኤት የለውምና እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ በአሞጽ አድሮ በሀ ገር ላይ ትልቅ ረሀብን አመጣለሁ ይላል ይኸውም የሥጋ ረሀብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል አለመ ስማት ነው ሲል መንፈሰዊው ረሀብ ከባድ መሆ ኑን ገልጦ ተናግሯል (አሞ. ፰. ፲፩) ። የነፍስ ምግቧ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ፤ በእግዚአብሔርም ፈቃድ መራመድ ነው ፤ ይኸም ከተጓደለባት ትራ ባለች ፤ ትጠማለች ።

እውነተኛ ሕይዎትን የሚሰጠው የነፍስ ምግብ ሁል ጊዜ በቤተ ክርስቲያን የሚሰበከው ከቅዳሴውም አንድ አካል የሆነው ሊለይም የማይገባው የእግዚ አብሔር ቃል ነው ፤ ስለዚህ በየዕለቱ በቅዳሴ ጊዜ ቍርባኑን ተቀብሎ የእግዚአብሔርንም ቃል ሰምቶ መዋል ለክርስቲያን ሁሉ አስፈላጊ ነው ። 



## ፮. ይቅር በለን ፡

«ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅ ድግ ለዘአበሰ ለነ» (ማቴ ፡ ፮ ፡ ፲፪) ። (በደላችን ተውልን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል) ። በጥንተ አብሶ የበደልነውን ሁሉ ጌታ በጥምቀት አስተሥርዮልናል ፡ ነገር ግን ከዚያ በኋላ በየጊዜው የምንሠራውን ለማስተሥረይ እኛ የበደሉንን ሁሉ ይቅር እንደምንል አንተም እኛን ይቅር በለን እያልን እንድንጸልይ ያስተምረናል ። ይኸ ቃል እኛ ራሳችን ይቅር ባዮች የይቅርታም ሰዎች ሁነን እንድንገኝ የሚያመልክት ነው ፡ ስለዚህ እኛ አስቀድመን የተጣሉንን የበደሉንንም ሁሉ ከልብ ይቅር እንድ ንል ግዴታችን ነው ፡ ከዚያ በኋላ ሁሉን ይቅር በማለት ወደታመነው አምላክ እንድንቀርብና ይቅ ርታም እንድንጠይቅ ያስገነዝበናል ።

በሰዎች መካከል ትንሽ ነው ፡ ትልቅ ነው ፤ ሳንል የተጣላነውን ሁሉ ሁልጊዜ ይቅር እንደ ምንል ሁልጊዜ የይቅርታ ሰዎች እንደመሆናችን ስናውቅ ሰይጣን አገብሮን በድፍረት ፤ ሳናውቅም በስሕተት ከምንሠራው በደል ሁሉ አንተም ይቅር በለን ማለት አለብን ።

የኛ ይቅር ማለት፥ይቅርታም ማድረግ ያጠራጥር





ይሆናል፥ምክንያቱም ራሳችንን ለይቅርታ አላዘጋ ጀንምና ፡ አምላክ ግን አንድ ሰው ይቅር ብሎ ይቅ ርታም አድርጎ ከቀረበለት ቸል ሳይል ይቅርታ ልማዱ ስለሆነ ሁሉንም ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ነው ፡ የእርሱ ቅዱስ ፈቃድ ሁሉም ይድን ዘንድ ነውና ።

እኛ ለሰዎች መልካሙን ብንመኝ፥ በጐውንም ብንሠራ ለሰዎች ይቅርታን ብናደርግ አምላክ ለእ ኛም መልካሙንና የተሻለውን ያደርግልናል ፡ ከበ ደላችንም ያነፃናል ።

ሁልጊዜ ኃጢአት እየሠራን እየበደልን ጻድቅ መስለን ዝም ብለን ልንቀመጥ አይገባንም ፤ ወይም ይቅር ሳንል ፈጣሪያችንን ይቅርታ ልንጠይቀው አንችልም ፤ ወይም ኃጢአት አንሠራም ፤ በደልም የለብንም ብለን ራሳችንን ልናታልል አይገባንም ምክንያቱም አንድ ሰው በአንዲት ዕለት ብዙ ሳይ በድል አይውልምና ፡ ይኸንም በደል የለብኝም የሚለውን ቃል ወንጌላዊው ዮሐንስ « ኃጢአት የለብንም ብንል እኛ ራሳችንን እናስታለን ፡ እውነ ትም የለንም » ሲል ይወቅሳል (ዮሐ፡ ፩ ፡ ፰) ።

ይቅር ብለንም ይቅርታን ብንጠይቅ ይቅርታን እንደሚያደርግልን ራሱ ክርስቶስ ተናግሮናል ።

ግን ሁል ጊዜ እየበደልን ይቅርታን ሳናገኝ እንኖራ ለን ማለት ደግሞ በራስ ላይ መፍረድ ነው ፥ ስለዚህ እኛ ይቅር ስንል እርሱም ይቅር እንደሚለን አምነን አስቀድመን እኛ የበደሉንን ይቅር እንበል ።

እኛ ሰዎች ስንሆንሰውን ማስቀየማችን ፥ ከወን ድማችን ጋር መጣላችን ራሱ በደል ነው ፤ የባሰ ውን ደግሞ ይቅርታ ሳያደርግ እግዚአብሔርን ይቅ ርታ መጠየቅ የበደል በደል ነው ፤ ስለዚህ እኛ አስቀድመን የበደሉንን ሁሉ ይቅር ማለት፤ይቅርታ ማድረግ ተገቢ ነው ፥ከዚያ በኋላ እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል ይቅር በለን፤ብለን እንጸልያለን ይቅርታም እናገኛለን ።

እንግዲህ ይቅርታ ያለው ከኛ ከራሳችን ነው ፣ ይቅር ብንል ይቅር እንባላለንና ፥ ይቅርም ካላልን ግን ይቅር አንባልምና ። ከዚህ ጸሎት መጨረሻ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር «ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማይ አባታችሁ ደግሞ ይቅር ይላችኋል ፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም» ብሏል (ማቴ ፥ ፮ ፥ ፲፬—፲፭) ።

ቂምን በቀልን በመያዝ ልቦናችንን ልናጸናው አይገባንም እንግዲያውስ ይኽን ጸሎት በጸለይን





ጊዜ የበደሉንን ሁሉ ይቅር እንድንልና ከሰማዩ አባ ታችን ይቅርታ እንድናገኝ ያስገነዝበናል ።

በየዕለቱ በየሰዓቱ ይኽን ጸሎት እየጸለየ ይቅር የማይል ሰው ከእግዚአብሔር ይቅርታን የማያገኝ ፍርዱ በራሱ ነው ፥ ማለት እርሱ ይቅር ስለማይል እግዚአብሔርም እርሱን ይቅር አይለውም ፥ ይቅ ርታም አያደርግለትም

እንግዲያውስ ጸሎት ከማድረጋችን፤ቊርባንንም ከማቅረባችን በፊት የተጣላን ፥ ወይም እኛ የተጣ ላነው እንዳለ ማሰብ አለብን፤በዚህን ጊዜ ቁርባኑንም ጸሎቱንም አቆይቶ ሂዶ የተጣሉትን ይቅር ማለት ከዚያ በኋላ ተገኝ[ኸ]ነትን ለመግለጥ ወደ እግዚአብሔር መብዓውንና ቊርባኑን ማቅረብ ፥ ጸሎት መጸለይ ይገባል ። ያለዚያ የተጣሉት ሰው በዳኛ ይከሳል ያስቀጣል በዚህም ምክንያት የኑሮ ጸጥታ ማጣት የንብረት መባከን ይፈጠራል፤ ይኽ በምድራዊ ሕይ ወታችን የሚገጥመን ችግር ሲሆን ፤ በሰማያዊ ሕይወታችን ደግሞ እኛ የበደሉንን ይቅር እንዳላ ልናቸው ሰማያዊዩ አባታችን እኛንም ይቅር አይለ ንም ፤ ፈጽሞ ይቅርታ የለንም ማለት ነው (ማቴ ። ፭ ፥ ፳፫—፳፮) ። እንግዲያውስ በበደል እያለን እን ዴት ንጹሑን አምላክ አባታችን ልንለው እንችላ ለን ! ስለዚህ ይቅር እንድንባል ይቅር እንበል ።





እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ስለሆነ ከቂም ከበቀል ንጹሕ ሁነን ከቀረብን እርሱ ደግሞ ከበ ደል ሁሉ ያነፃናል። ወደርሱ ንጹሕ ሁነን እንቅረብ ፤ የእርሱ ልጆች ነንና ።

ይኽን ጸሎት ከልባችን የምንጸልየው ከሆነ ይኽን ቂም ነገር እንዲሁ ልናልፈው አንችልም ፤ በቂም በበቀል ሁነን ልንጸልይ ስሙንም ልንጠራው አይገባንም ነበር ፥ ነገር ግን እንዲሁ የምንገዴ ከሠ ጸለያችን የተነሣ ይኽን ሁሉ ልናስታውስ አንችልም አባታችን እግዚአብሔር የሰላምና የይቅርታ አምላክ እንደመሆኑ እኛም ልጆቹ ይቅር ባዮች ሁነን መገኘት አለብን ።

## ፫. ወደ ፈተና አታግባን ፡

«ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድ ኅነነ ወባልሐነ እምኩሉ ዕኩይ » (ማቴ ፥ ፮፡፲፫) (ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ) ።

አባታችን እግዚአብሔር ጠባቂያችን ስለሆነ ወደልዩ ልዩ ፈተና ወደ ሰይጣንም ወጥመድ እንዳ ንገባ ጠብቀን ስንል እንድንለምነው ያስተምረ ናል ፥ ወደ ፈተናም እንዳንገባ ያስጠነቅቀናል ፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ካልተለየን በቀር ወደ ፈተና





አንገባም ፥ እግዚአብሔርም አሳልፎ ለፈተና አይ ሰጠንምና ።

ሀ. ፈታኙ ማነው ? እግዚአብሔር ፈታኝ አይ ደለም ፥ ማንም እንዲፈተን እርሱ አይፈቅድምና (ያዕ ፥ ፩ ፥ ፲፫ ) ። ፈታኙ ሁል ጊዜ ጠላታችን ሰይ ጣን ብቻ ነው ፤ በሰይጣን ፈተና ወጥመድ የሰው ልጅ እንዳይገባ መጠንቀቅ መጸለይም አለበት ። ሰልፋችን ውጊያችንም ከሰው ጋር ሳይሆን ከጨለ ማው ገዥ ከሰይጣን ጋር ነው እንጂ፤ ቅ ። ጳውሎስ እንደተናገረው « መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር ፥ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» ( ኤፌ ። ፮ ። ፲፪ ) ።

ዲያብሎስ የሥጋን ፈቃድና ምኞት በማነ ሳሣት ሰውን ይፈትናል ፥ እንኳን ሰውን ክርስቶስ ንም በልዩ ልዩ ፈተና ፈትኖታል (ማቴ ፥ ፬፥፫—፲)። ሆኖም ክርስቶስ በፈተናው አልተቸነፈም በመጣበት አቅጣጫ ሁሉ ድል ነሣው እንጂ ፥ ማለት በሦስቱም አርእስተ ኃጣውእ ድል ነሥቶታል ፤ በስስት ቢመጣ በት በትዕግሥት ፥ በፍቅረ ንዋይ ቢመጣበት በጸሊአ ንዋይ ፥ በትዕቢት ቢመጣበት በትሕትና ድል ነሥ ቶታል ።

ዲያብሎስ አስቀድሞ የሰው ነገድ አባትና እናት የሆኑትን አዳምንና ሔዋንን ተፈታትኗቸዋል ፤ እነርሱ ግን በፈተናው ወድቀዋል ፤ ለፈቃዱም ተገዝተዋል ፤ ስለዚህም ከሚወዳቸው ጌታቸው ለይቷቸዋል ፤ ከመልካሟ ቦታቸው ከገነት አውጥቷቸዋል ( ዘፍ ・ ፫ ・ ፳፪—፳፬ ) ። እንግዲህ እኛም ሰይጣን ኃይል አግኝቶ እንዳይበረታብን ኃይሉን አድክምልን፣ መርዙን አልጫ አድርግልን ብሎ እንደመጸለይ ነው ።

ለሰይጣን መብትና ኃይል አትስጠው ፤ በእኛ ላይም ይሠለጥን ዘንድ ፈቃድ አትስጠው ፥ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰይጣን ሊፈታተነን አይችልምና ። ኢዮብን ሲያስት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየጠየቀ እንደሆነ ተረድተናልና(ኢዮብ ፩፡፮—፲፱)።

እንግዲህ ሰይጣን ለሰው ልጅ አይተኛም፥ ሁልጊዜ የእርሱ ፈቃድ ታዛዥ ለማድረግ ይጥራል፤ ለሰው ክፉ ጠላት ነው ፤ ሁኖም በስንፍና በደካምነት መንፈስ ሲያገኝ ድል ሊያደርገን ፥ ሊማርከን ይችላል እንጂ ነቅተን ተግተን ከኖርን ፤ በጸሎትም ጽሙዳን ከሆን ድል እናደርገዋለን እንጂ ድል አያደርገንም ። አንድ አውሬ አዳኝ ወይም ዓሣ





አጥማጅ የሆነ ሰው ሥራው ስለሆነ ዓሣው እንዴት እንደሚያዝ ምን ጊዜ እንደሚገኝ ያውቀዋል ፤ ያን ጊዜም ለማጥመድ ተግቶ ነቅቶ ይጠብቃል ። አውሬ አዳኙም አውሬው እንዴት የት እንደሚገኝ ያውቃል በዚህም መሠረት ያድናል ፤ ስለዚህም ሁልጊዜ እንዳሳማው ሲፈጽም ይገኛል ። ሰይጣንም የሰው ልጅ የሚጠመድበትን ጊዜ ፥ ቦታ ፥ ሁናቴ ያውቃል ፥ በዚያም በሚያመቸው ጊዜ አሽከላውን ይዘረጋል ተግቶም ሰውን ያጠምዳል ፤ ከዚያ ለማምለጥ ግን የሰው ልጅ ሁሉ መጸለይ ያስፈልገዋል ለፈተናም አለመጋለጥ ነቅቶ ተግቶ መኖር ተገቢ ነው ።

ለ/ ፈተና ኃጢአት አለመሆኑ ፥ ፈተና እንዲሁ በድንገት በማንኛውም ሰው ላይ ይደርሳል ፤ ስለዚህም በጻድቃንም ላይ ሳይቀር ይደርሳል ፤ እንዲያውም ፈተናው በቅዱሳን ላይ የበዛ የጸናም ይሆናል ፥ ነገር ግን እነርሱም ታጥቀው ሰይጣንን ስለሚዋጉት በፈተናው አይወድቁለትም በአሸናፊነት ይገኛሉ እንጂ ። ነቢዩ ዳዊት ስለዚህ ሲናገር «የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው ፥ እግዚአብሔር ከሁሉም ያድናቸዋል» ብሏል (መዝ ፡ ፴፬ ፡ ፲፱) ። ስለዚህ መፈተን ኃጢአት አይደለም ፤ እንዲያውም





ተፈትነው የወጡ ብቻ ናቸው ዋጋ ያላቸው ፤ ከፍተኛ ዋጋ ለማግኘት ማንኛውም ክርስቲያን በግድ መፈተን ያስፈልገዋል ፥ ነገር ግን በፈተናው የወደቁ ለሰይጣንም የታዘዙ እንደሆን በአንፃሩ ከፍተኛ ፍዳ ያገኛቸዋል ።

ወርቅ በእሳት ካልተፈተነ ግብዙና ጽሩዩ ተለይቶ አይታወቅም፤ ስለዚህ ሁልጊዜ ወርቅ በእሳት ይፈተናል ፥ ንጥሮም ይወጣል ። ጻድቅም የጽድቁ ውጤት የሚታወቀው በልዩ ልዩ መከራ ተፈትኖ አልፎ የወጣ እንደሆን ነው ። ጻድቃን ፥ ሰማዕታት ሁሉ በመከራ ተፈትነው አልፈው የአሸናፊነት የክብር አክሊል ለማግኘት ይችላሉ ። ክርስቲያንን ሁሉ በመጠኑም ቢሆን ይኸ ዕድል ይጠብቃቸዋል ፥ ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያን በደረሰበት መከራ ችግር ሳይመረር ችግሩን ሳይቆጥር በምስጋና ይቀበለዋል ፥ በትክክልም ፈተናውን ያልፋል ፥ የክብር አክሊልም ይቀዳጃል ። «ዝናብ ባይመጣ ሁሉ ቤት ፤ እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሴት» እንደሚባለው ፈተና ባይኖር ሁሉም ክርስቲያን ነው ፥ ሁሉም ጻድቅ ነው ፥ ነገር ግን እውነተኛው ክርስቲያን የሚለየው በፈተና ጊዜ ነው ፥ ማለት ፤ ችግር መከራ ሲመጣ በእግዚአብሔር ስም በምስጋና ተቀብለው የሚያ





ሳልፉ አሉ ፥ በፈተናው ተመርረው ደግሞ የሚወድቁ አሉና ።

ፈተና የሚደርስበት ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጅ እንደሆነ ይታወቃል ፥ ይኸውም ሰይጣን የሚፈትነው የሚዋጋውም ጽድቁን ትሩፋቱን አይቶ ነው ፥ ለምሳሌ ኢዮብን እንመልከት ። ኢዮብ ጻድቅ ሰው እንደነበር የእግዚአብሔርን ፍለጋ ይከተል እንደነበር እግዚአብሔር አምላክ ራሱ እንዲህ ሲል መስክሮለታል « እግዚአብሔርም ሰይጣንን በውኑ ባሪያየ ኢዮብን ተመለከትከውን ? በምድር ላይ እንደርሱ ፍጹም ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ፥ ከክፉትም የራቀ ሰው የለም አለው « (ኢዮ. ፩ ፥ ፰) ። ነገር ግን በእርሱ ላይ በዓይነታቸው በብዛታቸው የተለያዩ መከራዎች ደርሰውበታል፥ሰይጣን ተመላልሶ ፈትኖታልና (ኢዮ. ፩ ፡ ፲፩ — ፳፪ ፤ ፪. ፩ — ፱ ) ። ሁኖም እርሱ ደግሞ እስከ መጨረሻ የታገሠ ስለሆነ ሰይጣንን አሸንፏል ፥ ስለዚህም የድል አክሊልን አግኝቷል ፥ ማለት የጠፋው ሁሉ ተመልሶለታል ለትዕግሥት ምሳሌ ሁኖ እስካሁን ይነገርለታል ( ኢዮ ፡ ፵፪ ፡ ፲—፲፯ ) ።

የተፈተነው ሰው እግዚአብሔርን እንደሚያ መሰግነው እንደሚያስደስትም ጦቢት ተናግሯል ( ጦቢት ፤ ፲፫ ፤ ፲፫ ፤) ። ፈተና መከራም የሚደ ርስበትና የሚታገሥ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ብፁዕ እንደሚባል ቅ ፤ ማቴዎስ ነግሮናል (ማቴ. ፭ ፤ ፲ ) ።

ይኸንም ስላልን በሌብነቱ በወንጀለኛነቱ መከራን የሚቀበል ፤ ልዩ ልዩ ችግር የሚደርስበት እንዳለ የታወቀ ነው ፤ የክርስቲያን ፈተና መከራ ግን ከዚህ ይኸን ከመሰለው ሁሉ የተለየ ነው ። እንደ ክፉ ሥራው ክፉ ቢደርስበት የሥራውን ዋጋ አገኘ ይባላል እንጂ ፈተና ደረሰበት አይባልም፤ ክርስቲያን ግን በክርስቲያንነቱ ብቻ ሰይጣን ፈተና አምጥቶበት የሚያሠቃየው ለክብር ስለሆነ በደ ስታ ሊቀበለው ይገባል ፤ ፈተናም የሚባለው ይኸ ዓይነቱ መከራ ነው ። ይኸንም ዓይነት መከራ ቅዱስ ጴጥሮስ በመግለጥ እንዲህ ሲል ይነግረ ናል « ከናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚ ገባ ሁኖ መከራን አይቀበል ። ክርስቲያን እንደመ መሆኑ ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአ





ብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር » (፩ ፤ ጴጥ፤ ፬ ፤ ፲፭) ።

አሁንም ሳያጠፉ ወደ ፈተና የሚወድቁ ሁሉ የእግዚአብሔር ወዳጆች እንደሆኑ አያጠራጥርም ሰይጣን ራሱ የወደቁለትን አይፈትናቸውምና ።

ሐ. ፈተናውን ማለፍ ፤ ወደ ፈተና አታግባን እያልን እንጸልያለን እንጂ ወደፈተና መግባት ግድ ይሆንብናል ፤ፈተና በግድ ይመጣልና «ወዮ ለዓለም ስለማሰናከያ፤ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና..... .......» ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል (ማቴ. ፲፰ ፤ ፯ ) ። ፈተና ሳያስቡት ባልታወቀ መንገድ በግድ ይመጣል ፤ ምክንያቱም መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ብዙ ፃዕርና ጭንቅ ያስፈልጋልና (የሐ. ሥራ . ፲፬ . ፳፪ ) ።

ሐዋርያው ያዕቆብ ፈተና በግድ እንደሚመ ጣብን ያንንም ፈተና በትዕግሥት መቀበል እንዳ ለብን እንዲህ ሲል ያስተምረናል « ወንድሞቼ ሆይ ልዩ ልዩ ፈተና በደረሰባችሁ ጊዜ በደስታ ሁሉ ቁጠሩት » ( ያዕ . ፩ ፤ ፪ ) ። እያንዳንዱ የሚፈተ ነው ከፍተኛ ዋጋን ለማግኘት ስለሆነ ማንኛውም ሰው በደስታ መቀበል አለበት ። አንድ ጐበዝ ሰው





ጦርነት ገብቶ ችግሩን መከራውን ተጋፍጦ ድል አድርጎ የወጣ እንደሆነ ይመሰገናል ይሸለማል ፤ የጐ በዝ ቀን የሚባል አለና ፤ ያለዚያ የሸሸ ፤ ወይም እጁን ለጠላት የሰጠ እንደሆነ የሁሉ መዘበቻ ይሆ ናል ።

ፈተናም ሲደርስበት በምስጋና የሚቀበል ሁሉ ብፁዕ ነው ፤ ከፈተና በኋላ የሕይዎት አክሊል ይወ ስዳልና ፤ እግዚአብሔርን ለሚወዱት ተስፋ ያስደ ረገውን (ያዕ ፤ ፩ ፤ ፲፪ ) ።

ብዙው ሰው ሠራተኛን አድክሞ ብዙም አሠርቶ ተገቢውን ዋጋ ይከለክለዋል ፤ እግዚአብሔር አም ላክ ግን ለሁሉ የድካሙን ዋጋ ከፋይ ስለሆነ በስሙ መከራን የተቀበሉትን ሁሉ ዋጋቸውን ይከፍላል ፤ ማለት ላለቀሱት ዕንባቸውን የሚያብስላቸው እርሱ ነው ፤ በኋላም የድል አድራጊነት አክሊልን የሚያ ቀዳጃቸው እርሱ ነው ።

አንድ ጻድቅ ሰው ፈተና በገጠመው ጊዜ እግዚ ዚአብሔር በጸጋው እንደጐበኘው መቁጠር አለበት፤ ምክንያቱም ፍሬ ከሌለበት ባዶ ዛፍ ላይ ወፎች እንዳ ይብላሉ ፍሬ ትሩፋትም በሌለው ሰው ላይም አጋ ንንት አይረባረቡበትም ፤ ችግርም አይገጥመውም። ማንኛውንም ዓለማዊ ሰው ፈተና አያገኘውም ፤





ሃይማኖቱን ያጸና፤ምግባሩን ያቀና፤ትሩፋትን የሠራ እንደሆነ ግን ፈተና ይገጥመዋል ፤ ሰልፍ ፤ ውጊያ ይኖርበታል።ብዙዎች ጻድቆች ፈተና ሲመጣባቸው ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያገኙበት ስለሚያውቁ በደስታ ይቀበሉታል ፤ ለምሳሌ ሐዋርያትን እንመልከት ፤ ሐዋርያት የክርስቶስን ስም እንዳያነሱ ፈሪሳውያን አስጠንቅቀው ገርፈው ሲያስወጧቸው እየተደሰቱ ወጡ ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷቸዋልና (የሐ ፤ ሥራ. ፭ ፤ ፵ — ፵፩ ) ።

በዚህም መልክ እውነተኛ ክርስቲያን ከሆነ ፈተና የማይደርስበት ችግር የማይመጣበት ሊኖር አይችልም ፤ ታዲያ « ወደ ፈተና አታግባን » የሚ ለው ቃል ደንበኛውን ትርጉም እንዴት ሊያገኝ ይችላል ?

ነገሩን በትክክል የተመለከትን እንደሆን ፤ አንድ እውነተኛ ሰው በሚኖርበት በዚህ ምድራዊ ሕይዎት ችግር መከራ አይደርስበትም ማለት አይ ቻልም ፤ ይኸ ዓለም ራሱ የመከራ የሕማም ዓለም ነውና ( ኢዮ ፤ ፯ ፤ ፩ ) ፤ ስለዚህ ሁሉም ይፈተናል ፤ በተለይ ግን የቅዱሳን ፈተናቸው ብዙ ነው ፤ እነ ርሱ ግን በትክክል ይወጡታል ።

አንዳንድ ሰዎች ሐሰተኞች ፤ ሌቦች ሁነው

በምድር ተደላድለው ተቀማጥለው የሚኖሩ ፈተና
የማያገኛቸው ይገኛሉ ፣ እንዲያውም እንዲህ ያለው
ሰው በታየ ጊዜ ባላዋቂዎች ዘንድ እግዚአብሔር
ሳይቀር የሚወድለት እንደሆን ይነገርለታል ፤ ግን
እውነቱን ሲናገሩ ጠላት ይበዛል፣ፈተናው ይከተላል፣
ይኽን በመፍራት በሐሰት ጸንተው የሚኖሩ ብዙዎች
ናቸው ፤ አባቶችም ይኽንን አውቀው « እውነቱን
ተናግረህ ከመሸብህ እደር » ይላሉ ፤ ይኽንም የሚ
ሉበት ምክንያት እውነት ከተናገርህ በእውነት
ከሠራህ ጠላት ይነሣብሃል ፣ ማደሪያም ታጣለህ
ማለት ነው ።

«ወደ ፈተና አታግባን » የሚለው ቃል ስለ
ጽድቅ ብለን በምንሠራው ሁሉ ፈተና ቢደርስብን
በፈተናው እንዳንወድቅ አንተ ርዳን ፣ ከድቀት አድ
ነን ፣ ወደ ፈተና እንደገባን አንቅር አውጣን ማለት
ነው ። የዚህን ዓለም ፈተና እየፈሩ በኃጢአት የሚ
ወድቁ ብዙዎች ናቸው ፣ እኛም እንደነዚያ እንዳ
ንወድቅ አንተ ርዳን ፣ አድነንም ማለት ነው ።

መንፈስ ብርቱ ሲሆን ሥጋ ግን ደካማ ነው ፣
ስለዚህ ሰው የጊዜውን በመመልከት ቀዋሚው ሕይ
ዎት ያመልጠዋል ( ማቴ . ፳፮ ፣ ፵፩ ) ።

ሁልጊዜ የሚታገለውን ጻድቅ ሁሉ የእግዚ





አብሔር ጸጋ አይለየውም ፣ ስለዚህም በፈተናው
ድል ያደርጋል ፣ ያቸንፋል ፣ እንግዲህ «ወደፈተና
አታግባን » ማለት ከገባነው ፈተና አንተ ረዳታ
ችን ሁን ፣ አታጋልጠን ፤ ጸጋህን አትንሣን ፤ ኃይ
ልህን ስጠን ብሎ እንደመለመን ነው ። የእግዚአ
ብሔር ጸጋ ካልተጨመረልን በትግላችን ብቻ
ጠላታችን ሰይጣንን ድል ልንነሣው አንችልም የእ
ግዚአብሔር ጸጋ እንዲጨመርልን ደግሞ «ወደፈተና
አታግባን » እያልን መጸለይ አለብን።

ከሁሉ በፊት እግዚአብሔር አምላክ የማንች
ለውን ፈተና ከቶ አያመጣብንም ፣ የምንችለውን
እንጂ፣ ይኽን ደህና አድርገን ማወቅ አለብን ፣ ስለ
ዚህም ነገር ቅ ፣ ጳውሎስ ያስረዳናል « ሌላ ፈተና
አላገኛችሁም እንደ ሰው ያለ ፈተና እንጂ ፤ እግዚ
አብሔር ግን እውነተኛ ነው አይተዋችሁም ትፈ
ተኑ ዘንድ በማትችሉት ። ነገር ግን ከፈተናችሁ
መውጫውን ያደርግላችኋል ትታገሡ ዘንድ እንድ
ትችሉ » ( ፩ ፣ ቆሮ ፣ ፲ ፣ ፲፫) ።

መቼም ቢሆን ፈተና የደረሰበት ሰው በቶሎ
ወደጸሎት ማዘንበል አለበት ፣ እግዚአብሔር ኃይ
ሉን ይሰጠውና ይችል ዘንድ ፣ በዚህን ጊዜ ፈተ
ናውን ያልፋል በድል አድራጊነት ይገለጣል ፣የድል





አድራጊነትም አክሊል ይቀዳጃል ።

ቅ. ሐዋርያት ከጌታ ጋር በባሕር ሲጓዙ
ድንገት ማዕበል ተነሣ ፣ ሞገድም በረታ ፣ መርከ
ቡን በኃይል መታው ፣ ወደመስጠም መቃረባቸ
ውን በተረዱ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ወደመምህራቸው
ሂዱና ችግራቸውን ነገሩ ፣ ይኽም እንደ ጸሎት
የሚቆጠር ነው ። ዛሬም የዚህ ዓለም ማዕበልና
ሞገድ ሲነሣብን ለጌታ ብቻ መንገር አለብን፤ የዚያን
ጊዜው ኢየሱስ ክርስቶስ የዛሬውም እርሱው ነውና።
ያን ጊዜ ነፋሱን የገሠጸው ማዕበሉን ጸጥ ያደረገው
ዛሬም ፍጹም ኃይል መለኮታዊ ሥልጣን ገንዘቡ
የሆነው አምላክ እኛን ለማዳን ዝግጁ ነው ( ማቴ፣
፰ ፣ ፳፫ ) ።

ለፈተና ሁሉ መመከቻ ጋሻው ጸሎት ነው ፡
ጸጥታ ማግኛው ወደባችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ነው ፣ እርሱም « ጸልዩ ትጉም ወደመከራ እን
ዳትገቡ » ሲል ያስጠነቅቃል ( ማቴ ፣ ፳፮ ፣ ፵፩) ።

በፈተና ጊዜ በመታገሣችን ዋጋ እንደምናገኝ
በመመረራችንና ከዚያ ለማምለጥ በመጣራችን ዋጋ
እንደምናጣ በቅ ፣ ጳውሎስ ሁኔታ ልንረዳው እንች
ላለን ። ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቶስ ታማኝ ሐዋርያ
ብዙዎችን በሽተኞች የሚፈውስ ሲሆን በእርሱ ላይ





አሰቃቂ በሽታ ነበረበት ፣ ከዚያም ለመላቀቅ ግብር
ገብቶ ነበር ፤ ግን ያገኘው መልስ እንግዲያውስ
ጸጋዬም ይበቃሃል የሚል ነበር ( ፪ ፣ ቆሮ ፣ ፲፪ ፣ ፯
— ፱ ) ። ስለዚህ ፈተና ሲደርስብን እንታገሥ ።
ግን አጥብቀን እንጸልይ ። አሁን የምንጸልየው ፤

ሀ . ፈተና በደረሰብን ጊዜ በትዕግሥት ለማሳ
ለፍ እግዚአብሔር እንዲያስችለን

ለ. ፈተና እንዳንገባ በዚያውም ወድቀን ተቸን
ፈን እንዳንቀር በአቸናፊነት በድል አድራጊነት
እንድንወጣ ኃይሉን ጽንአቱን እንዲሰጠን ነው ።

## ፬ አድነን ፡

«አላ አድኅነነ ወባልሐነ ዕምኩሉ እኩይ »(ከክፉ
አድነን እንጂ) ።

የማዳን ኃይል ፈቃድም ያለው እግዚአብሔር
አምላክ ብቻ ነውና አድነን ስንል በአባትነቱ ተዝ
ናንተን እንለምናለን ።

ወደማንም ቢጠጉ በማንም ቢመኩ ከቶ ከእ
ግዚአብሔር በቀር የሚያድን የለም ፣ እርሱ ሲፈ
ቅድ እርሱም ሲወድ ግን ለድኅነታችን ብዙ ምክ
ንያት ይኖራል ስለዚህ ወደ እርሱ ብቻ መቅረብ
እርሱንም ብቻ መማጸን አድነን ብሎ መለመን
ተገቢ ነው ። እግዚአብሔር ሁሉ ይድን ዘንድ

ፈቃዱ የሆነ አምላክ ነው ፤ ለድኅነታችን ብዙ
ምክንያቶችን አዘጋጅቶልናል ፤ ልንድን ከፈቀድን
ለመዳን እንችላለን ።

ከክፉ አድነን ስንል እንድንጸልይ አዞናል ፤
ግን ክፉ የሚባለው ምን ነው ፣ ወይስ የትኛው ነገር
ነው ? ይኸን ጥያቄ ሁል ጊዜ ይኸን ጸሎት ስንጸልይ
እናስበው ይሆናል ፣ መልሱ ግን ብዙ ስለሆነ እንደ
ሚከተለው እንመልከት ።

ሀ፥ የክፉ ነገር ሁሉ ምንጭ መነሻም የሆነው ዲያ
ብሎስ ነው ፣ ፈታኙ እርሱ ነውና ፣ ክፉው ነገር
ሁሉ የሚመነጨው ከእርሱ ነውና ። ጌታን ሳይቀር
የፈተነው እርሱ ነውና ( ማቴ ፣ ፬ ፣ ፩ — ፲፩) ።
ስለዚህም ከዲያብሎስ ምክር ፤ ፈተና ፣ አሽከላም
አድነን ስንል እንድንጸልይ አስተማረን ።

የኃጢአት ዓይነቱና ስልቱ ብዙ ነው ፣ ለዚ
ህም ሁሉ መነሻው ዲያብሎስ ነው ፣ ስለዚህም ከዲ
ያብሎስ ወጥመድ ከእርሱም ምክር መዳን ይቻላልና
ወደ እግዚአብሔር መጠጋት አድነንም ብሎ
መለመን ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ከጠበቀ ፣እግ
ዚአብሔርም ከሰውዬው ጋር ከሆነ ምንም አያገኘ
ውም ፣ ምንም አይደርስበትም ፣ ስለዚህ የእግዚአ
ብሔርን ስም መጥራት እርሱም እንዳይለየን እንዳ





ያጋልጠንም አድነን እንጂ አታጋልጠን እያልን
መለመን አለብን ።

በሐሳብ ፤ በንግግር የሰው ልጅ ይበድላል ፣ ለዚ
ህም ሁሉ መነሻው ሰይጣን ነው ፣ ግን ወደ እግዚ
አብሔር ከቀረብን አድነንም ብለን በእግዚአብሔር
ከተማጸን እንድናለን ፤ ዲያብሎስንም እናቸንፋለን
የኃጢአትም ምንጩ ይደርቃል ፣ ሥሩ ይበጠሳል ።

ለ ፡ ክፉ የተባለው መከራ ሥጋ ነው ፣ እርሱም
ረሀብ ፤ጥም ፤እርዛት ፣ አባር ቸነፈር ፣ ጦርነት ፣ በጠ
ቅላላውም የሰውን ልጅ የሚጐዱ የተለያዩ ችግሮች
ናቸው ፣ ከእነዚህም ሁሉ የማዳን ችሎታ ያለው
እግዚአብሔር ብቻ ነው ፣ ስለዚህ ወደ እርሱ ብቻ
አድነን ብለን እንጮሃለን ።

እነዚህ ዓይነታቸው ስማቸው የተለያዩ ችግሮች
ሁሉ የሰው ዘርን ሁሉ የሚጐዱ ናቸው ፣ የሰውም
ልጅ በኃይሉ በጥበቡ ከነዚህ ሊያመልጥ አይች
ልም ፤ ትክቁ መፍትሔ ጸሉት ስለሆነ አድነን
እያሉ መጸለይ ፣ እግዚአብሔርም በሰጠው ዕው
ቀት መሥራት ለሰው ሁሉ ተገቢ ነው ።

ይኸ ትዕዛዝ ለሰው ልጅ ሁሉ ስለሆነ ሁሉም
በዚህ መልክ ቢሠራ ፣ ቢጸልይም ከቶ የሰው ልጅ





በችግር ባልተዋጠም ነበር የእግዚአብሔር ቃል
እውነት ነውና በጸሎት ይዳናልና ።

ሐ ፣ ከክፉ አድነን ስንል እንድንጸልይ ሲያዝ
ክፉ የተባለው መከራ ነፍስ ነው ፤ እርሱም ክህደት
ገሃነመ እሳት ነው ፣ በዚህ ዓለም እንደኖርን እንኖራ
ለን ፣ ግን ይኸ ሁሉ ያልፋል በክርስቶስ ፪ኛ መም
ጣት ጊዜ ግን ከፍተኛ ፍርድ አለ ንዑና ሑሩ የሚል
፣እንግዲህ ሑሩ እምኔየ የሚል ድምፅ ከመስማት
የበለጠ ክፉ ነገር የለምና ከዚህ እንድንድን አሁን
ምግባር ትሩፋት እንድንሠራ ፣ አሁን በጸሎት ጽሙ
ዳን እንድንሆን ያስተምረናል ። ከሁለተኛ ሞት
ከመጨረሻው ፍርድ አድነን እያልን አሁን መጸ
ለይ አለብን ። አሁን ሰይጣን አሳስቶን ከእውነተ
ኛው መሥመር ወጥተን ከኖርን ምግባር ትሩፋት
ካልሠራን « ሑሩ እምኔየ » መባላችን አይቀርም፤
ነገር ግን ጌታችን እንዳስተማረን እርሱን ብቻ እያ
መለክን ለእርሱ ብቻ የተገዛን የእርሱንም ትእዛዝ
ብቻ የተቀበልን ከአሁኑ አድነን እያልን ጸሎት የጸ
ለይን እንደሆን እንድናለን ።

በኋላ ንስሐ የለም ጸጸት ብቻ ነው ፣ ስለዚህ
አሁን ምቹ ጊዜ አለን ዛሬ በሠራነው ነገ ዋጋችንን
የምናገኝ ስለሆነ አድነን እያልን መጸለይ አለብን።





# ክፍል ፫ መደምደሚያ

## ሀ፥ የመንግሥት ባለቤት ፣

« እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ፣ ኃይል ወስ
ብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን » ( ማቴ ፣ ፮ ፣ ፲፬ ) ።
(መንግሥት ያንተ ናትና፥ ኃይልም ምስጋናም ለዘ
ለዓለሙ አሜን ) ።

« እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት »

መንግሥት ያንተ ናት ማለት ሥልጣኑ የባ
ሕርይህ ነው ፣ ሁሉን ለማድረግ ትችላለህ ማለት
ነው ። ሁሉን ለማድረግ ፣ ሁሉን ለመቆጣጠር
ችሎታ ያለህ ፣ ሁሉን የምትገዛ መንግሥትና ሥል
ጣን ገንዘብህ የሆንክ አንተ ነህና ። መንግሥት ሁሉ
ኃይልም ሥልጣንም የእግዚአብሔር ብቻ ነውና፤
ሰው የማይሾመው የማይሽረው ፣ በባሕርይውም
ሞት በመንግሥቱም ሽረት የሌለበት እርሱ ብቻ
ነው ፣ ስለዚህ መንግሥት ሁሉ ያንተ ናት እያልን
እናመሰግነዋለን ። ለሰይጣን ራሱን የቻለ መንግ
ሥት የለውም ሥልጣኑም የእግዚአብሔር ብቻ
ነው ፣ስለዚህ ለሰይጣን አንተ ሥልጣን አትስጠው
መንግሥት ያንተ መሆኑን እምናለሁና ።

መንግሥትህ ትምጣ ብላችሁ ጸልዩ ብሎ ነበርና መንግሥቱ ሰው ሠራሽ ያልሆነች ጊዜያዊትና ቅጽበታዊትም ያይደለች እውነተኛና ሰማያዊት መሆኗን ለመግለጥ መንግሥት ያንተ ናትና ስንል ባለቤትነቱን እናረጋግጣለን ።

እኛ የእግዚአብሔር ልጆች የሆን ሁሉ ፍጹም ደስታ ሙሉ ጸጥታ ያለን ሰዎች ነን ፤ ምክንያቱም መንግሥት ገንዘቡ የሆነ የሰማያዊው ንጉሥ ልጆች ነንና ። መንግሥት የእርሱ ስለሆነች ማንም ባለ ሥልጣን አይበረታብንም ከእርሱ መንግሥት ውጭ ሊያደርገን የሚችል ኃይል የለምና ። ፍርሃትና ጭንቀት የለብንም ፤ ሁሉንም በእግዚአብሔር ኃይል ድል እንነሣለንና ።

ምናልባት ልንፈራው የሚገባን ነገር ቢኖር ኃጢአት ሠርተን በደል በድለን ከሰማያዊ አባታችን ርቀን እንዳንገኝ ነው ፤ ይኸ ከሆነ ግን ራሳችንን ለጠላት አሳልፍን በራሳችን ፍላጐት ሰጠን ማለት ነው ፤ በዚህ ነገር በጣም ልንጠነቀቅ ፤ ከክፉ ነገር ሁሉ ልንርቅ ይገባናል ፤ ምክንያቱም አንድ ጊዜ ከሰይጣን እጅ ከገባን ለመውጣት አንችልምና ።

የጌታን ጸሎት ሳናቋርጥ መጸለይ የሚገባን





ከዚህ ሁሉ ልንድን እንችል ዘንድ ነው ፤ ይኸን ጸሎት ስንጸልይ ወደ ፈተና እንዳንገባ ይረዳናል ለሥጋችንም ለነፍሳችንም ዐቃቤ ርእስ ይሆነናል።

መንግሥተ ሰማያት የማውረስ ሥልጣን የእርሱ ብቻ መሆኑን ፤ እርሱ ደግሞ ቸር አባት መሆኑን ለእርሱ ያለው ሁሉ ለኛ እንደሚሆን በማመን «መንግሥት ያንተ ናት » እርሷን ለመውረስ የበቃን አድርገን ፤ ለመንግሥተ ሰማያት ባለ ቤት የላትምና ማለት ነው ።

መንግሥት የሌላ ቢሆን አስተዳዳሪውም ባለ ሥልጣኑም ሌላ ይሆን ነበር ፤ አሁን ግን መንግሥት የአባታችን የእግዚአብሔር ነው ፤ የእርሱ የባሕርዩ ናት ፤ ስለዚህ አስተዳዳሪውም ባለቤቱም እርሱው ነው ፤ ይኸም ከሆነ የባሕርይ ምስጋና የሚገባው እርሱ ብቻ ነው ።

## ለ. ኃይል የባሕርዩ የሆነ፤ኃይል ከሃሊነትም

የባሕርይህ ነው ፤ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለህ አንተ ብቻ ነህ እያልን እንድናመሰግነው ያዘናል ።

ሰውን ኃያል ነው ቢሉት ድካም ይሰማዋል ፤ በሞት ይለወጣል ፤ ይኸንኑም ቢሆን የሚያገኘው ከኃያሉ ከእግዚአብሔር ነው ፤ እግዚአብሔር





አምላክ ግን ፍጹም ኃይል የባሕርዩ ነው ፤ ስለዚህ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ አለው ።

ከእግዚአብሔር ባሕርያት ፩ኛው ፍጹም ኃይል መሆኑና ፍጹም ኃይል ገንዘቡ መሆኑ ነው ፤ ሁሉን ፈጥሯል ሁሉን መሥርቷል አቅቶት የተወው ነገር የለምና ። ዛሬም ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው ፤ ፍጹም ኃይልም ገንዘቡ የሆነ እርሱ ብቻ ነውና ፤ ስለዚህ ለከ ኃይል ፤ ለከ ጽንዕ እየተባለ ይመሰገናል ፤ የቤተ ክርስቲያናችን ጸሎትም «ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ---»የሚል ነው ።

እግዚአብሔር ፍጹም ኃያል እንደመሆኑ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው እርሱ ብቻ ነው ፤ ስለዚህም መልአኩ ቅ/ገብርኤል ሲመሰክር «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለውም» ብሏል (ሉቃ- ፩፡፴፯) ። ኢዮብም «ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንክ ሐሳብህም ይከለከል ዘንድ እንደ ማይቻል አወቅሁ» ሲል መስክሯል (ኢዮ- ፵፪፡፪)።

እኛም ኃይል ጽንዓት እንዲኖረን ከእርሱ ጋርም አንድነት እንዲኖረን ያስፈልገናል ፤ እርሱ ከኛ ጋር ከሆነ ሁሉን ለማድረግ እንችላለን የሚቃወመን የለም ማንም አይቃወመንም (ሮሜ ፡ ፰፡፴-፴፩) ።





## ሐ. የክብር ባለቤት ፤

« ወስብሐት » ክብር የክብር ክብር የሚገባህ ጌትነትም የባሕርይህ የሆነ አንተ ብቻ ነህ ፤ ስለዚህ ለአንተ ብቻ ምስጋና እናቀርባለን ።

የክብር ባለቤት ፤ የምስጋና ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው ፤ ስለዚህ ለእርሱ ብቻ ጉልበት ሁሉ ይምበረከካል ፤ አንደበትም ሁሉ እርሱን ብቻ ያመሰግናል ፤ እኛም ልጆቹ ቤተ ሰቦቹ ንጹሕ ምስጋናን ለእርሱ ብቻ እናቀርባለን ።

## መ. ዘለዓለማዊ፡

«ለዓለመ ዓለም» እግዚአብሔር የነበረ ፤ ያለ ፤ የሚኖርም እንደመሆኑ ምስጋናው ከሃሊነቱ ለዘለዓለም ነው ። ይኸ ቃል እኛም ዕለትና ሰዓት ሳንወስን ሁል ጊዜ እንድናመሰግነው ያስገነዝበናል ። ሁሉም ያልፉል ይጠፉልም ፤ እግዚአብሔር ብቻ ለዘለዓለሙ ጸንቶ ይኖራል ፤ ክብሩና ምስጋናውም ለዘለዓለም ነው ።

አምላክ ዘለዓለማዊ እንደመሆኑ ስጦታው ፤ ይቅርታውም ለዘለዓለም ነው ፤ ከቶ የሚያቋርጥበት ጊዜ የለም ፤ ስለዚህ ምስጋናውም ዘለዓለማዊ ነው ።

ልጆቹ ሁነን እንደየፍላጐታችን ገልጠን እን ድንለምነው ዕድል ሰጠን ፡ ሁሉንም እንደሚሰጠን አምነን መለመን እንዳለብን ስንናገር መጥተናል፤ አሁን በዚህ ማጠቃለያ የእግዚአብሔርን ከፍተኛ ነቱን ኃያልነቱን የምስጋና ባለቤት መሆኑን ገል ጠን የምንናገረው አባታችን እንዲህ ያለ ከፍተኛ ሲሆን እኛን ከምድር ሊያነሣን ከፍ ከፍም ሊያደ ርገን ስለወደደ በምሕረቱ ብቻ ልጆቹ አደረገን ፡ ስለዚህም እንደውለታ አድርገን እንድናመሰግነው በማጠቃለያው አስተማረን ።

እግዚአብሔር በዓለም ላይ ብቻውን ንጉሥ ነው ፡ ፍጹም ኃያልም እርሱ ብቻ ነው ፤ ስለዚህ ክብርና ምስጋና ለብቻው ይገባዋል ፡ ምስጋናም የባሕሪው ነውና ።

እንግዲህ ይኸን ጸሎት በጸለይን ጊዜ እያንዳን ዳችን በግል እምነታችን ሙሉ ሥልጣን ፍጹም ኃይል ያለውን አምላክ በዚህ ማምለክ ማመስገንም አለብን አምልኮትና ስግደትም የሚገባው እርሱ ብቻ መሆኑን መመስከር አለብን ።

## ሠ. ይደረግ ፡

«አሜን» አሜን የሚለው ቃል ዕብራይስጥ ነው፡ በግእዛችን ግን « ለይኩን » የሚለው ነው በአ





ማርኛ ደግሞ እሺ ፡ ይሁን ፡ ይደረግ ማለት ነው ።

እንግዲህ ከላይ ስንናገረው ስናትተውም የመ ጣነውን ሁሉ ይሁን ፤ ይደረግ ማለት ማጽደቅ ነው።

ከእግዚአብሔር የጠየቅነው ብዙ ነገር አለ ፡ እንግዲህ ያ ሁሉ ይሁንልን ፤ ይደረግልን ብለን አምነን መቀበላችን ነው ።

እግዚአብሔር አምላክ እውነተኛ አባታችን ስለሆነ የነገሩትን የማይረሳ ፤ የለመኑትን የማይነሣ ነው ፡ ስለዚህ የተመኘነው ፡ የለመነውም ሁሉ ይሁንልን ፤ ይደረግልን ብለን አምነን ጸሎታችንን መዝጋት ነው ።

«አሜን የመሆን» የማረጋገጫ ቃል ነው ፡ በመጀመሪያ ጸሎታችንን ስንጀምር ሁሉ እንደሚ ሆንልን አምነን ነው ፡ ስለዚህ ጸሎታችንን ሁሉ ስንፈጽም የለመነው ልመና ያቀረብነው ምስጋና ሁሉ ይሁንልን ! ይደረግልን ! ብሎ በዚህ ቃል ይዘጋል ። አሜን !





# ክፍል ፪ ምስጋና ስለ እመቤታችን፡

## መቅድም ፡

ቅ. ማርያም ከፍጡራን ሁሉ በላይ ፡ ከፈጣ ሪም በታች ስለሆነች ምስጋና የሚገባት የሰው ወገን ለሆነ ሁሉ መመኪያ የሆነች እመቤት ናት ። ለእ ግዚአብሔር ለአምላካችን ምስጋና የባሕርዩ ስለሆነ ፍጹም ምስጋና ከፍጥረቱ ሁሉ ይገባዋል ፤ ስለዚህ ማንኛውም ፍጡር በየመጠኑ በየግዕዛኑ ያመሰግነ ዋል ። ሌሎች ቅዱሳን እግዚአብሔር የቀደሳቸው እንደመሆናቸው ስለ ትሩፋታቸው ፤ ስለ ቅድስናቸው የጸጋ ምስጋና ይገባቸዋል።ቅ. ማርያም ግን ከሁሉ የተለየች ቅድስተ ቅዱሳንም ስለሆነች ከተቀደሱት የተቀደሰች ፤ ከከበሩትም የከበረች ናት፤ የአምላክ እናት ስለሆነች ከቅዱሳን ሁሉ የተለየ ከፍም ያለ ምስጋና ይገባታል ፤ አምላክ ቀድሷታል ፤ ለእናትነትም ፤ አብቅቷታልና ። ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀኗ ስለወሰነችው ከፍ ያለ ክብርና ምስጋና አሁንም ይገባታል ።

በዚህ በእመቤታችን ምስጋናና ጸሎት ውስጥ የእመቤታችንን የክብር ስሞች የሚገልጡ ፮ ቃሎች ይገኛሉ ፡ እነዚህም ቃሎች እግዝእትየ ማርያም ፡ ድንግል በክልዔ ፤ እመ እግዚአብሔር ፤ ቡርክት





አንቲ እምአንስት ፤ ምልዕተ ጸጋ ፤ ሰአሊተ ምሕ ረት የሚሉ ናቸው ከነዚህም ውስጥ ፪ቱ ቃሎች ብቻ በቤተ ክርስቲያን አባቶች የተወሰኑ ናቸው፤ እነርሱም እግዝእት ፡ ሰአሊተ ምሕረት የሚሉት ናቸው ።

ሌሎቹ ፬ቱ ግን ከሉቃስ ወንጌል የተወሰዱ መልአኩ የተናገራቸው ቃላት ናቸው ።

እነዚህ ቃላት የእመቤታችንን ክብር የሚገ ልጡ ፤ ከአምላክም ጋር ያላትን ግንኙነት የሚያ ስረዱ ቃላት በመሆናቸው በጸሎት መልክ ተዘጋ ጅቶ ጌታ ከአስተማረው ጸሎት ከአቡነ ዘበሰማያት ጋር ባለመለየት አብሮ እንዲጸለይ ቤተ ክርስቲያ ናችን ወሰነች ።

እነዚህን ፮ቱን ቃላት ተከትሎ ከፍ አድርጎ ነገረ ማርያምን ለመጻፍ ስለ ቅ ፡ ማርያም ሰፋ ያለ ድርሰት ለማቅረብ ይቻላል ፤ ይሁን እንጂ በጸሎት መልክ አሁንም ብናቀርበውም በትምህርተ ክርስትናም በኩል ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ለመ ሆኑ የማያጠራጥር ነው ፡ ምክንያቱም የሥላሴ ሦስትነትና አንድነት የታወቀ እግዚአብሔር ወልድ ከቅ ፡ ማርያም ከተወለደ በኋላ ነውና ፤ « ወአልቦ ዘአእመሮሙ ለሥሉስ ቅዱስ ዘእንበለ ይሠገው ወልድ ዋሕድ እምቅድስት እሙ» ይላልና።

በጠቅላላም ለክርስትናው እምነትና ትምህ
ርት መነሣት ምክንያት ክርስቶስ ከእመቤታችን
ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ፍጹም ሰው
ፍጹም አምላክ ሁኖ ከተገለጠ በኋላ ነውና ።

እመቤታችን ቅ ፡ ማርያም ለክርስቲያናዊ
እምነታችንና ትምህርታችን መሠረት ናት ፤ ስለ
ዚህ ይኸን የእርሷን ክብር የሚናገረውን ጸሎት
ስንጸልይ ወዲያውንም ድኅንነታችን የተገኘው ፥
ክብራችን የተገለጠው በቅ ፡ ማርያም አማካይነት
መሆኑን ያስገነዝበናል ፥ ስለዚህም እርሷን እናመሰ
ግናለን ክርስቲያናዊ እምነታችንና ትምህርታችንን
እንመሰክራለን ማለት ነው ።

እንግዲህ ወደ ጌታ ለመድረስ መሰላል የሆ
ነችን ቅ ፡ ማርያም እንደመሆኗ ከጌታ ሳንለይ
ይኸን ጸሎት በሚገባ እንጸልያለን ።

ስለ ቅ ፡ ማርያም ምስጋና በመጀመሪያ ያቀ
ረበው በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም መልአኩ
ቅ ፡ ገብርኤል ነው ፤ እርሱም ከእግዚአብሔር
ተልኮ ወደ ቅ ፡ ማርያም ቀርቦ «ምልዕተ ጸጋ
ሆይ ደስ ይበልሽ ! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር
ነውና» ሲል አሰምቶ ምስጋና አቅርቦላታል
(ሉቃ ፤ ፩ ፡ ፳፰) ።

ከቅ ፡ ገብርኤልም በኋላ ደግሞ ቅ ፡ ኤልሳ





ቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ የመልአኩን ቃል
በመድገም ከፍተኛ ምስጋና ለቅ ፡ ማርያም አቅር
ባለች ። መልአኩን ቅ ፡ ገብርኤልን ወደ ቅድስት
ማርያም የላከው መንፈስ ወደ ቅ ፡ ኤልሳቤጥ ሂዶ
በእርሷም ላይ አድሮ መልአኩን የተናገረውን ቃል
መልሳ ለቅ ፡ ማርያም ስታቀርብ ተገኝታለች ።
እንግዲህ ይኸ ምስጋና ከእግዚአብሔር የተፈቀደ፥
የታዘዘም መሆኑን ያመለክታል ።

ቅ. ማርያም ምስጋና እንዲገባት ከመላእክት
ወገን ቅ ፡ ገብርኤል ፥ ከሰው ወገን ደግሞ ቅ ፥ ኤል
ሳቤጥ አስመስግነዋታል ፤ የእነዚህን የምስጋና
ምስክርነት ከሰማች በኋላ ከእንግዲህ ወዲህ ፥
ከዛሬ ጀምሮ ፍጥረት ሁሉ ያመሰግኑኛል ፥ እግዚ
ብሔር ለኔ ታላላቅ ተአምራትን አድርጎልኛልና
ስትል ከሁሉም ዘንድ ምስጋና እንደሚገባት
አረጋግጣ ተናግራለች (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፰) ።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ይኸን ሁሉ
አብነት ነሥተው ለቅ ፡ ማርያም ንጹሕ ምስጋና
እንዲገባት ተናግረዋል ፥ የምስጋና ድርሳንም በያ
ይነቱ ጽፈዋል ።

የኛ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያ
ንም ስለ ቅ ፡ ማርያም ክብር ፤ ምስጋና የተለየ አስ
ተያየት አድርጋ በየጊዜውና በየሰዓቱ በማኅበርም





በግልም ጸሎት ጊዜ የሚጸለዩ የተለያዩ የጸሎት
ዓይነቶች አዘጋጅታ ስታመሰግን ትገኛለች ፥ ምእ
መናኑም ይኸንኑ ተከትለው ከአምላክ በታች ከፍ
ጡራንም በላይ የሆነ ክብር በመስጠት ምስጋና
ሲያቀርቡ ይገኛሉ ። ከጸሎቱም ዓይነት ፩ኛው
ከአቡነ ዘበሰማያት ባለመለየት ሁል ጊዜ የሚጸለይ
«በሰላመ ቅ ፤ ገብርኤል መልአክ » የሚለው
ከወንጌል የተወጣጣው ጸሎት ነው ።

ይኸም ጸሎት መልአኩ ቅ ፡ ገብርኤልና
ቅ ፥ ኤልሳቤጥ በመጀመሪያ ከተናገሩት ቃል የተ
ወጣጣ የቅ ፡ ማርያምን ሙሉ ክብሯን ፥ ቅድስና
ዋን ፤ እመ አምላክነቷን የሚገልጥ ጸሎት ነው።አቡነ
ዘበሰማያት በሚጸለይበት ቦታ ሁሉ ይኸ በሰላመ
ቅ ፡ ገብርኤል የተባለው ጸሎት በምንም መልክ
አይለይም፥አብሮ ይጸለያል፥ሁለቱም ጸሎቶች የጸሎ
ቶች ሁሉ ማሠሪያ ማጠቃለያ ሁነው እንዲጸለዩ
ቤተ ክርስቲያናችን ወስናለች ።

የዚህን ጸሎት ትርጉም ከነሙሉ ሐተታው
ማንኛውም ሰው ማወቅ ስመሚገባው እንደሚከ
ተለው እንገልጣለን ። የቅድስት ማርያም ፍቅር
ያደረበት የጸሎቱም ስሜት የቀሰቀሰው ምእመን
በሰፊ ልቦና እንዲከታተለው እናስገነዝባለን ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ





## ፩፡ በሰላመ ቅ. ገብርኤል መልአክ ፤

« በሰላመ ቅ . ገብርኤል መልአክ ፥ እእግዝእትየ
ማርያም ሰላም ለኪ »

(እመቤቴ ማርያም ሆይ ! በመልአኩ በቅ.ገብ
ርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ ) ።

ይኸ የመጀመሪያው ክፍል እንደ መግቢያ
ሆኖ የጸሎቱ ዓይነት ምን እንደሆነ የሚገልጥ ነው ፥
ማለት መልአኩ ቅ ፡ ገብርኤል በአመሰገነው ዓይ
ነት ፥ እርሱንም አብነት አድርገን ፥ ወይም እርሱ
ራሱ ያመሰገነበትን ጸሎት በመድገም ለቅ . ማር
ያም ምስጋና ማቅረብ ተገቢነቱን ይገልጣል ።
ይኸን ጸሎት መልአኩ ከራሱ አንቅቶ ከልቦናው
አውጥቶ አልተናገረውም ፥ ስለዚህ ልብ ወለድ
ጸሎት አይሆንም ፤ ነገር ግን መልአኩ ቅ . ገብር
ኤል ከእግዚአብሔር ታዞ ከእግዚአብሔርም ተልኮ
መጥቶ አመስግኗታል ፥ ስለዚህ እኛም መልአኩ
ቅዱስ ገብርኤል በሰጠሽ ሰላምታ በአቀ
ረበልሽ ምስጋና ሰላም እንልሻለን ፤ ምስጋና እና
ቀርብልሻለን ! ስንል አምላክ የፈቀደው ያዘዘውም
ምስጋና ጸሎትም መሆኑን ገልጠን እንመሰክራለን
ምስጋናም እናቀርባለን ።

የምራሥች በተቀበለችው በዚህች ድንግል አማካይነት ማንኛውም አማኒ የጸጋ ባለቤት መሆኑን ልንረዳ እንችላለን ፤ በሔዋን በእናታችን ምክንያት ሰው ሁሉ ጸጋው እንደተገፈፈ እናውቃለን ምልዕተ ጸጋ በተባለች የሁላችን እናት በሆነች በቅ ፡ ማርያም ግን ሁሉም የጸጋ ባለቤት ሁኗል ።

ቅ . ማርያምን ለዓለሙ መዳን ምክንያት ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር መርጧታል ፤ ስለዚህም የሁሉ እናት ትሆን ዘንድ ምልዕተ ክብር አደረጋት።

ቅ . ማርያም መልአኩን ማየት ፤ ከእርሱም ጋር መነጋገር የምሥራች ድምፅንም መስማት ታላቅ ሲያደርጋት አስደሳችም ሲሆን ሰላም ለአንቺ ይሁን የሚለውን ቃል ደግሞ በበለጠ ለነፍስም ለሥጋም ጸጥታን የሚሰጥ በመሆኑ ድርብ ደስታን ይሰጣል። ከዚህ የበለጠ ግን እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው የሚለው ከፍተኛ የብሥራት ቃል ነው ፤ ይኸም ለጊዜው ንጽሕናዋን ቅድስናዋን አይቶ የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኗን ያመለክታል ፤ ፍጻሜው ግን የእግዚአብሔር እናት መሆኗን ያመለክታል ።

ይኸ ሁሉ ዕጥፍና ድርብ የሆነ አስደሳች ቃል ሲነገራት ቅ . ማርያም ከዕለታዊ ስሜቷ የተለወጠችበት ከቶ አልነበረም ፤ ከንቱ ውዳሴ እንዳይሆ





ንባት በመፍራት ።

ለቅ . ማርያም የመጀመሪያ ምስጋና አቅራቢ የምሥራችም ተናጋሪ ሁኖ የቀረበው መልአኩ ቅ . ገብርኤል እንደሆነ ቅ . ሉቃስ በወንጌሉ መዝገቡ ይገኛል ( ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፳፮ — ፴፰ ) ።

እኔም አሁን እርሱን አብነት አድርጌ ፤ እርሱ እንዳቀረበልሽ ሰላምታ ፤ እርሱም እንዳመሰገነሽ ያለ ምስጋና አቀርብልሻለሁ በማለት እያንዳንዱ ምእመን ለቅ . ማርያም ምሥጋና ያቀርቡላታል ፤ ምልጃም ያደርጋሉ ።

መልአኩ ቅ . ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ እንደመጣ ቀኝም ግራም ሳይል ቅ . ማርያም ወደ አለችበት ክፍል በቀጥታ ሰተት ብሎ ገብቶ ጸጋንና ክብርን ያገኘሽ እመቤት ሆይ ! ደስ ይበልሽ ሲል ቅ . ማርያምን ምልዕተ ጸጋ እንደ ሆነች እግዚአብሔርም ከእርሷ ጋር እንደሆነ ገልጦ ተናግሯል ። ቅ . ማርያምን ምልዕተ ጸጋ ብሎ የሰየማት ቅ ፡ ገብርኤል ነው ፤ በሌላ ስም ሳይጠራ « ምልዕተ ጸጋ » ሲል ነው የጠራት ። በእርግጥም ቅ ፡ ማርያም ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር ናት ፤ ስምን መልአክ ያወጣዋል የተባለው ይኸን በመሰለው ሲታይ ነው ፤ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን





ነሥቶ የተወለደው ክርስቶስ ለሁሉ ጸጋን አብዝቶ የሚሰጥ ሁኗልና ።

መልአኩ ቅ . ገብርኤል ወደ ቅድስት ማርያም ገብቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበውን ሰላምታና ምስጋና ቅ ፡ ሉቃስ እንዲህ ሲል በቀጥታ ይነግረናል « ——መልአኩም ወደ እርሷ በገባ ጊዜ አለ ደስ ይበልሽ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ፤ ከሴቶችም ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ» (ሉቃ፡ ፩፡፳፰) ። ቅ.ማርያም ምልዕተ ጸጋ መሆኗን ሲናገር ደስ ይበልሽ ብሎ ደስታንም አስከትሎ ነው ፤ ምክንያትም ሲሰጥ "እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና በማለት ጠቅላላ መግለጫ ሰጥቶበታል ።

እንግዲህ እኛም አሁን ሌላ ጸሎት ሳይሆን በመልአኩ በቅ ፡ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን ማለት ለሰላምታ ለምስጋናም እንግዳ አይደለሽም፤ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባሻል ፤ መልአኩን አብነት አድርገን እናመሰግንሻለን ስንል ምስጋናዋን እንጀምራለን ።

ስለ ቅ፡ ማርያም የምስጋና ጀማሪው ይኸ መልአክ ይሁን እንጂ ወዲያውኑ የቅ ፡ ማርያም አክስት የምትሆን መንፈስ ቅዱስን የተመላች





ቅ . ኤልሳቤጥ የመልአኩን ቃል በመድገም ምስክርነቱንም በማጽናት « ቡርክት አንቲ አምአንስት ፤ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ » ስትል አመስግናለች (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፪ )።

ይኸቺ ቅድስት ሴት ለራሷ መንፈስ ቅዱስን የተመላች ሁና በመንፈስ ቅዱስም ተገልጦላት ታመስግን እንጂ መልአኩ ቅ ፡ ገብርኤል በመጀመሪያ የሰጠውን ሰላምታ ያቀረበውንም ምስጋና በመድገም ተናግራለች ፤ ይኸም የቅ ፡ ማርያም ምስጋና ከእግዚአብሔር ዘንድ የተፈቀደ መሆኑን ያመለክታል ። ስለዚህ እኛም አሁን እንደ መልአኩ ቅ ፡ ገብርኤል ሁነን እርሱንም አብነት አድርገን ሰላምታ ይገባሻል እያልን ልናመሰግናት የሚገባ መሆኑን ለመግለጥ ቤተ ክርስቲያናችን ይኸን ጸሎት አዘጋጅታ ሁሉም እንዲጸልየው ወስናለች ፤ ስለዚህ በመልአኩ በቅ ፡ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ እያልን እናመሰግናታለን ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ እንደመጣ ምስጋናውንና ሰላምታውን ከእግዚአብሔር አግኝቶ እግዚአብሔር ገልጦለት እንጂ ከራሱ አውጥቶ እንዲሁ የተናገረው አይደለም ፤ ( ሉቃ . ፩ . ፳፮ ) ። እንግዲያውስ በእግዚአብሔር

መንፈስ ተመርቶ ከእግዚአብሔርም አግኝቶ መልአኩ ቅ. ገብርኤል በአመሰገነበት ምስጋና ሰላምታ ለአንቺይገባል እያልን እኛም ማመስገን ግዴታችን ነው ።

ከቅዱሳት ሴቶች ውስጥ የምትሆን ኤልሳቤጥ እንኳን ከሴቶች ሁሉ አንቺ የተለየሽ ነሽ ስትል ማርያም ቅድስተ ቅዱሳን መሆኗን ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብርም መሆኗን መስክራ ተናግራለች ፤ ምክንያቱም ራሷ የእግዚአብሔር ጸጋ በዝቶ ያደረባት ፤ መንፈስ ቅዱስንም የተመላች ሁና ሳለ ቅ ፤ ማርያም ከእርሷ የበለጠች መሆኗን ገልጣ መስክራለችና ።

ቅ. ማርያም ንጽሕት ቅድስት ሁናለች አምላክ ደግሞ የበለጠ አንጽቶ ቀድሶ ለእናትነት መርጧታል ፤ ስለዚህ ቅድስተ ቅዱሳን እየተባለች መመስገን የሚገባት እመቤት ናት ።

<u>ቅዱስ ገብርኤል መልአክ</u> ፤ ተፈጥሮቸው መላእክት ሳሉ ከክብራቸው የተዋረዱ ከማዕርጋቸው የወረዱ እንደእነ ሣጥናኤልና ሠራዊቱ ካሉት ውስጥ ሳይሆን ንጽሐ ጠባዩ እንዳልተለወጠበት ንጹሕ መልአክ እንደሆነ ለማጠየቅ ቅዱስ መልአክ እንደሆነ ለማሳየት ቅዱስ ገብርኤል በማለት ቅድ





ስናውን ገልጠው አሳዩለት ፤ የምስጋናም አብነት መሆኑንም አባቶች ተናገሩለት ። ስሙ ያልታወቀ መልአክ እንዳይባል ገብርኤል በማለት ፤ መልአከ ጽልመት ሳይሆን መልአከ ብርሃን ፤ ተርታ መልአክ ሳይሆን ሊቀ መልአክና የእግዚአብሔር ባለሟል የሆነ ፤ ይኸንንም በእግዚአብሔር ፊት የምቆም እኔ ገብርኤል ነኝ ሲል ራሱ መልአኩ ለዘካርያስ ነግሮት ነበር ፤ (ሉቃ . ፩ ፣ ፲፱) ፤ ከቅዱስ እግዚአብሔር ፊት የሚቆም ቅዱስ መልአክ ስለሆነ ቅዱስ መልአክ አለው ፤ ገብርኤል አብሣሬ ትፍሥሕት አብሣሬ ትስብእትም ለመሆን የቻለ የታመነና ቅዱስ መልአክ በመሆኑ ነው ፤ ይኸም ሁናቴ የተለየ መልአክ ያደርገዋል ፤ ስለዚህ የተለየ ቅ. መልአክ ለማለት ይኸን ማዕርግ አባቶች ሰጡት ። ገብርኤል ማለትም ወልደ እግዚአብሔር ማለት ነው ።

እንዲሁም ገብር የሚለው ቃል ባለሟል ማለት ነው ፤ ኤል ማለት ደግሞ የእግዚአብሔር ስም ነው ፤ ስለዚህ ገብርኤል ማለት የእግዚአብሔር ባለሟል ማለት ነው ። መልአክ ማለት ደግሞ





መልእክተኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚ ማለት ነው ። በየቋንቋው ሁሉ የመላእክት ስማቸው ሥራቸውን የሚገልጥ ተላላኪነታቸውን የሚያጸድቅ ቃል ነው ። ሴማዊያን በሆኑ ቋንቋዎች ሁሉ መልአክ የሚለው ቃሉም ትርጉሙም ሳይለወጥ አንድ ሁኖ ይገኛል ።

እንዲሁም በግሪክኛው አንጌሎስ የሚለው ቃል ለአውሮፓውያን ቋንቋዎች ንባቡም ትርጉሙም እርሱን ተከትሎ የሚሄድ መልአክ ማለት መልእክተኛ ማለት መሆኑን ይገልጣል ። የመላእክት ተግባር ፫ ዓይነት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ስማቸው የሚገልጠው መላላክን ማገልገልን ነው ። ለምስጋና ለብሥራት ወደቅድስት ማርያም የተላከ ስለሆነ መልአክ ሲል ስሙን ከነ ግብሩ በመግለጥ ተናገረ ።

<u>ኦ እግዝእት የ ማርያም</u> ፤ እመቤቴ ማርያም ሆይ ! ልጅዋ እየሱስ ክርስቶስ እኛን ከግብርናተ ዲያብሎስ ነፃ አውጥቶ የሚያስተዳድረን የሚገዛን ስለሆነ እግዚእ « ጌታ » ይባላል ፣ የእርሱም እናት እግዝእት ትባላለች ። ስሟንም ማርያም ብለን ሳንጠራ እግዝእትን « እመቤታችን » ብንል ለሌላ ሴት ሊሆን አይችልም አሻሚነት የሌለው ቃል





ነው ፤ ይኸ ቃል ለእመቤታችን ብቻ የተሰጠ ፤ ቅጽል ነውና ።

እንግዲያውስ ዝም ብሎ ማርያም በማለት መጥራት እንደድፍረት እንደማዋረድም ይቆጠራል፤ ስለዚህ እግዚእትነ ማርያም ወይም ቅ ፣ ማርያም እያልን እንድንጠራት ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምረናለች ። ቅ ፣ ማርያም ለሰው ልጅ ሁሉ መመኪያ ናት ፤ የባሕርያችን የተፈጥሮአችንም መመኪያ ናትና ።

<u>ሰላም ለኪ</u> ፤ ሰላም ለአንቺ ይሁን ፤ ምስጋና ለአንቺ ይገባል ማለት ነው ። የሰው ልጅ ሁሉ የሥጋም የነፍስም ሰላም ጸጥታ ያገኘው ሰላም የተባለውም ክርስቶስ ከእርሷ በሥጋ ከተወለደ በኋላ ነው ። ገና ክርስቶስ ሲወለድ መላእክት ያሰሙት ድምፅ « ሰላም በምድር » የሚለውን ቃል ፤ ነው ፤ ስለዚህ ሰላምን ለማግኘታችን ሰላምም ለመሆናችን ምክንያት የሆነች የሰላምም መተላለፊያ የሆነች ቅ. ማርያም ናት ፤ ስለዚህ ሰላም ለአንቺ ይሁን እያልን እናመሰግናታለን «ብኪ ድኅነ ዓለም ወበወልድኪ ኮነ ሰላም » ይላታልና ።

እመቤታችን ሰላም የሌላት ሁና ሰላም እንድታገኝ የምንለምንላት ፤ የምንመኝላት አይደለም፤

ሰላም ለኪ የሚለው ቃል ምስጋናን እንደማቅረብ ነው ፥ እኛም ሰላም ለአንቺ ይሁንስንል ምስጋና ማቅረባችን ነው ።

እናቷ ሔዋን ከመልአክ ሳይሆን ከሰይጣን (ከእባብ) ቃልን ሰማች ሰላምታን ሳይሆን ኀዘንን ሰማች ፥ ቅ/ማርያም ግን ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣውን መልአክ ድምፅ ሰማች ፥ ግን ኀዘን ሳይሆን የሰላምታ ድምፅ ሰማች ። በዚህም የሰላምታ ቃል ሔዋን እናታችን የሰማችው መራራና የሚያሳዝን ቃል እንደተሠረዘ ያጠይቃል ።

ኀዘን የሰውን ልብ ይሰብራል መልኩን ያጠቁራል ፥ ደስታና ሰላምታ ደግሞ አጥንትን ያለመልማል፤መልክን ያበራል ስለዚህ ቅ. ማርያም የደስታ ቃልን ከመልአኩ በሰማች ጊዜ በሰው ዘር ወርዶ የነበረው የኀዘን የድንጋጤ ቃል ሁሉ ተሰረዘ ጠፋ ፥ የሰው ዘርም ሁሉ ደስተኛ መሆኑን ያመለክታል ።

## ፪. ድንግል በክልዔ ማርያም

« ድንግል በሕሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ» (በሐሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሺም ድንግል ነሺ) ። ሰው የሆነው ሁሉ ከመሥራት ንጹሕ ይሁን እንጂ ከማየት ከመስማት ፥ በተለይም ከማሰብ ከቶ ንጹሕ





ሰው ሊሆን የሚችል አይገኝም ። ብዙዎቹን ቅዱሳን እግዚአብሔር በጸጋው ይቀድሳቸዋል እንጂ ከዚህ ሁሉ ንጹሕ ድንግል አይሆኑም ፥ ከገቢር ግን ንጹሐን ናቸው ። እንግዲህ በአንድ ወገን ብቻ ድንግል ይሆናሉ እንጂ እንደ ቅድስት ማርያም በ፪ በኩል ድንግል ሊባሉ አይቻልም ማለት ነው ፤ ቅ . ማርያም ግን በሐሳቧም ድንግል ናት፥ በሥጋዋም ድንግል ናት ፥ ማለት በሐሳብም በገቢርም ድንግል ናት ማለት ነው ፥ ስለዚህ ድንግል [በክልዔ ትባላለች ።

ሁሉን እናያለን ሁሉን እንሰማለን ፥ ሁሉን እንናገራለን ፤ ግን ብዙ ጊዜ ስሜት አንሰጠውም ፤ በበለጠ ደግሞ አንሠራውም ፥ በእውነት ይኸም ቢሆን ታላቅ ተጋድሎ ነው ፥ ነገር ግን በአዩና በሰሙ ቁጥር ስሜት ለሕሊናቸው የሚያስተላልፉ አሉ ፤ በሐሳብም በማየትም በመስማትም የሚበድሉ ፥ ከዚህም ሁሉ አምልጠው ከቅድስና ከብፅዕና ማዕርግ ደርሰው ለሌላው በረከትን የሚያሰጡ ቅዱሳን ብዙዎች ናቸው ፤ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ በአንድ ወገን ድንግል በመሆናቸው ቅዱሳን ሁነዋል ፥ ቅዱሳንም ተብለዋል ፥ ቅ. ማርያም ግን በሕሊናዋም በሐሳቧም ድንግል ናት ፥ በሥጋዋም





ማለት በገቢርም ድንግል ናት ፥ ስለዚህ ድንግል በክልዔ ትባላለች ፥ ቅድስተ ቅዱሳንም የሚያሰኛት ይኸው በ፪ በኩል፤ ድንግል መሆኗ ነው ፤ «ወኢረኩስት በምንትኒ እምዘፈጠራ ድንግል በሕሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ» ሲል ተናግሯል ።

የአምላክ እናትም ለመሆን ያበቃት ቅሉ ንጽሕናዋ ቅድስናዋም ነው፥እግዚአብሔር አብ ተመለከተ በቅድስና በንጽሕና የተዋበ እንደ ቅድስት ማርያም ያለ ስላልተገኘ እርሷን ብቻ ለልጁ እናትነት መረጣት ። «ቡርክት አንቲ እምአንስት» የሚያሰኛትም ዋናው ይኸ ነው ፥ ንጽሕናዋን ጠብቃ የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር በመሆኗ ከሴቶችም ተለይታ ለአምላክ እናት ትሆን ዘንድ ተመርጣለችና ።

እግዚአብሔር አምላክ ንጹሐ ባሕርይ ነው ፥ የእርሱም ማደሪያ የሚሆነው ሁሉ ንጹሕ መሆን አለበት ፥ ስለዚህ ቅድስት ማርያም ከቅዱሳን ዘሮች ከመወለዷ በላይ ራሷን በራሷ ጠብቃለች ስለዚህ በሐሳብ ድንግል ናት ፥ በሥራዋም ድንግል ናት ፥ በምንም መልክ ነፍሷንም ሥጋዋንም የሚያረክስ የሚጐዳም ሥራ አልሠራችም ።

ስለዚህ አሁን በአማን ቅድስት ፥ በአማን ንጽ





ሕት ፥ በአማን ብፅዕት እያልን እናመሰግናታለን ንጽሕናዋን ቅድስናዋንም እንመሰክራለን ።

## ፫. የእግዚአብሔር እናት ቅ. ማርያም

« እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ» (የአቸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ! ሰላምታ ለአንቺ ይገባል) ።

የእግዚአብሔር እናት ሆይ ፤ ወላዲተ አምላክ ሆይ !ብለን እንጠራታለን ፥ ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀኗ ወስናለችና ። የነገሥታት፥የልዑላን፥የታላላቅም ሰዎች እናት ሳትሆን የአምላክ እናት ስለሆነች ክብሯን ገናንነቷን ገልጠን በመናገር እናመሰግናታለን ።

፫ኛው የቤተክርስቲያን ዐቢይ ጉባኤ በ፬፻፴፩ ዓ/ም ተሰብስቦ ስለእመቤታችን ቅድስት ማርያም የሰጠው ማዕርግና ደረጃ «ወላዲተ አምላክ» የሚለውን ቃል ነው ፤ በዚሁ መሠረት ቤተክርስቲያናችን እመ እግዚአብሔር ፤ እመ አምላክ ፤ ወላዲተ አምላክ እያለች ታከብራታለች ፤ ቅድስት ማርያምን መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን አድርጋ ክብር ትሰጣታለች ።

ይኸም «ወላዲተ አምላክ» የሚለው ቃል የአምላክ እናትነቷን የቅድስት ማርያምን ክብር

ብቻ የሚገልጥ ቃል አይደለም ፤ የአምላክን ፍጹም ሰውነት ፣ ፍጹም ሰው መሆን በጠቅላላውም ምሥጢረ ተዋህዶን የሚገልጥ ቃል ነው ፣ ይኸውም አካላዊ ቃል ከቅ/ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ አምላክ ፍጹም ሰው በመሆን የተወለደውን ልደት ይገልጣልና ።

ንስጥሮስ የተባለው መናፍቅ ወላዲተ አምላክ መባሏ ሐሰት ነው ፤ ተገቢም አይደለም ሰውን ነው የወለደች ፣ ስለዚህ የሰው እናት ትባላለች ብሎ ነበር ፣ እኛ ግን በማሕፀኗ ያደረው ሥጋን የተዋሐደው የአብ ቃል ፍጹም መለኮት ነው ፤ ሥጋን በመዋሐዱ ከቅ/ማርያም ተወለደ ፣ እንግዲህ የተጸነሠው መለኮት ነው ፣ እርሱም በቅ/ማርያም ማሕፀን ሥጋንም ነፍስንም ተዋሕዶ ፍጹም ሰው ሁኖ ተወልዷል ። ስለዚህ የተወለደው ሰው የሆነው አምላክ ነው ፣ ታዲያ ወላዲተ አምላክ ትባላለች ወላዲተ አምላክነቷም የታመነ ነው ።

መልአኩም መልሶ አላት «መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ይመጣል ፣ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል ፣ ስለዚህም ደግሞ ቅዱሱ ከአንቺ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» (ሉቃ.፩፡፴፭) ። ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ ይባላል ሲል ከ፫ቱ ቅዱስ ፩ዱ ቅዱስ እግዚ





አብሔር ወልድ መሆኑን ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ያለው ደግሞ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደውን የእግዚአብሔር ልጅ ወልድን መሆኑን ያጠይቃል ፤ ስለዚህም ቅድስት ማርያም በትክክል ወላዲተ አምላክ ናት ።

ቅድስት ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ ምሥጢረ እግዚአብሔር ተገልጦላት ቅድስት ማርያም የእግዚአብሐር እናት እንደምትሆን እንዲህ ስትል አስቀድማ መስክራለች «ለኔ እንዴት ይገባኛል የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጭ ዘንድ» (ሉቃ፡ ፩፡፵፫) ። የጌታየ እናት ስትል የተናገረችው ቃል ጌታ የሚለው ማነው የሰውን ልጅ ሁሉ ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ አውጥቶ በመንፈሳዊ አገዛዝ የሚገዛ የሁሉ ጌታ የሁሉም ገዥ የሆነውን አካላዊ ቃልን ለማመልከት አይደለምን?

## ቤዛዊተ ዓለም ፤

ክርስቶስን ቤዛ ዓለም ፤ መድኃኒተ ዓለም እያልን እንደምንጠራው እመቤታችንን ቅድስት ማርያምንም ቤዛዊተ ዓለም ብለን እንጠራታለን ይኸንንም የክብር ስም እንሰጣታለን ።

ይኸ የክብር ስም ከመቼ ጀምሮ እንደተወሰነና





እንደተሰጣት አይታወቅም እንጂ ቅ/ማርያምን እመ አምላክ ፣ ወላዲተ አምላክ እያልን እንደምንጠራት ሁሉ ቤዛዊተ ዓለም እያልን ስለ ዓለም ድኅነት እንደሠራች እንመሰክራለን ፤ በዚህም ስም እንጠራታለን ።

ዓለምን ያዳነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ አምነን የተቀበልነው እውነት ነው ፤ ግን ከቅድስት ማርያም በነሣው ሥጋ ዓለም ያዳነ በመሆኑ «ብኪ ድኅነ ዓለም ፣ ወበወልድኪ ኮነ ሰላም» እያልን እንናገራለን የአዳኝነት ሥራንም እንደሠራች አድርገን እንመሰክራለን ።

በቤተ ክርስቲያናችን የጸሎትና የሥርዓት መጻሕፍት ቅድስት ማርያምን ቤዛዊተ ኩሉ ዓለም ሲላት ይገኛል ፤ እንግዲህ ይኸን ቃል አማናዊ ለማድረግ አስረጇውን እንሰጣለን ፤

፩/ ጌታ ሰው ለመሆን ሥጋንም ለመልበስ ምክንያት ስለሆነች ለድኅነታችንም ምክንያት ሁናለችና ነው ፤ ስለዚህ ቤዛዊተ ዓለም እንላታለን ።

፪/ ለአዳኛችን ለክርስቶስ መውረጃ መሰላል ሁናለች ፤ ለድኅነታችን መሸጋገሪያ ድልድይ ሁናለች ፤ እንዲሁም የምንበላው ሥጋ ፣ የምንጠጣው ደም መድኃኒታችን ሲሆን ክርስቶስ ከእርሷ የነሣው





ነውና ከዚህም ሁሉ የተነሣ በአንች ዳን ፤ ለድኅነታቹን ምክንያት ሆንሺን ስለዚህ ቤዛዊተ ዓለም እያልን እናመሰግናታለን በማለት ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም ትባላለች ።

<u>እግዚአብሔር ጸባኦት</u> ፣ የእግዚአብሔርን ቅጥል ጸባኦት በማለት ተናገረ ፣ የሠራዊት ጌታ ለማለት ነው ፣ እግዚአ ጸባኦት እንደማለት ነው ። ጸባኦት የሚለው ቃል ዕብራይስጥ ነው ፤ ትርጉሙም ሠራዊት ማለት ነው ፤ በግእዛችን ግን አንዳንድ ጊዜ ጸባኦት የሚለውን ቃል እንዳለ እንጠቀምበታለን ግን ትርጉሙን አቸናፊ እያልን ተርጉመናል ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ትርጉሙን ሠራዊት፤ ኀያላን እያልን እንናገረዋለን ፣ ለምሳሌ «እግዚአ ኃያላን ምስሌነ« እግዚአብሔር አምላክ ኀያላን ውእቱ ዝንቱ ንጉሠ ስብሐት» ስንል በቀጥታ የሠራዊት ጌታ የኀያላን ጌታ ማለታችንን ያመለክታል ። ሁኖም አቸናፊም ብንል ማንም ኃያል የማይጋፋው ፍጹም ኀይል የባሕርዩ የሆነ አምላክ መሆኑን ለመግለጥ ነው ። የሠራዊት ጌታ ብለን ብንተረጉመውም ኃያላኑ ሁሉ የሚገዙለት የሚሰግዱለት ከሁሉ በላይ የሆነ አቸናፊ አምላክ ለማለት ነው ።

እንግዲህ ይኸ ሁሉ የሚሰግድለት ከሁሉ

በላይ የሆነ የሠራዊት አምላክ በፍጻሜ ዘመን ሰው ሆነ ሥጋንም ለበሰ ከቅ.ማርያም ተወለደ ፤ ቅ.ማርያምም የዚህ ኃያል አምላክ እናት ተባለች ፤ የዚህ ኃያል አምላክ እናት ሆነች ለማለት እመ እግዚአብሔር ጸባኦት አለ ።

## ፬. ከሴቶች የተለየች ቅ.ማርያም ፤

«ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ» (ሉቃ. ፩፡ ፵፫-፵፱) ። ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው) ።

«ቡርክት አንቲ እምአንስት» መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ ፤ ያላደረብሽ ፤ ስለዚህም በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን የምትሰጭ እናት ነሽ ። ከሴቶች ይልቅ አንች ከፍ ያልሽ ፤ የከበርሽ ፤ የተመሰገንሽ ነሽ ፤ አንች ምልዓተ ጸጋ ፤ ምልዕተ ክብር ነሽና ። አንች ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን የአገኘሽ ነሽ ። ቅ/ማርያም ሆይ! አንቺ የእግዚአብሔር እናት ትሆኚ ዘንድ የታደልሽ ነሽ ፤ ስለዚህም ከሴቶች ሁሉ የተለየሽ ነሽ ፤ ከሴቶች ሁሉ ይልቅ አንች የተባረክሽ ነሽ ማለት የሴቶችን ዕርግማን ሁሉ የምታስወግጂ ነሽ ። በእናታችን በሔዋን ምክንያት የመጣውን ዕርግማን ያስወገደች እርሷ ናትና ።





ክብር ካላቸው ፤ ጸጋም ከተሰጣቸው ሴቶች ሁሉ ይልቅ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ። በመላእክት የምትመሰገኚ እመቤት ከመላእክትም ይልቅ አንቺ የከበርሽ ነሺና ። ጸጋን የታደለች በመንፈስ ቅዱስም የተመላች ኤልሳቤጥ ሳትቀር «አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ የሆድሽም ፍሬ የተባረከ ነው» ስትል ገልጣ አመስግናታለችና (ሉቃ. ፩.፵፪)።

ድንግልናን ከእናትነት ፤ ግርድናን ከእመቤትነት ጋር አስተባብራ የያዘች ቅድስት ማርያም ብቻ ናት ፤ ይኸም ክብር የተሰጠ ለእርሷ ብቻ ነው ፤ ስለዚህ ከሴቶች ሁሉ ትበልጣለች ከሁሉም ይልቅ ትከበራለች ። ሌሎች ሴቶችን የምናከብራቸው ዝነኛ ታላላቅ ሰዎችን ወለዱ ፤ የታላላቅ ሰዎችም እናቶች ናቸው ብለን ነው ፤ ቅ.ማርያምን ግን የአምላክ ሰማይ ወምድር እናት ሆነች ፤ እርሱንም ወለደች ብለን ነውና ፤ ይኸም ሁናቴ ከሌሎች ሴቶች የተለየች ያደርጋታል ። እመቤታችን ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት በቅድስና ናት ፤ ሌሎችን ሴቶች ጽኑዓት ናቸው ብንል ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው በኋላ ግን ፈቲው አለባቸው ፤ ተፈትሖ ማሕፀንም አለባቸው ፤ ቅ/ማርያም ግን ጌታን ከመፅነሷም በፊት ከመፅነሷም በኋላ ጌታን ከመውለዷ በፊ





ትም ጌታንም ከወለደችው በኋላ ጽንዕት ናት ተፈትሖም ፈቲውም የሌለባት ድንግል ናትና ቡርክት አንቲ እምአንስት አለ ። ይኸም ሁሉ ተደምሮ ቅ/ማርያምን ከሴቶች ሁሉ የተለየች ያደርጋታል ፤ ስለዚህ ቡርክት አንቲ እምአንስት እያልን እናመሰግናታለን ።

ቅ/ማርያም ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀንዋ ወስናለች ፤ ይኸም ከሆነ ከሰማይም ከምድርም ትበልጣለች ፤ ከሰማይም ከምድርም ይልቅ ትከበራለች ፤ ከሁሉም ተለይታ የተባረከች ናት ።

ሴቶች ንጉሥን ልዑላንን ኀያላኑን ወለዱ ተብለው ይመሰገናሉ ፤ ቅ/ማርያም ግን የነገሥታትን ንጉሥ ፤ የኃያላኑን ኀያል ኢየሱስ ክርስቶስን ወልዳለች ስለዚህ ከሴቶች ተለይታ የተባረከች የተመሰገነች የከበረችም ናት ።

«ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ» የማሕፀንሽ ፍሬም የተባረከ ነው ፤ ማለት ቡሩክ ነው ፤ ምስጉን ነው ፤ የምስጋና ጌታ የክብር ባለቤት ነው ። ቅ/ማርያም ያለ ወንድ ዘር አካላዊ ቃልን የፀነሰችው ስለሆነ ለእመቤታችን ብቻ ሰጥታ የማሕፀንሽ ፍሬ ስትል ተናገረች ፤ አካላዊ ቃል በማሕፀንዋ ተቀርፆ ፍጹም





አካል ነሥቶ የሚወለድ ነውና ። እርሱም ዕርግማንን የሚያጠፉ በረከትን የሚሰጥ ለሁሉ ጸጋን የሚያድል ነውና ። እንዲህ ያለውን ወሀቤ ጸጋ የሆነውን አምላክ የጸነሰች ቅ/ማርያም የተባረከች ናት ።

ብዙዎች ነቢያት «ቡሩክ ዘይመጽእ ፤ ቡሩክ አንተ በጽርሐ ቅድሳተ ስብሐቲከ ፤ ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ------እያሉ» የምስጋና ጌታ መሆኑን መስክረው ተናግረው ነበርና ቅ/ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ ቡሩክ ፤ ምስጉን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትወልድ ገልጣ «ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ» በማለት ተናገረች ።

የተባረኩ ልጆች ሲወለዱ ፍሬ ከርሥ ይባላሉ ፤ ያለዚያ ግን ማሕፀኑም የተረገመ ነው ፤ ፍሬውም የተረገመ ይባላል ፤ እመቤታችን ግን እርሷም ቡርክት ናት የማሕፀንዋ ፍሬም ቡሩክ ነው የባሕርይ አምላክ ነውና ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ አለ ።

## ፭፡ ምልዕተ ጸጋ ማርያም ፤

«ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ » (ሉቃ. ፩.፳፰) ።

(ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚ

እብሔር ከአንቺ ጋር ነውና) ።

ጸጋን የተመላሽ ማለቱ ጸጋን ለሁሉ የሚያድ
ለው አምላክ እናት ሆናለችና ፤ ስለዚህም የጸጋ
መገኛ ለሚሆነው እናት ከሆንሽ አንቺ ጸጋን የተመ
ላሺ ነሺ ማለቱ ነው ።

አዳምና ሔዋን በሠሩት በደል የሰው ዘር
ሁሉ ከጸጋው ተለይቶ ፤ ጸጋውንም ተገፎ ይኖር
ነበር ፤ አምላክ ዓለሙን ታርቆ ወደዚህ ዓለም
ሲመጣ ግን ለድኅነታችን ድልድይ መሸጋገሪያ
የሆነችው ቅ/ማርያም በመጀመሪያ ምልዕተ ጸጋ ፤
ምልዕተ ክብር ሁና መገኘቷን መልአኩ ቅ/ገብርኤል
ገልጦ ተናገረ ።

ጸጋ ብዙ ዓይነት ነው ፤ ልጅ መውለድ ለሴ
ቶች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋ ነው ፤ በተለይ
ከፍ ያለ የታወቀ ሲወለድ ጸጋው ይጐላል ፤ ቅ/ማር
ያም ግን ልጅ መውለዷ አንድ ጸጋ ሲሆን አምላክን
በመውለዷ ደግሞ ምልዕተ ጸጋ ያደርጋታልና ።

ምልዕተ ጸፀ በማለት መልአኩ የተናገረውን
ቃል ራሷ ቅድስት ማርያም «ብርቱ የሚሆን እርሱ
ለኔ ታላቅ ሥራን ሠርቷልና -------»ስትል በመ
ተርጐም እግዚአብሔር ጸጋ አድርጐ የሰጣትና
የሠራላት ብዙ መሆኑን መስክራ ተናግራለች (ሉቃ.
፩. ፵፱)።





እግዚአብሔር አምላክ ጸጋውን ሰፍሮ ወስኖ
አይሰጥም ፤ ለሰው ሁሉ እንደ ሃይማኖቱ ጽናት
እንደምግባሩ ብዛት ለመሸከም እንደሚችለው ይሰ
ጠዋል እንጂ ፤ ስለዚህ ቅ/ማርያም በሃይማኖት በም
ግባር የጸናች፤ በንጽሕና በቅድስና ያጌጠች፤ለጸጋው
መተላለፊያ የበቃች ስለነበረች ጸጋው በዝቶ ተሰጥቷ
ታል ፤ ስለዚህ ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር ሁናለች።

«እግዚአብሔር ምስሌኪ» እግዚአብሔር ከአንቺ
ጋር ነው፤ማለት ከበደል በኋላ እግዚአብሔር አምላክ
ከሰው ተለይቶ ከሰውም ርቆ ነበር፤እንዲያውም ሰውን
በመፍጠሩ እንደተጸጸተ ድምፅ ያሰማበት ጊዜ አለ
(ዘፍ.፮.፮) ። በዚህ መልክ እግዚአብሔር ወደ
ሰው ቀረበ ፤ አንድነቱንም ከሰው ጋር አደረገ ፤
ለዚህም ለመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ
የቻለችው በንጽሕና በቅድስና የተዋበችው ቅ/ማር
ያም ስለሆነች መልአኩ ቅ/ገብርኤል እግዚአብሔር
ከአንቺ ጋር ነውና ሲል ተናገረ ። እንዲሁም
አምላክ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ባሕ
ርይዋን ባሕርይ አድርጐ በማሕፀኗ አድሯልና እግ
ዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው አለ ።

ቅ/ማርያምን ምልዕተ ክብር ምልዕተ ጸጋ
የሚያሰኛት ፩ኛው እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር በመ





ሆኑ ነው ።

ከሔዋን ጋር አንድ የሆነው በሥጋ ከርሷ
የተሰወረው ሰይጣን ነበር ፤ ስለዚህም በአንድ
ጊዜ የሚያልፍ ሳይሆን በእርሷም በልጆቿም ላይ
የሚቀጥል ኀዘንን አተረፈላት ፤ ከቅ/ማርያም ጋር
የሆነው ግን በሥጋ ሰብእ የተገለጠው አካላዊ
ቃል ነው ፤ ስለዚህም በእርሷም በአደራ ልጆችዋ
በምእመናንም ላይ እየቀጠለ ያለማቋረጥ የሚሄድ
የሚያስደስት የምሥራች ሰማች ። ቅ/ማርያም ለጊ
ዜው እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው የሚለውን ቃል
ሰማች እንጂ በፍጻሜው ግን ሁላችንም ከእግዚ
አብሔር ጋር መሆናችን የሚያበሥር ቃል ነው፤
በቅ/ማርያም አማካይነት እግዚአብሔር ከኛ ጋር
ይሆናልና ፤ ቅ/ማርያም የወለደችው አምላክ ስሙ
አማኑኤል ተብሏል ፤ አማኑኤልም ማለት እግዚአ
ብሔር ከኛ ጋር ነው ማለት ነውና (ማቴ.፩.፳፫፤
ኢሳ. ፯. ፲፬) ።

## ፮. ሰአሊተ ምሕረት ማርያም

«ጸልዩ ወሰአሊ ለነ ምሕረተ ኀበ ፍቁር ወል
ድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ»
(ከተወዳጁ ልጅሺ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ
ለምኝልን ፤ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ)





«ጸልዩ ወሰአሊ ለነ» ለምኝልን ፤ አማልጂን
ማለት ነው የእመቤታችን ምስጋና እስከ አሁን
የተናገርነው ሁሉ ከወንጌል የተወጣጣ ነበር ፤
ይኸ ግን የቤተ ክርስቲያናችን ምስክርነት ስለእ
መቤታችን ግብር ማለት ፤ የአማላጅነቷን ሥራ
የሚገልጥ ነው ። እመቤታችን ቅ.ማርያም ከልጅዋ
ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የማማለድ ቃል ኪዳን
እንደተቀበለች ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ፤
ስለዚህ ኪዳነ ምሕረት የሚባል ሌላ ስም ለእመ
ቤታችን አላት ፤ ይኸም የሚያመለክተው የአም
ላክ እናት እንደመሆኗ ስሟን የጠራው ፤ በቃል
ኪዳኗም የተማጸነው ሁሉ ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ
ነፍስ የሚያገኝ መሆኑን ፤እመቤታችን የምታማልድ
መሆኗን የሚያረጋግጥ ትምህርትና ምስክርነት ነው።

ቅድስት ማርያም የምሕረት ቃል ኪዳን ከአ
ምላክ ዘንድ ስላላት ሰአሊ ለነ ፤ ጸልዪልነ ፤ ተን
ብሊ ለነ እያልን ሁላችን እንድንለምናት እንድንማ
ጸንባትም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታስተም
ራለች «---- ጻድቁን በጻድቁ ስም የተቀበለ
የጻድቁን ዋጋ ያገኛል (ማቴ. ፲. ፵፩ —፵፪)።
ያለው አምላካዊ ቃል እውነት ነው ፤ ይኸም ከሆነ
ከተቀደሱት ይልቅ የተቀደሰች ከጻድቃንም ይልቅ

ጻድቅት የሆነች የአምላክ እናት ቅ/ማርያም ስለሆነች የእርሷን ስም የጠራ ፣ በእርሷም ስም የተቀበለ የእርሷን ዋጋ ያገኛል ማለት ነውና ።
የቅ. ማርያም ክብሯን በመግለጥ ምስጋናዋን በማቅረብ ሲናገር መጥቶ አሁን በቃል ኪዳኗ መማጸን እንድታማልደንም መለመን እንዳለብን ተገቢነቱን ለመግለጥ ጸልዩ ወሰአሊ ለነ በማለት አመለከተ ።

«ኀበፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ» የማዳን ኃይል ያለው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ እርሱም ልጅዋ ፤ ወዳጅዋ ነው ፤ ስለዚህም የእናት ልመና ፊት አያስመልስም አንገት አያስቀልስምና ታማልደናለች ፤ ስለዚህ አማልጂን ለምኝልን እንላታለን ።

የምትወደው ልጅዋ የሚወዳት እናቱ እንደሆነች በመከራ በመስቀልም ላይ እያለ እንኳን አልረሳትም ነገር ግን ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ የእናቱን ነገር አደራ ሲል ሰጠው እንጂ (ዮሐ. ፲፱ ፳፯)።
ቅ/ማርያም እናት እንደመሆኗ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ሲበተኑ ጥለውትም ሲሸሹ በመስቀሉ አንጻር ከዮሐንስ ጋር ቁማ ስታለቅስ ውላለች እንጂ ከቶ ለደቂቃ እንኳን አልተለየችውም (ዮሐ. ፲፱.፳፭) ።





«ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ» እኛን ለማዳን ሲል ሰው ከሆነው ከልጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ለምኝልን ኃጢአታችንን ያሥተሠርይልን ዘንድ ። በጌታ ማመናችን የጌታን እናት መማጸናችን አምላክ ይቅር እንዲለን ከበደላችንም እንዲያነፃን ነው ። አምላክ ሰው የሆነው ከቅ.ማርያምም የተወለደው እኛን ለማዳን ከበደላችንንም ለማንፃት ነው፤ስለዚህ ቅ.ማርያም ከልጅዋ ከወዳጅዋ እንድታማልደን በደላችንን ኃጢአታችንንም በመናዘዝ ወደ ቅድስት ማርያም እንቀርባለን እንለምናለንም ኃጢአታችንን ልጅዋ ወዳጅዋ ያስተሠርይልን ዘንድ ። ቅ/ቤተ ክርስቲያናችን የቅድስት ማርያምን አማላጅነት ታምናለች በቅ/ማርያም ቃል ኪዳን ትማጸናለች ፤ ስለዚህ ለምኝልን ፣ አማልጅን እያልን እንድንጸልይ ታዛለች ።

ሁሉን ይቅር የሚል ይቅርታም ገንዘቡ የሆነ አምላክ ስለሰው ድኅነት ሰው ሁኗል ፣ ለዚህም ለድኅነታችን መሸጋገሪያ ምክንያት የሆነችው ቅ/ማርያም ናት ፣ ዛሬም ለአምላክ ምሕረት መትኣለፊያ ለኛ በደል ማስተሥረያ ምክንያት የምትሆን እርሷ ናትና አማልጅን ለምኝልን እንላታለን ። ክስርቶስ ሰው ለመሆን ወደዚህም ዓለም ለመም





ጣት ምክንያት እንደሆንሺ ለኛ ድኅነት ማግኛ ፤ ለአምላክ ምሕረት መተላለፊያ ምክንያት ሁኚን ማለት ነው ።

ሁሉን ለማዳን አምላክ ምክንያት ይፈልጋል፣ እመቤታችንም ምክንያተ ድኂን ናት ፣ ስለዚህ ለኛ ለእያንዳንዳችን መዳኛ ምክንያት አማላጅ መሆኗን አምነን ልንለምናት በቃል ኪዳኗም ልንማጸንባት ይገባናል ።

## ፯. ለይኩን

«አሜን ፤ ለእመቤታችን ምስጋና ፣ ሰላምታ የሚገባ ነው ፣ ስለዚህ የተናገርነውና ያተትነው ሁሉ ይሁን ይደረግ! የአማላጅነቷም ቃል ኪዳን በሁላችን ላይ ይሁን ይደረግ! አሜን ።